ትምህርት ዐሥር

የመጀመሪያ ቀን ማርቆስ 5–7

1ኛ ጥያቄ፡– ሀ) የሰይጣን ጎይል አይሎ ያየህበትን ጊዜ ግለጽ። ለ) የኢየሱስ ጎይል ሰይጣንን ሲያሸንፍ ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ። ይህ ስለ ኢየሱስ ምን ያስተምረናል? ሐ) ብዙ ክርስቲያኖች ሰይጣንን፥ ቡዳን፥ እርግማንን የመሳሰሉትን የሚፈሩት ለምንድን ነው? መ) መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ፍርሃት ምን ያስተምራል?

የግርማ አባት ጠንቋይ ነበሩ። እርሱ ከልጅነቱ ጀምሮ ለሰይጣን የተሰጠ በመሆኑ ብዙ ክፉ መናፍስት ሰፍረውበት ነበር። እያደገ ሲመጣ የሰይጣን ጭቆና በዛበት። አንድ ቀን ጭንቀቱን መቋቋም ተስኖት ራሱን ለማጥፋት ሞከረ። በዚህ ጊዜ አንድ ክርስቲያን ሕይወቱን አተረፈለት። ክርስቲያኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያምን ከሰይጣን ነፃ እንደሚወጣ ገለጸለት። ግርማም ምስክርነቱን ሰምቶ አመነ። ወዲያውኑ ክፉ መናፍስት ወደ መሬት ጣሉት። እዚያ ወድቆ ይንፈራፈርና ያጓራ ጀመር። ክርስቲያኑ ወዳጆቹን ሰብስቦ ብዙ ጸሎት ካደረገ በኋላ፥ መናፍስቱ ለቅቀውት ወጡ።

በቀጣዩ እሑድ ግርማ በአቅራቢያው ወደምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ሄደ። በአምልኮው ጊዜ አንድ ሰው፥ ሰይጣን ታስሮ ወደ ጥልቁ እንዲወርድ እያዘዘ ሲጸልይ ሰማ። ሰዎች፥ «በኢየሱሱሱሱሱስ ስም?» እያሉ ይጮኹ ጀመር። «ሰዎች የኢየሱስን ስም እንዲህ የሚጠሩት ለምንድን ነው?» ሲል አሰበ። ክርስቲያኖቹ የግርማ አባት ኃይል አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ቃላት በሚደጋግምበት መንገድ የኢየሱስ ስም ምትሐታዊ ኃይል አለው ብለው ስለሚያምኑ ይሆን?

በሌላ ስፍራ ከአንድ ጠንቋይ አጠገብ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተከፍቶ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ጠንቋዩ ሌሊት ሌሊት ከበሮውን እየመታ በማጓራት ክርስቲያኖችን ይረግም ነበር። በዚህ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ተማሪዎች ይፈራሉ። ከመኝታ ክፍላቸው ተሯሩጠው በመውጣት፥ «በኢየሱሱሱሱስም ስም!» እያሉ ድምፃቸውን አጉልተው ይጮኻሉ።

ኢየሱስ ከሰይጣን ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት አለው? እኛ በሰይጣን ላይ ምን ሥልጣን አለን? የኢየሱስ «ስም» ከሥልጣናችን ጋር ምን ግንኙነት አለው? የኢየሱስን ስም እየደጋገሙ መጥራቱ ተጨማሪ ኃይል ይሰጠዋል?

ይሄ የሚያጠራጥር አይደለም። የምንፋጠጠው ከሰይጣን፥ ከትልቅ ጠላት ጋር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሊውጠን ፈልጎ ከሚያገሳ አንበሳ ጋር ያነጻጽረዋል (1ኛ ጴጥ. 5፡8)። ጎይሉ ከፍተኛ ነው። ተአምራትን መሥራት ይችላል፥ ተፈጻሚነት የሚኖራቸውን እርግማኖችና ሌላም ሊያደርግ ይችላል። ነገር ግን ኢየሱስን በመታዘዝ ከሚመላለሱ ክርስቲያኖች ጋር ሲነጻጸር፥ ጎይሉ ምንድን ነው? ከዚህ በበለጠ ደግሞ ከኢየሱስ ጋር ሲነጻጸር፥ ጎይሉ ምንድን ነው? ለክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እውነት በግልጽ መረዳቱ አስፈላጊ ነው። ልናስወግዳቸው የሚገቡን ሁለት አክራሪ አቋሞች አሉ። ብዙ የተማሩ በተለይም በምዕራቡ ዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖች ሰይጣንን ችላ ይላሉ። ሰይጣን መኖሩን ሊያምኑ ቢችሉም፥ ስለ እርሱ አያሳስባቸውም። ዛሬ

እንደምንመለከተው ሰይጣን ብርቱ ጠላት ስለሆነ፥ እነዚህ ክርስቲያኖች በእርሱ ተሸንፈዋል። ሰይጣን ክርስቲያኖችን ለማሸነፍ የሚሠራባቸውን መንገዶች የማያውቁትን ክርስቲያኖች በቀላሉ ያጠቃቸዋል። ሌሎች ደግሞ ስለ ሰይጣን ሁልጊዜም ያስባሉ። በሚጸልዩበት ጊዜ ሁሉ ሰይጣን ወደ ጥልቁ እንዲጣል ያዝዛሉ። የሚደርሰው ጉዳት ሁሉ የሰይጣን ጥቃት እንደሆነ ያምናሉ። ብዙውን ጊዜ የሰይጣንን ጎይል ይፈራሉ። እርሱን እየፈሩ ስለሚኖሩ ሰይጣን እነርሱንም አሸንፎአቸዋል። ይህም መንፈሳዊ ሕይወታቸው ጠንካራና በድፍረት የተሞላ እንዳይሆን ያደርገዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰይጣን ብዙ ያስተምራል። አራት ዐበይት እውነቶችን ማስታወስ አለብን፦

ሀ. ሰይጣን ህልውናው የተረጋገጠ ጎይለኛ ጠላታችን ነው። የእግዚአብሔር መራራ ጠላት ሲሆን፥ ሰዎችን በራሱ የጨለማ መንግሥት ለማቆየት ወይም የእግዚአብሔር መንግሥት አካል የሆኑትን ወገኖች ውጤታማነት ለመቀነስ ተግቶ ይሠራል።

ለ. ኢየሱስ በሰይጣን ላይ ሙሉ ሥልጣንና ጎይል አለው። ሰይጣንና አጋንንት ኢየሱስ ማን እንደሆነ ስለሚያውቁ ይፈሩታል (ያዕ. 2፡19)። ይታዘዙታል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደተጻፈው ኢየሱስ ከሰይጣን ወይም ከአጋንንት ጋር ሲገናኝ፥ በአንዲት የትእዛዝ ቃል ያሸንፋቸው ነበር።

ሐ. ሰይጣን ተሸንፎአል። ኢየሱስ በመስቀል ላይ የጎጢአታችንን ዕዳ በመክፈል፥ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ልጆች ለመክሰስ የሚጠቀምበትን ሥልጣን አስወግዶል። በዚያም የፍጻሜያቸውን እርግጠኛነት በማሳየት ምርኮ ወስዶል (ቆላ. 2፡13–15)። በሰይጣን ላይ ዐቢዩን ድል ከተጎናጸፍን በኋላ፥ ሰይጣን የሸንፈት ጦርነት በሚያካሂድበት ዘመን ውስጥ እንኖራለን። ኢየሱስ በዳግም ምጽአቱ ሰይጣንና አጋንንቱን ወደ ሲኦል በመስደድ ሙሉ በሙሉ ያሸንፋቸዋል (ራእይ 20፡7–10)።

መ. ክርስቲያኖች «በክርስቶስ» ስለሆንን፥ ጥበቃውና ሥልጣኑ አይለየንም። መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎቻችንን እስከ ለበስን ድረስ (አፌ. 6፡10–18 አንብብ)፥ የሰይጣንን ጥቃት መፍራት የለብንም። ሰይጣን አምልኳችንን እንዳይረብሽ ወይም በሕይወታችን ውስጥ ጣልቃ እንዳይገባ፥ እያሰርነው እንድንጸልይ የተሰጠ ትእዛዝ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አይገኝም። ትኩረት የተሰጠው መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎችን በመልበስ፥ ከሰይጣን ጥቃት የተጠበቅን መሆናችንን በማረጋገጡ ላይ ነው። በብቁ ሁኔታ የታጠቀ ሠራዊት የተሸነፈን ዓማፂ መፍራት የለበትም። እኛም ሰይጣንን መፍራት የለብንም። በክርስቶስ ሥልጣን ሥር እስከ ተጠለልን ድረስ ሰይጣንን እናሸንፋለን። በራሳችን ጎይል ብንዋጋ ግን ምንጊዜም አናሸንፍም። «በኢየሱስ ስም» ከታገልነው በራሳችን ሳይሆን፥ በክርስቶስ ኃይል እናሸንፋለን።

ይሁንና ብዙ ክርስቲያኖች «በኢየሱስ ስም» እየጸለዩ ሰይጣንን መዋጋት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በትክክል አያውቁም። «በኢየሱሱሱስ. . . ስም» የሚሉት፥ ስሙን እየጠሩ የሚጮኹት፥ ወይም የኢየሱስን ስም ሦስት ጊዜ የሚጠሩት ለምንድን ነው? ይህ ሁሉ የመጣው መጽሐፍ ቅዱስ

በኢየሱስ ስም ስላለን ሥልጣን የሚያስተምረውን ጠንቅቆ ካለማወቅ ነው። «በኢየሱስ ስም» መጸለይ ማለት ምን ማለት ነው? <u>በመጀመሪያ</u>፥ ጎይልን የምናገኘው በኢየሱስ ስም ብለን በመጮኻችን አይደለም። ስለሆነም «በኢየሱሱሱሱ...ስ ስም» ማለቱም ሆነ መጮኹ ወይም ሦስት ጊዜ መደጋገሙ የሚጨምረው ነገር አይኖርም። ስለዚህ የኢየሱስን ስም እንደ ምትሐታዊ ቃል ከመጠቀም መጠንቀቅ አለብን። ይህን በማድረግ ከፉ መናፍስትን ለመቋቋም ከታቦችን ከሚያንጠለጥሉ ሰዎች ጋር እንዳንመሳሰል ልንጠነቀቅ ይገባል። <u>ሁለተኛ</u>፥ በራሳችን ጎይልና ሥልጣን እንደሌለን ለሰይጣን መናገራችን ነው። የጸሎታችንና የትእዛዛችን ሥልጣን ሁሉ የሚመጣው ከክርስቶስ ጎይል ነው። እኛ ያለን በውክልና የተሰጠን ጎይልና ሥልጣን ብቻ ነው። ስለዚህም፥ በኢየሱስ ክርስቶስ የምናምንና ሰይጣንን ለማሸነፍ፥ ከክርስቶስ ሥልጣን የተሰጠን ሰዎች በመሆናችን፥ ሰይጣንን እናዝዘዋለን። (<u>ማስታወሻ</u>፦ ይህ ጸሎታችንን «በኢየሱስ ስም» ብለን ከምንፈጽምበት ሁኔታ ጋር አንድ ዓይነት ፍች አለው። ይህን ስንል ወደ ሁሉን ቻይ እምላክ ለመምጣትና ከእርሱ ዘንድ መልስ ለመጠበቅ የቻልነው፥ ከክርስቶስ ጋር ባለን ግንኙነትና ወደ እግዚአብሔር እንድንመጣ በሰጠን ሥልጣን ምክንያት መሆኑን መግለጻችን ነው። ይህም በእግዚአብሔር ፊት የቀረብነው በራሳችን ጽድቅና የብቃት ስሜት እንዳልሆነ የምንገልጽበት ነው።)

2ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ሰዎች የኢየሱስን ስም ጮክ ብለው የሚጠሩት ወይም የሚደጋግሙት ለምንድን ነው? ለ) ከላይ ከቀረበው ትምህርት አንጻር፥ ጸሎታችን እንዴት ሊለወጥ ይገባል?

3ኛ ጥያቄ፦ ማር. 5–7 አንብብ። ሀ) እነዚህ ምዕራፎች ስለ ኢየሱስ ምን ያስተምሩናል? ለ) ኢየሱስንን ስለ መከተል ከእነዚህ ምዕራፎች ምን እንማራለን?

1. ኢየሱስ በአጋንንት የተያዘን ሰው ፈወሰ (ማር. 5፡1–20)።

ኢየሱስ በሰይጣን ላይ ሙሉ ሥልጣን እንዳለው በግልጽ ከሚያሳዩት ነገሮች አንዱ፥ በጌርጌሴኖን አካባቢ በብዙ ከፉ መናፍስት የተያዘውን ግለሰብ ባዳነበት ሁኔታ ተገልጾአል። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፥ እነዚህ ከፉ መናፍስት ክርስቶስን ለይተው አውቀውታል። ስለዚህም፥ ኢየሱስ «የልዑል እግዚአብሔር ልጅ» እንደሆነ በግልጽ አውጀዋል። ይህም ኢየሱስ ራሱ አምላክ እንደሆነ የሚያመለክት ነበር። ኢየሱስ በእነርሱ ላይ ሙሉ ሥልጣን እንዳለውና እግዚአብሔር ለዘመናት የወጠነው ዕቅድ በሚፈጸምበት ጊዜ፥ ኢየሱስ ወደ ሥቃይ ስፍራ (ሲዖል) እንደሚልካቸው ያውቁ ነበር።

ይሁንና፥ የኢየሱስ ጎይል ከሰይጣን ጋር የሚነጻጸረው እንዴት ነው? ኢየሱስ ከሰይጣን የሚበልጠው ትንሽ ብቻ ነው? ማርቆስ የኢየሱስ ጎይል ፍጹማዊ እንደሆነና መጨረሻ በሌለው ሁኔታ ከሰይጣን ጎይል እንደሚልቅ አሳይቷል። በሮም ሠራዊት፥ አንድ ሌጌዎን (ጭፍራ) 6,000 ወታደሮችን ይይዛል። አጋንንት መንፈሳዊ ፍጥረታት ስለሆኑና አካላዊ ስፍራ ስለማይይዙ፥ በዚህ አንድ ግለሰብ ሰውነት ውስጥ 6,000 ከፉ መናፍስት ነበሩ። ነገር ግን ኢየሱስ ይህን የአጋንንት ሠራዊት ምን አደረገው? ፈራቸው?

በፍጹም። አጋንንቱ እርሱን እንዳዩ በፍርሃት ተሸበሩ። ወደ ሥቃይ ስፍራ እንዳይሰዳቸው ኢየሱስን ለመኑት። ቀላል ትእዛዙን ሰምተው ለመታዘዝ ተገደዱ። ከፋት በባሕርዩ ራሱ ያጠፋል። ይህንኑ ለማሳየት፥ ክፉ መናፍስት ወደ እሪያዎች ገብተው ገደሏቸው። ክፉ መናፍስቱ አልሞቱም ነበር። ነገር ግን የመኖሪያ ስፍራቸው ተወሰደባቸው።

በተጨማሪም፥ ማርቆስ ለዚህ የኢየሱስ ታላቅ ተግባር ሁለት የተለያዩ ምላሾችን ያነጻጽራል። አብዛኞቹ ሰዎች ለኢየሱስ ለመገዛትና እርሱን ለማክበር ስላልፈለጉ፥ ከአካባቢያቸው ለቅቆ እንዲሄድ ጠየቁት። በአጋንንት ተይዞ የነበረው ሰውዬ ግን ኢየሱስን ለመከተል ፈለገ። ኢየሱስ ግን ለዚህ ሰው የተሻለ አገልግሎት ሰጠው። ክርስቶስ ግለሰቡ ወደ ቤተሰቡ ተመልሶ እግዚአብሔር ስላደረገለት ምሕረት እንዲመሰክር ነገረው። ከደቀ መዛሙርት የሚጠበቀው ምንድን ነው? ማርቆስ ደቀ መዛሙርት ለሌሎች ስለ ክርስቶስ መመስከር እንዳለባቸው አመልክቷል። ነገር ግን የምስክርነታችን ዋና ነገር ምን መሆን አለበት? የተወሳሰበ ክርክር ወይም ሥነ መለኮታዊ እውነቶችን ማስተማር መሆን አለበት? አይደለም። ክርስቶስ ከሁሉም የሚበልጠውን ታላቅ ምስክርነት እኛን ለማዳን ያከናወነውንና አሁንም እኛን ለመርዳት እያከናወነ ያለውን ተግባር ለሌሎች ማካፈል እንደሆነ አሳይቷል። ብዙ ሰዎች ወደ ክርስቶስ የሚመለሱት ጥሩ በሚመስሉ ክርክሮች አማካኝነት ሳይሆን፥ በሚያውቋቸው ሰዎች ሕይወት ክርስቶስ የሚሠራውን በማየት ነው።

4ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በቅርቡ ኢየሱስ በሕይወትህ እየሠራ ያለው እንዴት ነው? ለ) ይህንን ለሦስት የማያምኑ ሰዎች አካፍልና ውጤቱን ለጥናት ቡድንህ ለማካፈል ተዘጋጅ።

---

2. ኢየሱስ የሞተች ልጅ አስነሣ፥ የታመመች ሴት ፈወሰ

(ማር. 5፡21–43)

በሰዎች ላይ ከፍተኛ ፍርሃትና የተሰፋ መቁረጥ ስሜት የሚያስከትሉ ሁለት ነገሮች አሉ። <u>በመጀመሪያ</u>፥ ከሁሉም የከፋው የሰው ልጅ ጠላት ሞት ነው። ኢየሱስ በሞት ላይ ምን ሥልጣን አለው? የሚለው ምላሽን የሚሻ ጥያቄ ነበር። <u>ሁለተኛ</u>፥ የረዥም ጊዜ ሕመም አለ። ኢየሱስ ለረዥም ጊዜያት ሐኪሞችን ሁሉ አሸንፎ የቆየን በሽታ ሊፈውስ ይችላል? ማርቆስ እነዚህን ሁለት ታሪኮች በመጠቀም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ፥ እነዚህን ሁለት ጠላቶች ሊያሸንፍ እንደሚችል አሳይቷል።

የመጀመሪያው ታሪክ ለ 12 ዓመታት ደም ስለሚፈሳት ሴት የሚናገር ነበር። ከዚህ በሽታ የተነሣ ሴትዮዋ ከማኅበረሰቡ ተገልላ ትኖር ነበር። የዚህ ዓይነት ችግር ያለባቸው ብዙ ሴቶች ከትዳራቸው ለመፈናቀል ተገድደዋል። ይህች ሴት መፍትሔ ለማግኘት ወደ ብዙ ሐኪሞች ዘንድ ብትሄድም አልተሳካለትም ነበር። የመጨረሻ ተስፋዋ ኢየሱስ ስለነበር፥ በሕዝብ መካከል እየተጋፋች ሄዳ ልብሱን ነካችው። ወዲያውም ተፈወሰች።

ኢየሱስ በነበረበት ስፍራ እንዲቆምና ይህች ሴት እንደነካችው እንድታምን ያስገደዳት ለምን ነበር? ኢየሱስ ሁሉንም ነገር ስለሚያውቅ፥ እንደ ነካችው ቀድሞውኑ ተረድቶ ነበር። ክርስቶስ ይህንን ያደረገው

የመፈወስ ችሎታውን ለማሳየት አልነበረም። ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ ስለ ተአምራቱ ለሌሎች እንዳይናገሩ ሰዎችን ያስጠነቅቅ ነበርና። ነገር ግን ኢየሱስ ለዚህች ሴት ስለ ራሱ አንድ ነገር ለማስተማርና ወደ መንፈሳዊ ፈውስም ለመምራት ፈልጎ ነበር። ኢየሱስ ምንጊዜም በሥጋዊ ፈውስ ብቻ ስለማይረካ፥ ለእያንዳንዱ ሰው የመንፈሳዊ ፈውስ ዕድል ለመስጠት ይፈልጋል። ለዚህም ነው ሕዝቡን ሁሉ ከመፈወስ ይልቅ በግለሰብ ደረጃ መፈወስን የመረጠው። ስለሆነም ኢየሱስ ሴቲቱ የተከሰተውን ሁኔታ እንድታምን በማድረግ፥ እምነቷ ሥር እንዲሰድ እያደረገ ነበር። ሴትዮዋ ሥጋዊ ፈውስ ብታገኝም፥ መንፈሳዊ ፈውስና እውነተኛ ሰላምን ማግኘት ያስፈልጋት ነበር። በማርቆስ ወንጌል ኢየሱስ ለፈውስ የተጠቀመው ቃል «መዳን» ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ስለሆነም ሥጋዊ ፈውስ አግኝታ ከመከራዋ የዳነችው ይህች ሴት፥ አሁን ደግሞ መንፈሳዊ ፈውስን አግኝታ ሰላምን ተጎናጽፋለች።

በሁለተኛው ታሪክ፥ ኢየሱስ በቀላል የትእዛዝ ቃል የኢያኢሮስን ልጅ ከሞት አስነሥቷል። ከኢየሱስ ጋር ሲነጻጸር ሞት ኀይል ያለው ጠላት አይደለም። በቀላል የትእዛዝ ቃል ሁላችንም ከሞት እንነሣለን። ለዚህም ነው ጳውሎስ ለክርስቲያኖች የሞት መውጊያ እንደ ተሰበረ የጻፈው (1ኛ ቆሮ. 15፡53-56)።

በዚህ ታሪክ ውስጥ ሌላም አስገራሚ ነገር ተከስቷል። ኢየሱስ ተአምሩን ለማሳየት ደቀ መዛሙርቱን ሁሉ ከመውሰድ ይልቅ፥ ዮሐንስን፥ ያዕቆብንና ጴጥሮስን ብቻ ወሰደ። ይህ የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ቁልፍ መሪዎች ለሚሆኑት ለእነዚህ ሦስት ደቀ መዛሙርት፥ የሥልጠና ዓይነት ተግባር ነበር። ኢየሱስ ከ12ቱ በላይ በጥልቀት አስተምሯቸዋል።

3. ኢየሱስ ባደገባት የናዝሬት ከተማ ተቀባይነትን አጣ

(ማር. 6፡1-6)

ለብዙ ሰዎች፥ በተለይም እርሱን በቅርብ ለሚያውቁት ከስብእናው አልፎ የኢየሱስን መለኮታዊነት መመልከቱ ከባድ ነበር። በሥጋዊ ሁኔታው ኢየሱስን ከሌሎች ሰዎች የሚለይ ምንም ነገር አልነበረም። በአሁኑ ዘመን የክርስቶስን ሥዕል በብርሃን አሸብርቆ መሥራት የተለመደ ቢሆንም፥ ትክክለኛ መልኩ እንደዚህ ዓይነት አልነበረም። የናዝሬት ሰዎች ለምን ሊቀበሉት አልፈቀዱም? ምክንያቱም ከተአምራቱ ሁሉ ባሻገር፥ መለኮታዊነቱን ሊመለከቱ አልቻሉም ነበር። ኢየሱስ እንደ ሰው ተራ የአናጺነት ተግባር የሚያከናውን ሰው ነበር። ቤተሰቦቹ ድሆችና በማኅበረሰቡ ውስጥ የማይታወቁ ነበሩ። በሥጋዊ ሁኔታው መሢሕ የሚያስመስል ምንም ዓይነት ነገር አልነበረውም። ማርቆስ የኢየሱስን መለኮታዊነትና ሰብአዊነት ሚዛናዊ አድርገን ማነጻጸር እንዳለብን ገልጾአል። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም፥ ሰው ነው። ግልጽ ተቃውሞ በነበረበት ናዝሬት ኢየሱስ ተአምራትን የማድረግ ኃይል ቢኖረውም፥ ይህንኑ ከማድረግ ተቆጥቧል።

4. ኢየሱስ 12ቱን ደቀ መዛሙርቱን ላከ (ማር. 6፡6-13)።

አንድ ሰው ከተወሰነ ሥራ በላይ ሊያከናውን አይችልም፥ ስለሆነም፥ አገልግሎቱ እንዲያድግና ወደ ሁሉም ሰው እንዲደርስ ከተፈለገ፥ ክርስቶስ ሥራውን ለማከናወን ሌሎችን ማሠልጠን ያስፈልገው ነበር። ክርስቶስ ለተወሰነ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ሲያሠለጥን ነበር። እነዚህ ደቀ መዛሙርት ስለ ንስሐ ሲሰብክ፥ አጋንንትን ሲያወጣና ሰዎችን ሲፈውስ ተመልከተዋል። አሁን የተመለከቱትን ተግባራዊ የሚያደርጉበት ጊዜ ደረሰ። ክርስቶስ ብዙ ሰዎች ወንጌል የሚሰሙበትን አጋጣሚ ለማመቻቸትና ደቀ መዛሙርቱን በመፈተን ለአመራር ለማዘጋጀት ሲል፥ ሁለት ሁለት አድርጎ ላካቸው። ለዚህም ሁለት ምክንያቶች ነበሩ። <u>በመጀመሪያ</u>፥ እርስ በርሳቸው መደጋገፍ ነበረባቸው። አንድ ሰው (ወንጌላዊ) በቀላሉ ብቸኝነትና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ሊሰማው ስለሚችል፥ ሁለት ሆነው ጎብረት ሊያደርጉና ሊበረታቱ ችለው ነበር። <u>ሁለተኛ</u>፥ በአይሁዶች ልማድ አንድን እውነት ለማጠናከር ቢያንስ የሁለት ሰዎች ምስክርነት ወሳኝ ነበር (ዘዳግ. 19፡15)። ከዚህ የተነሣ፥ ስለ ክርስቶስ በቂ ምስክሮች ነበሩ። ክርስቶስ ያደረገውን ሁሉ (መስበክ፥ አጋንንትን ማውጣትና መፈወስን) 12ቱ ደቀ መዛሙርት የማከናወን ብቃት ተሰጥቷቸዋል። ማርቆስ ክርስቶስ ይህንን ሥልጣንና ኀይል እንደ ሰጣቸው ያሳያል። በተመሳሳይ መንገድ የእኛም ኃይልና ሥልጣን የሚመነጨው ከራሳችን ሳይሆን ከክርስቶስ ነው።

5ኛ ጥያቄ፡- መሪዎች ብዙውን ጊዜ እንደ ልባቸው የሚረዳቸው ሰው እንደሌለ በመግለጽ ያማርራሉ። ሀ) ክርስቶስ፥ ደቀ መዛሙርቱን ማሠልጠኑ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን መሪ አገልግሎቱን ለማስፋትና የቤተ ክርስቲያንን የአመራር ፍላጎቶች ለማሟላት፥ ሊያከናውን ስለሚገባው ተግባር ምን ዓይነት አርአያነትን ይሰጣል? ለ) ይህ ብዙም የማይታየው ለምን ይመስልሃል? ሐ) አንተ የቤተ ክርስቲያን መሪ ከሆንህ፥ እግዚአብሔር አሠልጥነህ በሥራህ ውስጥ የምታሳትፋቸውን አምስት ወጣቶች እንዲሰጥህ በጸሎት ጠይቅ።

5. የመጥምቁ ዮሐንስ አንገት መቀላት (ማር. 6፡14–29)

ማርቆስ የዮሐንስን መሞት የገለጸው አንዳንድ ዝርዝር ጉዳዮችን በመጨመር ነበር። ለምን? ምናልባትም የመጥምቁ ዮሐንስ ሞት በሌሎች ላይ ለሚደርሰው ስደት አርአያነት ያለው ተግባር ሳይሆን አይቀርም። መጥምቁ ዮሐንስ ክፋትን ስለ ተቃወመ ታስሮ ነበር። ሰዎች በኃጢአታቸው ሲቀጥሉ ዝም ብሎ ሊመለከታቸው ይችል የነበረ ቢሆንም፥ ይህን አላደረገም። እኛም በተመሳሳይ መንገድ የሰዎችንና የአገራችንን ኃጢአት ግጋለጥ አለብን። ይህንን በምናደርግበት ጊዜ ግን ስደት ሊገጥመን እንደሚችል ማወቅ አለብን።

6. ኢየሱስ አምስት ሺህ ሰዎችን መገበ (ማር. 6፡30–44)።

ማርቆስ ኢየሱስ አምስት ሺህ ሰዎችን እንደ መገበ በገለጸበት ታሪክ ውስጥ፥ ስለ ጠቅላላዎቹ ደቀ መዛሙርት የሰብክት ጉዞ ዘግቧል። «ሐዋርያ» የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ ሌላውን ሰው ወክሎ አንድን ተግባር የማከናወን ሥልጣን የተሰጠውን ሰው ያመለክታል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ፥ ይህ ቃል በሁለት የተለያዩ መንገዶች አገልግሏል። <u>በመጀመሪያ</u>፥ ይህ ለ12ቱ ደቀ መዛሙርት የተሰጠ ስያሜ ነው። አዲስ ኪዳን ሁልጊዜም እነዚህ 12 ደቀ

መዛሙርት ቤተ ክርስቲያንን ለመምራትና ከእግዚአብሔር የሆነውንና ያልሆነውን ለመበየን ሥልጣን እንደ ተሰጣቸው አድርጎ ያቀርባል። በተጨማሪም፥ አዲስ ኪዳን ጳውሎስም የ12ቱን ያህል ሥልጣን እንዳለው ያስተምራል (ሮሜ 1፡1)። ከጳውሎስና ከ12ቱ ሐዋርያት ሞት በኋላ በቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነት ልዩ ስፍራ የነበረው ሰው እንደ ነበር የሚያመለክት መረጃ የለም። ከእነዚህ መሪዎች ሞት በኋላ የዚህ ዓይነቱ ሥልጣን እንዳበቃ የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ጸሐፊዎች ጠቅሰዋል። ስለዚህ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሰዎች ምን ሊያደርጉ እንደሚገባ ለመናገር የሚያስችል ፍጹም ሥልጣን ያላቸው ሐዋርያት ይኖራሉ ብለን መጠበቅ የለብንም። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በቤተ ክርስቲያን ላይ ሙሉ ሥልጣን ያለን ሐዋርያት ነን የሚሉ ሰዎች ተግባር፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌለው አደገኛ ትምህርት ነው።

<u>ሁለተኛ</u>፥ ሌሎችም ሐዋርያት ተብለው ተጠርተዋል። ምንም እንኳ የተለየ ሥልጣን ቢኖራቸውም፥ የ12ቱንና የጳውሎስን የሚያህል ሥልጣን አልነበራቸውም። እነዚህ አገልጋዮች (እና የአዲስ ኪዳን የትንቢት ስጦታ የነበራቸው ሰዎች) ዐበይት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተደርገው የሚቆጠሩ ሲሆን፥ ምናልባትም እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን የመትከልና በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት የመምራት ስጦታ ከሰጣቸው ሰዎች ጋር ተመሳሳይ ሳይሆኑ አይቀሩም። በርናባስ (የሐዋ. 14፡14)፥ የጌታ ወንድም የሆነው ያዕቆብ (ገላ. 1፡19)፥ አንዲሮኒቆንና ዩልያን (ሮሜ 16፡7) ሐዋርያት መሆናቸው ተጠቅሷል።

ኢየሱስ አምስት ሺህ ሰዎችን ከመገበበት ታሪክ፥ ስለ ኢየሱስ አያሌ እውነቶችን እንመለከታለን። <u>በመጀመሪያ</u>፥ ኢየሱስ የሰዎችን ፍላጎት ለማሟላት፥ ነገሮችን የመለወጥና የማብዛት ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ልጅ ነው። <u>ሁለተኛ</u>፥ ኢየሱስ መልካም እረኛ መሆኑን እንመለከታለን። በመዝሙር 23፡1 እንደ ተመለከተው፥ ክርስቶስ የበጎቹን ፍላጎት ያሟላል። ይህ ታሪክ የክርስቶስ ተከታዮች ለሥጋዊ ፍላጎቶቻቸው፥ በተለይም ለሚበሉት ምግብ መጨነቅ እንደሌለባቸው ያስተምራል። ክርስቶስ ሁልጊዜም ለተከታዮቹ በመራራት ፍላጎታቸውን ያሟላላቸዋል። <u>በመጨረሻም</u>፥ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት (በተለይም ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች) ያላቸውን ትንሽ ነገር ወስዶ በማብዛት የእግዚአብሔርን መንጋ ፍላጎቶች እንደሚያሟላ የሚያስገነዝብ ነው። እንዲሁም፥ የሰዎችን ፍላጎቶች እንዴት እናሟላለን ብለን ሳንጨነቅ፥ ለእግዚአብሔር ያለንን በልግስና ልንሰጥና እግዚአብሔር እንደሚያባዛው ልንተማመንበት ይገባል። ምክንያቱም ሕዝቡ የእግዚአብሔር ሀብት በመሆናቸው፥ እግዚአብሔር ይራራላቸዋል! ስለሆነም፥ መሪዎቹ የሕዝቡን ፍላጎቶች እንዲያሟሉም ይጠቀምባቸዋል።

7. የኢየሱስ በውኃ ላይ መራመድ (ማር. 6፡45–56)

አንዳንድ ጊዜ ፍርሃት ተፈጥሯዊና ጠቃሚ ምላሽ ነው። በመኪና መንገድ ላይ ተጠንቅቀን እየሄድን ሳለ፥ ጥሩምባው ሲነፋና ፍሬኑ በሚያዝበት ወቅት ሰቅጣጭ ድምፅ ሲሰማ፥ በፍርሃት ከመንገዱ ፈቀቅ እንላለን። በሌሎች ጊዜያት ደግሞ ፍርሃት ያለማመን ምልክት ይሆናል። የክርስቶስ ተከታዮች እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ በእምነት ለመመላለስ ከፈለጉ፥ የስደትንና የችግሮችን ፍርሃት ማስወገድ አለባቸው። ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ በውኃ ላይ ሲራመድ በማየታቸው፥ (አይሁዶች) መናፍስት ከውኃ ውስጥ ወደ ላይ እንደሚወጡ የሚያስረዳ ባሕል ነበራቸው) እና በነፋሳት ላይ ባሳየው ኀይል በመደነቃቸው፥ «ያለ መጠን እጅግ ተገረሙ፤ ስለ እንጀራው አላስተዋሉምና ነገር ግን ልባቸው ደንዝዞ ነበር።» (ማር. 6፡51–52)። ክርስቶስን በበለጠ ስናውቅ፥ እርሱ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እንዳለ ሁልጊዜም ማስታወስ አለብን። እርሱ ከእኛ ጋር ካለ የሚያስፈራን ነገር አይኖርም። ክርስቶስ ፍላጎታችንን ሁሉ ከማሟላቱም በላይ፥ የተፈጥሮንም ኃይል ይቆጣጠራል። ነፋስን መቆጣጠር ከቻለ፥ ማዕበልንም ሊቆጣጠር ይችላል። ማዕበሉን እንደተቆጣጠረ ሁሉ፥ ደቀ መዛሙርቱ የሚጋፈጧቸውን ችግሮችና ስደትም ሊቆጣጠር ይችላል። የሕይወት ማዕበል በሚያጋጥመን ጊዜ የምንፈራ ከሆነ ክርስቶስ ነገሮችን ሁሉ የሚቆጣጠር የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆኑ እምነት የለንም ማለት ነው። እምነት በቃል ወይም በዝማሬ ብቻ የሚገለጽ አይደለምና። ሕይወታችንን በምናምነው እውነት ላይ ተመሥርተን ልንመራ ይገባል። ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ እንደሆነ ካመንን፥ እርሱ ነገሮችን እንደሚቆጣጠር በማወቅ ወደ ሕይወታችን ለሚመጡ ጉዳዮች ሁሉ በእርሱ ልንተማመን ይገባል።

6ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በፍርሃት ስለተያዝክበት ጊዜ ግለጽ። ይህ በክርስቶስ ላይ ስላለህ የእምነት ጥልቀት ምን ያሳያል? ለ) ፍርሃት፥ አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ እንዳይኖር የሚያደርገው እንዴት ነው? ሐ) የፍርሃት መድኃኒቱ ምንድን ነው?

8. ክርስቶስ ሰውን ስለሚያረክስ ነገር አስተማረ (ማር. 7፡1–23)

በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ከቀረቡት ረዣዥም ታሪኮች አንዱ፥ ሰውን ስለሚያረክሱና ስለሚያነጹ ነገሮች የሚያስረዳው ነው። ይህ ቤተ ክርስቲያን ልትረዳው የሚገባት ጠቃሚ እውነት ነው። በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች ይጠይቋቸው ከነበሩት ዐበይት ጥያቄዎች አንዱ፥ «ሃይማኖታዊ ንጽሕናችንን ለማሳየት ልንጠብቃቸው የሚገቡ ትውፊቶች አሉ ወይ?» የሚል ነበር። ለብዙ ምእተ ዓመታት አይሁዶች የተወሰኑ ነገሮችን በማድረግ ውስጣዊ ሕይወትን በንጽሕና መጠበቅ እንደሚቻል ተምረው ነበር። ለምሳሌ፥ ንጽሕናን በተመለከተ አንዱ መንገድ የተወሰኑ የሥጋ ምግቦችን አለመመገብ ወይም ደግሞ እጅን በተወሰነ መንገድ መታጠብ። ይህ ሥርዓት የእግዚአብሔር ፈቃድና ጠቃሚ መሆኑን ሲማሩ የነበሩት አይሁዶች፥ በክርስቶስ ባመኑበት ጊዜ፥ ክርስቲያኖችም ይህንኑ ማድረግ አለባቸው ብለው ያስቡ ነበር። አይሁዶች ብቻ ሳይሆኑ የአሕዛብ ክርስቲያኖችም እነዚህኑ ሥርዓቶች እንዲፈጽሙ ተነግሯቸዋል። ላይ ላዩን ሲታይ የተወሰኑ ምግቦችን

መመገቡ ወይም እጅን መታጠቡ ብዙ ለውጥ ስለማያመጣ፥ ለአሕዛብ የአይሁድን የአኗኗር መንገዶች መከተሉ ከባድ አልነበረም። ነገር ግን በውስጡ አደገኛ የሆነ ትምህርት እንደነበረ ግልጽ ነው። ይህም የተወሰኑ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን በምንፈጽምበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ደስ እንደሚሰኝብን፥ እንዲሁም ለእኛ የተስማማን ነገር ሁሉ ለሁሉም ሰዎች መልካም እንደሆነ አድርገን እንደምንገምት የሚያሳይ ነው። ስለሆነም፥ የኃጢአት ሥር የሚኖርበትን የልባችንን አመለካከት ትተን በሃይማኖታዊ ሥርዓት ላይ እናተኩራለን።

የሃይማኖት መሪዎች፥ ክርስቶስና ደቀ መዛሙርቱ በእግዚአብሔር ፊት ሰዎችን ንጹሕ ያደርጋሉ የሚሏቸውን አንዳንድ ሥርዓቶች አለመከተላቸውን በመግለጽ በወቀሱዋቸው ጊዜ፥ ክርስቶስ ሁለት ጠቃሚ ነገሮችን አስተማራቸው። <u>በመጀመሪያ</u>፥ በውጫዊ ልማዶችና ሥርዓቶች ላይ በማተኮር፥ ይበልጥ ጠቃሚ የሆነውን ነገር ላለማየት የመታወር አደጋ መኖሩን ገለጸ። ፈሪሳውያን እግዚአብሔርን በአፋቸው እያከበሩ፥ በሕግጋት ላይ ቢያተኩሩም፥ ልባቸው ወደ እግዚአብሔር ስለመቅረቡ ግድ የላቸውም ነበር። ሕግጋቱን በቀላሉ ወደሚፈጽሙበት አቅጣጫ ጠምዝዘዋቸው ነበር። ይህም እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ እየኖርን ነው ብለው እንዲኩራሩ አደረጋቸው። ብዙውን ጊዜ ግን እግዚአብሔር በማይፈልገው መንገድ ይመላለሱ ነበር። ስለዚህ አመለካከታቸው ከእግዚአብሔር ትእዛዛት «መንፈስ» የራቀ ነበር።

<u>ሁለተኛ</u>፥ ጌታችን የትኛውም ሰው ሠራሽ ውጫዊ ተግባር አንድን ሰው ንጹሕ ወይም ርኩስ ሊያደርግ እንደማይችል አስተማረ። መንፈሳዊ ንጽሕና ወይም ርኩሰት የሚመጣው ከልብ ነው። የሰው አመለካከቶች፥ አሳቦችና ፍላጎቶች የሚኖሩት በልብ ውስጥ ነው። ልብ የመልካም ነገሮች (እግዚአብሔርንና ባልንጀራን መውደድ) እና የመጥፎ ነገሮች (ጥላቻ፥ ምኞት፥ ቁጣ) ምንጭ ነው። የክርስቶስ ተከታዮች በእነዚህ ነገሮች ላይ ማተኮር አለባቸው። ተግባራችን መልካምና እግዚአብሔርን የሚያስከብር ይሆን ዘንድ ከርኩስ ነገሮች መራቅ አለብን። እውነተኛ ሃይማኖት ሰዎች የሚያዩት ሳይሆን፥ በአማኙ ልብ ውስጥ ያለው ነው።

7ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ክርስቲያኖች ክርስቲያንነታቸውን የሚያሳዩባቸው፥ ጠቃሚና መልካም ተደርገው የሚወሰዱትን አንዳንድ ክርስቲያናዊ ልምምዶች ለምሳሌ፥ ዓይንን ጨፍኖ መጸለይ፥ በጌጣጌጥ አለመዋብ የመሰሉትን ዘርዝር። ለ) ክርስቶስ ባስተማረው መሠረት፥ ስለ እነዚህ ነገሮች ምን ዓይነት ግንዛቤ ሊኖርህ ይገባል?

ክርስቶስ ፈሪሳውያን ወይም ደቀ መዛሙርት እነዚህን ሰው ሠራሽ ልምምዶች እንዲያቆሙ አልተናገረም። ነገር ግን ስለ ደንቦች ትክክለኛ ጭብጥ ሊኖራቸው እንደሚገባ አስጠንቅቋቸዋል። ከጊዜ በኋላ ሁላችንም ትክክል ናቸው የምንላቸውን ውጫዊ ልምምዶች እናዳብራለን። ለምሳሌ፥ አልኮል አለመጠጣት ጥሩ ክርስቲያን መሆናችንን ያሳያል ብለን እናስባለን። (<u>ማስታወሻ</u>፡– በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ኃጢአት የተጠቀሰው መስከር ብቻ ነው)። ዓይኖቻችንን ጨፍነንና እጆቻችንን አጣጥፈን መጸለይ እንዳለብን እናስባለን፤ ስንዘምርም ዓይኖቻችንን ጨፍነን ራሳችንን ወደ

ሰማይ እናቀናለን። በዕልልታ ሃሌ ሉያ እያልን እንጮኻለን። እነዚህ ድርጊቶች ስሕተት ባይሆኑም፥ እንድናደርጋቸው እግዚአብሔር ያዘዘን አይደሉም። መንፈሳዊ ሕይወታችን ምን እንደሚመስል እነዚህ ነገሮች አያሳዩም። ጫማ ሳያወልቁም ሆነ፥ አውልቆ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማምለክ ይቻላል። ዓይንን ጨፍኖ ወይም ሳይጨፍኑ መጸለይ ይቻላል። በዝማሬ ጊዜ ዓይንን መጨፈን ወይም አለመጨፈን እጅን ማንሳት ወይም ማውረድ፥ ማጨብጨብ ወይም አለማጨብጨብ ይቻላል። በአምልኮ ውስጥ እነዚህ ውጫዊ ተግባራት ትክክል ወይም ስሕተት የሚባሉ አይደሉም። ዋናው የልባችን ሁኔታ ነው።

9. ታላቅ እምነት ያላት አሕዛብ (ማር. 7፡24–30)

ክርስቶስ ጎሰኛ ነበር? የገዛ ወገኖቹ ለነበሩት ለአይሁዶች ብቻ ይጨነቅ ነበር? ወይስ ለአሕዛብም ያስብ ነበር? ለሮማውያን አንባቢዎች እነዚህ ጥያቄዎች አስፈላጊዎች ነበሩ። ስለሆነም፥ ማርቆስ ክርስቶስ ወደ ሶርያና ፊንቄ (ካርታውን ከመጽሐፉ መጨረሻ ተመልከት)፥ ተጉዞ አሕዛብ የነበረች ሴት እንዳገኘ አብራርቷል። ክርስቶስ በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት አይሁዶችን በመጀመሪያ ለማገልገል መጠራቱን ተናግሯል። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር ልጆች የነበሩትን አይሁዶች መግቦ ገና አልረካም ነበር። እግዚአብሔር፥ ክርስቶስና ደቀ መዛሙርቱ ወደ አሕዛብ እንዲሄዱ ገና አላዘዛቸውም ነበር። ይህን ማለት ግን ክርስቶስ ስለ አሕዛቡ ሕዝብ አያስብም ማለት አይደለም። ሴቲቱ ክርስቶስ አጋንንትን ለማውጣት እንደሚችል በመግለጽ እምነቷን ስታሳይና እግዚአብሔር በረከቶቹን ለአሕዛብ የማዳረስ ባሕርይ እንዳለው ስታመለክት፥ ክርስቶስ ልጁን ፈወሰላት። የሚገርመው የእግዚአብሔር ልጆች የነበሩት አይሁዶች፥ «ውሾች» ናቸው ከሚሏቸው ከአሕዛብ ያነሰ እምነት ነበራቸው።

10. ኢየሱስ በአጋንንት የተያዘ ደንቆሮና ዲዳ ሰው ፈወሰ

(ማር. 7፡31–37)

የክርስቶስ ፈውስ በአንድ መንገድ ብቻ አልነበረም። አንዳንድ ጊዜ በቃሉ በመናገር፥ ሌላ ጊዜ በእጁ በመዳሰስ ሰዎችን ይፈውስ ነበር። በዚህ ስፍራ ክርስቶስ ሰውዬውን እንትፍ ብሎ በመዳሰስ ፈውሶታል። ይህም የደነቆሩትን ጆሮዎች ነካ፥ መናገር በተሳነው ምላስ ላይ እንትፍ አለ፥ ከዚያም በጸሎት ወደ ሰማይ ተመለከተ። እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች ለጸሎት መልስ ስለሚሰጥ ሁልጊዜም አንድ ዓይነት ስልት ላይከተል ይችላል። ምሥጢሩና ጎይሉ የሚመጣው ከክርስቶስ ማንነት ነው። ሰዎች መንፈሳዊ ውጤት የሚያመጡት በተወሰነ መንገድ በመሄዳቸው፥ ወይም በመስበካቸው እንደሆነ በማሰብ፥ እንዳንሳሳት መጠንቀቅ አለብን። ውጤቶችን የሚያመጣው የአሠራር መንገድ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ራሱ የሚፈጽመው ተግባር ስለሆነ፥ እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ከእውነት የራቀ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር አህያን ለማናገር ከቻለ (ዘኁል. 22፡28)፥ ማንንም ሰው ሊያናግር ወይም የፈለገውን መንገድ ለክብሩ ሊጠቀም ይችላል።

ሰዎችን ያስደነቀው የክርስቶስ መፈወስ ብቻ ሳይሆን፥ ሁሉንም በሚገባ መፈጸሙ ነበር። ነገሮችን የምናከናውንበት መንገድ ነገሮችን ከማከናወን እኩል አስፈላጊ ነው። ያለ መልካም ዝግጅት የይድረስ ይድረስ ተግባር ብናከናውን ድርጊቱ ግምት ላይ ይጥለናል። ይህን ብናደርግ ለእግዚአብሔር ክብር ሳናስብ የራሳችንን ፍላጎት የምንፈጽም መሆናችንን ያሳያል። ዓለምን የፈጠረውና ሁሉም «መልካም ነው» ያለው እግዚአብሔር፥ ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ እንድናከናውን ይፈልጋል። ከሥራ ላለመባረር፥ በትምህርት ቤት ከከፍል ወደ ክፍል ለማለፍ ወይም መንፈሳዊ ለመምሰል ላይ ላዩን ከመጣር ይልቅ፥ ፍሬ ያለው ሥራ ከልባችን ለመሥራት መትጋት አለብን።

8ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በግማሽ ልብ የተሠሩ ነገሮች በከፍተኛ ጥንቃቄ ከተሠሩት እንዴት ይነጻጸራሉ? ይህ ምን ልዩነት ያስከትላል? ለ) ሥራችን ባሕርያችንንና ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት የሚያሳየው እንዴት ነው? ሐ) ይህ ትምህርት የማስተማርንና የስብከት አገልግሎታችንን እንዴት ሊለውጠው ይገባል?

ሁለተኛ ቀን ማርቆስ 8፡1–11፡26

9ኛ ጥያቄ፡– ማር. 8፡1–11፡26 አንብብ። ሀ) ከዚህ ክፍል ስለ ክርስቶስ ምን እንማራለን? ለ) ይህ ክርስቶስን ስለ መከተል ምን ያስተምረናል?

1. ኢየሱስ አራት ሺህ ሕዝብን መገበ (ማር. 8፡1–21)

ክርስቶስ ምንም ያህል ሥራ ቢበዛበትም ስለ ሰዎች ጥቅም የሚያስብ ሲሆን፥ ጉዳታቸው ልቡን ይሰማውና ይራራላቸው ነበር። በዚያን ጊዜ ለሰዎች መጎዳት የራራው ክርስቶስ፥ ዛሬም የሚያስፈልገንን ሁሉ በሚመለከትበት ጊዜ ይራራልናል።

ክርስቶስ አሁን አራት ሺህ ሕዝብ ለመመገብ ያነሣሣውን የርኅራኄ ምክንያት ቀደም ሲል አምስት ሺህ ሕዝብ በመገበበት ወቅት፥ ለደቀ መዛሙርቱ አስተምሮ የነበረውን ትምህርት አጠናክሯል። በዚህም ክርስቶስ ፍላጎታቸውን ሁሉ የሚያሟላ አምላክ መሆኑን አሳይቷል።

ፈሪሳውያን እንዲህ ያለ ታላቅ ተአምራት ቢመለከቱም እንኳ፥ በክርስቶስ ለማመን ፈቃደኞች አልነበሩም። የአንድ ግለሰብ ልብ ከደነደነና በክርስቶስ ላለማመን ከወሰነ፥ ምንም ዓይነት ተአምራት ቢመለከት ሊያምን አይችልም። እግዚአብሔር ኀይሉን ለማሳየት በተአምራት ሊጠቀም ቢችልም፥ ሰዎች ሁልጊዜ በተአምራት ላይ ካተኮሩ፥ ይህ ፍላጎታቸው የእምነት እጥረት እንዳለባቸው ያሳያል። ፈሪሳውያን ክርስቶስ መሢሕነቱን ለማረጋገጥ ከዚያ የበለጡ ተአምራት እንዲሠራ ጠይቀውታል። ክርስቶስ ግን ተአምራት የማያምን ትውልድ ምልክቶች መሆናቸውን በመግለጽ፥ ለማመን ለማይፈልጉ ሰዎች ታምራትን እንደማያደርግላቸው ገልጾአል።

ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ ራስን የማጽደቅ አመለካከት እንዳይይዙና ለማመን ተጨማሪ ተአምራትን እንዳይሹ አስጠንቅቋቸዋል። ራስን የማጽደቅ አመለካከት እንደ እርሾ መንፈሳዊነታቸውን በማጥፋት ወደ ሌሎችም ይዛመት ነበር።

12ቱ ደቀ መዛሙርት እንደ ብዙዎቻችን ከመንፈሳዊ እውነት ይልቅ በምድራዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮራቸው፥ የክርስቶስን ትምህርት በተሳሳተ መንገድ ተረጎሙ። የሚያስቡት ክርስቶስ ስለ ፈሪሳውያን ባስተማረው ጉዳይ ላይ ሳይሆን፥ ስለ ምግብ ነበር። ይህም ክርስቶስ ፍላጎታቸውን ሊያሟላ እንደሚችል አለማመናቸውን ያሳያል።

2. ኢየሱስ ዓይነ ስውሩን ፈወሰ (ማር. 8፡22–26)

ይህ ተአምር በሁለት ደረጃዎች የተከናወነ በመሆኑ፥ በክርስቶስ አገልግሎት ውስጥ ለየት ያለ ነበር። ብዙውን ጊዜ የክርስቶስ ተአምራት በአንድ ጊዜ የተሳካ ውጤቶችን የሚያስገኙ ነበሩ። በዚህ ጊዜ ግን ክርስቶስ መጀመሪያ በታወሩት በሰውዬው ዓይኖች ላይ ምራቁን ቀባ። የግለሰቡ ዓይኖች በከፊል ስለ ተፈወሱለት፥ ሰዎች እንደ ዛፍ ሲመላለሱ አየ። ነገር ግን ክርስቶስ እንደገና ሲዳስሰው ዓይነ ስውር የነበረው ግለሰብ አጥርቶ ለማየት ቻለ።

ይህ ምንን ያሳያል? ይህ አንዳንድ ጊዜ ተአምራት በከፊል ብቻ ውጤታማ እንደሚሆኑ ያሳያል? ዛሬ የመፈወስ ጎይል እንዳላቸው የሚያስቡ አንዳንድ ሰዎች እንደዚያ ይላሉ። ነገር ግን በዚህ ግንዛቤና በክርስቶስ ፈውስ መካከል አንዳንድ ዐበይት ልዩነቶች አሉ። ክርስቶስ አንድም ሰው በከፊል ፈውሶ ብቻ አላሰናበተም። የፈውሱን እርግጠኝነት ተጠራጥሮ እንደገና የተሟላ ፈውስ የሰጠው ራሱ ክርስቶስ ነበር። ማንም ሰው ከክርስቶስ ዘንድ ከፊል ፈውስ አግኝቶ የሄደ የለም። ዛሬም እግዚአብሔር አንድን ሰው በተአምራዊ መንገድ ከፈወሰው፥ ከፊል ሳይሆን ሙሉ ፈውስ ነው።

ክርስቶስ ይህንን ባለ ሁለት ደረጃ ፈውስ ያካሄደው አንዳች መንፈሳዊ እውነት ለማስተማር ይሆን? የአንድን ሰው መንፈሳዊ ዓይኖች መክፈት ማለትም፥ መንፈሳዊ እውነትን መረዳት ብዙውን ጊዜ የሂደት አካል ነው። በአንድ ጊዜ መንፈሳዊ እውነቶችን ሙሉ በሙሉ ሊረዳ የሚችል ሰው የለም። ደቀ መዛሙርቱም አልተገነዘቡም ነበር። ለዚህም ነበር ስለ ክርስቶስ አገልግሎት ብዙ ነገሮችን ከትንሣኤው በፊት ለመረዳት ያልቻሉት። ጳውሎስም ሳይቀር ነገሮችን በድንግዝግዝ እንደሚያይ ለማመን ተገድዷል (1ኛ ቆሮ. 13፡12)። ይህን ስላለ ግን ተስፋ እንቆርጣለን ማለት አይደለም። ይህ ትሑት እንድንሆን ያስተምረናል። በተጨማሪም፥ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ማደጋችንን እንድንቀጥል ያስተምረናል።

3. ጴጥሮስ የኢየሱስን መሢሕነት መሰከረ (ማር. 8፡27–30)

የማርቆስ ወንጌል የተመሠረተው በዚህ አጭር ምንባብ ላይ ነው። ማርቆስ ክርስቶስ መሢሑ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በብዙ የተለያዩ መንገዶች አሳይቷል። በመጨረሻም፥ ደቀ መዛሙርቱ ስለ ግል እምነታቸው የተጠየቁበት ጊዜ ደረሰ። ብዙውን ጊዜ ሌሎች ሰዎች ወይም ወላጆቻችን የሚያምኑትን ሃይማኖት መከተሉ ቀላል ነው። ነገር ግን ጠቅላላው ማንነታችን በእምነታችን ሊለወጥ በሚችልበት መልኩ በግላችን እውነትን ማመን አለብን። ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን በጠየቀበት ሰዓት፥ መጀመሪያ ስለ ሌሎች ከጠየቀ በኋላ፥ የራሳቸውን እምነት እንዲገልጹት አድርጓል።

4. ኢየሱስ ስለ መጭው ሞቱና የደቀ መዝሙርነት መንገድ አስተማረ (ማር. 8፡31–38)።

ጴጥሮስና ደቀ መዛሙርቱ የክርስቶስን መሢሕነት ከተገነዘቡ በኋላ፥ ጠቅላላው የኢየሱስ አገልግሎትና የማርቆስ ወንጌል ትኩረት ተለውጧል። በመጀመሪያ፥ ምን ዓይነት መሢሕ እንደሆነ የነበራቸውን የተሳሳተ ግንዛቤ ማስተካከል ነበረበት። እርሱ መከራ የሚቀበልና የሚሞት እንጂ፥ ወረራ የሚያካሂድና የሚገዛ ንጉሥ አልነበረም። ሁለተኛ፥ ለደቀ መዛሙርቱ እርሱን መከተል መስቀልን እንደሚያስከትል ነግሯቸዋል። ይህም ክርስቶስን በሚከተሉበት ጊዜ በመንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወታቸው እንደሚሞቱ የሚያመለክት ነበር።

ከዚህ ጊዜ አንሥቶ፥ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ስለሚመጣው ሞቱ ይናገር ጀመር። መጀመሪያ ይህ ደቀ መዛሙርቱን ስላስደነገጣቸው፥ ጴጥሮስ እንዲህ ዓይነት የመሢሕነት እርምጃ አይድረስብህ አለው። ክርስቶስ ሰይጣን በጴጥሮስ ቃላት ተጠቅሞ ከመስቀል ሊመልሰው የመፈለጉን ፈተና ተገነዘበ። ክርስቶስ ይህን ሁኔታ ስለ ደቀ መዝሙርነትም ለማስተማር ተጠቅሞበታል። ክርስቶስ የሚሞትበትን መስቀል ተሸክሞ ወደ ጎልጎታ በመሄድ ለሰው ልጆች ደኅንነትን አስገኝቷል። ደቀ መዛሙርቱም እያንዳንዳቸው የሚሸከሙት መስቀል ነበራቸው። መስቀላችን መንፈሳዊ ነው። ራሳችን በሕይወታችን ላይ ላለን ቁጥጥር፥ ለዓለማዊ ብልጽግና መሞት አለብን። የደቀ መዝሙርነት መንገድ ማለት ሥጋዊ ሕይወታችንን ጨምሮ በዚህ ዓለም ጠቃሚዎች ናቸው የተባሉትን ነገሮች ሁሉ ማጣትን ያካትታል። ከዚያ በኋላ ለሰው ከሁሉም የበለጠ ዋጋ ያለውን የዘላለምን ሕይወት እናገኛለን። ነገር ግን ሕይወታችንን ብንታደግና በዓለም ጠቃሚዎች የሆኑትን ነገሮች ብንከተል፥ የዘላለም ሕይወታችንን እናጣለን። በስደት ጊዜ፥ በክርስቶስ አፍረን እርሱን ከመከተልና ቃሉን ከማስተማር ብንቆጠብ፥ ዘላለማዊ ጉዳት ይደርስብናል። በዘላለሙ መንግሥት፥ ክርስቶስ በአባቱ ፊት አያከብረንም።

> 10ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ሰዎች ጠቃሚዎች እንደሆኑ የሚያስቧቸውንና፥ ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ ለመተው የሚቸገሩባቸውን ነገሮች ዘርዝር። ለ) ክርስቲያኖች በክርስቶስና በቃሉ ማፈራቸውን የሚያሳዩባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? ሐ) የመስቀሉን መንገድ መከተል እንዴት እንደ ለወጠህ ግለጽ።

ከዚህ በኋላ፥ ክርስቶስ በሞቱ ላይ ስላተኮረ ታሪኩ ተለውጧል። እርሱም ቀስ በቀስ ወደሚሞትባት የኢየሩሳሌም ከተማ ተጓዘ። ለደቀ መዛሙርቱም ስለ ሞቱና ትንሣኤው በተደጋጋሚ ይነግራቸው ጀመር።

5. ኢየሱስ ሰማያዊ ክብሩን ገለጸ (ማር. 9፡1–13)።

ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ አንዳንዶቹ ከመሞታቸው በፊት ክብሩን እንደሚያዩ ከተናገረ በኋላ፥ ጴጥሮስን፥ ዮሐንስንና ያዕቆብን ይዞ ወደ ተራራ ወጣ። በዚያም መለኮታዊ ክብሩን ገለጸ። በዚያም ሕግን የወከለው ሙሴና ነቢያትን የወከለው ኤልያስ ቀርበው ከኢየሱስ ጋር ተነጋገሩ። ለሁለተኛ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር የሚወደው ልዩ ልጁ እንደሆነ ሰሙ። ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ምን ያህል እንደ ተደሰቱ አስቡ። ወዲያው ግን

ኢየሱስ አምላክ ቢሆንም እንኳ፥ መከራን እንደሚቀበልና በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነትን እንደሚያጣ በመግለጽ ደቀ መዛሙርቱን አስደነገጠ። ያዩትን ሁሉ ለሌሎች አለመናገሩ ሳይከብዳቸው አልቀረም።

6. ኢየሱስ ከአንድ ልጅ አጋንንትን አስወጣ (ማር. 9፡14–32)።

ደቀ መዛሙርቱ ከተራራው ሲወርዱም እንደገና ደነገጡ። ከልጁ አጋንንት ለማውጣት ባለመቻላቸው ወደ ተራራው ያልወጡት ደቀ መዛሙርት፥ ተጨንቀውና አፍረው ቆመው ነበር። ቀደም ሲል ክርስቶስ ለአገልግሎት በላካቸው ጊዜ ያከናወኑት አጋንንትን የማስወጣት ተግባር፥ ለምን እንደ ተሳናቸው ሊገባቸው አልቻለም ነበር።

ክርስቶስ ይህንን ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ እምነት ለማስተማር ተጠቀመበት። <u>በመጀመሪያ</u>፥ ለልጁ አባት፥ ለሚያምን ሁሉም እንደሚቻል ገለጸለት (ማር. 9፡23)። ስለ እምነት ልናስታውሳቸው የሚገቡን ሁለት ነገሮች አሉ። ታላላቅ ነገሮችን የሚሠራው ራሱ እምነታችን ሳይሆን፥ የምናምንበት አካል ነው። ስለሆነም፥ በጣዖታት ላይ ከፍተኛ እምነት ያለው ሰው ታላላቅ ነገሮችን ሊያሳካ አይችልም። ነገር ግን በታላቁ አምላክ ላይ አነስተኛ እምነት ያለው ሰው እግዚአብሔር ታላላቅ ተአምራትን ሲሠራ ሊመለከት ይችላል። በተገላቢጦሹ እምነት በማይኖርበት ጊዜ ወይም ሰዎች ለማመን ሳይፈልጉ ሲቀሩ፥ እግዚአብሔር ተአምራትን ለመሥራት አለመቻሉ ሳይሆን፥ ነገር ግን ሰዎች እርሱን ወይም ችሎታውን በሚጠራጠሩበት ጊዜ ለመሥራት አለመምረጡ ነው።

<u>ሁለተኛ</u>፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ሥራዎችን ለማከናወን በእምነት መጽናት አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ እንዳለ ተናግሯል። ደቀ መዛሙርቱን ያጋጠማቸው ችግር ክርስቶስ በተአምር ለመፈወስ ኃይልን ማጣቱ አልነበረም። ክርስቶስ በአንድ የትእዛዝ ቃል ነበር አጋንንቱን ሁሉ ያስወጣው። ተግቶ የማይሠራ ሰው ጠንካራ ጡንቻ ሊኖረው አይችልም። በተመሳሳይ ሁኔታ በጸሎት ጽኑ ትግል የማያደርግና በጾም በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ መሆኑን የማያሳይ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጡንቻ ሊኖረው አይችልም። ስለሆነም፥ እግዚአብሔር ቀደም ሲል እኛን ለመርዳት ቢሠራም እንኳ፥ ጥያቄዎቻችንን በፍጥነት የማይመልስባቸው ጊዜያት አሉ። እምነታችንን የሚፈታተን ሁኔታ ሁሉ አዲስ ሁኔታ ነው። በቀድሞው ስኬት ወይም ብርታት ላይ ሳንመሠረት፥ እንደገና በእግዚአብሔር ላይ ጥገኝነታችንን ማኖር አለብን።

> 11ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ብዙውን ጊዜ አንድ ነገር ከተሳካልን በኋላ፥ በእግዚአብሔር ላይ መደገፋችንን የምናጸርጠው እንዴት ነው? ለ) እግዚአብሔር ለጸሎትህ ፈጣን ምላሽ ባለመስጠቱ ምክንያት መንፈሳዊ ብርታትህ የጨመረባቸውን መንገዶች የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ስጥ።

ማርቆስ፥ ክርስቶስ ለሦስተኛ ጊዜ ስለ መሞቱ ሞቱ፥ ቀብሩና ትንሣኤው መግለጹን ዘግቧል። ክርስቶስ የሞቱ እየተቃረበ መሆኑን ያውቅ ስለነበረ ሁኔታው አላሸበረውም።

7. ኢየሱስ በመንግሥቱ ውስጥ አመራር ምን እንደሚመስል አስተማረ (ማር. 9፡33–50)

የተሳሳቱ አመለካከቶችን ማስወገዱ ቀላል አይደለም። እጅግ ከተሳሳቱ አመለካከቶች አንዱ ሥልጣንና የመሪነት ስፍራ ለማግኘት የሚደረግ ጥረት ነው። በዓለም ሁሉ ያለው ባሕል በራስ ጥቅም ላይ ያተኩራል። ሰዎች መሪ ከሚሆኑባቸው ዋንኛ ምክንያቶች አንዱ ሥልጣን፥ ሀብትና ጎይል ለማግኘት ነው። ይህ አመለካከት ካልተወገደ በስተቀር ቤተ ክርስቲያንን እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ መምራት አይቻልም። ይህ የጎይልና የክብር ፍላጎት ደቀ መዛሙርቱን ይፈታተናቸው ስለ ነበር፥ ክርስቶስ የመንግሥቱ አመራር በአምስት መንገዶች እንደሚለይ አስተምሯል።

ሀ. በክርስቶስ መንግሥት አመራር ከዓለም የተለየ ነው። ታላቅነት የሚለካው አንድ መሪ ራሱን ዝቅ አድርጎ ከራስ ወዳድነት በጠራ መንፈስ ሌሎችን ለማገልገል በመቻሉ ነው። እንደ ትልልቅ ሰዎች በችሎታችንና በታላቅነታችን ከመመካት ይልቅ፥ እንደ ልጆች በእግዚአብሔር አብ ላይ ጥገኞች ልንሆን ይገባል።

ለ. በክርስቶስ መንግሥት አመራር የሚያከብረው ታላላቆች ናቸው የተባሉትን ሳይሆን፥ ዝቅተኛ ግምት የሚሰጣቸውን ሰዎች ነው። ጠቃሚዎች ናቸው የምንላቸውን ሰዎች (ሀብታሞች፥ ነጋዴዎች፥ ምሁራን) እየወደድን፥ ጠቃሚዎች አይደሉም የምንላቸውን ሰዎች (ልጆች፥ ሴቶች፥ ድሆች፥ መሃይማንን) እንንቃለን። በክርስቶስ መንግሥት ለዓለም የማይጠቅሙ የሚመስሉ ሰዎች አስፈላጊዎች ናቸው።

ሐ. የእግዚአብሔር መሪዎች ሌሎች ስኬታማ ሲሆኑና እግዚአብሔር ባልተጠበቁ መንገዶች ሲሠራ በሚመለከቱበት ጊዜ አይቀኑም። አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ሌላ አማኝ ክርስቶስን ሳያስፈቅድ አጋንንት ሲያወጣ በማየታቸው ቀንተው ክርስቶስ እንዲከለክለው ነገሩት። ክርስቶስ ግን የአመራር ሚና ሰዎችን ማበረታታት እንጂ መቆጣጠር እንዳልሆነ አስተማራቸው። ለእግዚአብሔር ክብርን የሚያመጣ ማንኛውም ነገር በሚከሰትበት ጊዜ መደሰት አለብን። ይህ የግድ «በእኛ» መሪዎች ወይም በምንጠብቃቸው ሰዎች መከናወን የለበትም። ምክንያቱም ለክርስቶስ ክብር የሚሠራ ሰው፥ ወዲያውኑ ተመልሶ የክርስቶስ ጠላት ሊሆን ስለማይችል ነው።

መ. አገልግሎት የሚለካው በምናከናውናቸው ተግባራት ታላቅነት ሳይሆን፥ በታማኝነትና በጥሩ አመለካከት በማገልገላችን ነው። የግድ ታላላቅ ሰባኪያን ወይም አስተማሪዎች መሆን የለብንም። የባሪያን በሚመስል አመለካከት የተሰጠ አንድ ኩባያ ቀዝቃዛ ውኃ ዋጋ አለው።

ሠ. መሪዎችና በሌሎች ላይ ኃላፊነት ያላቸው ሰዎች፥ (ለምሳሌ፥ ወላጆች) በተግባራቸውና በአመለካከታቸው ትንንሽ ልጆችንና የቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ወደ ኀጢአት እንዳይገፉ መጠንቀቅ አለባቸው። ክርስቶስ ሌሎችን በኀጢአት ለማሰናከል የተጋነነ ቋንቋ በመጠቀም አንድን ሰው ከማሰናከል ይልቅ፥ የግል አካላዊ ጉዳትን መቀበል እንደሚሻል

ተናግሯል። ሌሎችን የሚያሰናክሉ ሰዎች እውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ባለመሆናቸው፥ ከፍተኛ ቅጣት ይደርስባቸዋል። ተግባሮቻችንና አመለካከቶቻችን እንደ ብርሃን እያንጸባረቁ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ መምራት ይኖርባቸዋል። መንፈሳዊ ባሕርይን በመላበስ (በነፍሳችሁ ጨው ይኑርባችሁ)፥ እርስ በርሳችን በሰላም እንኖራለን።

12ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ክርስቶስ ስለ መሪነት ያስተማረውን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካለው ሁኔታ ጋር አነጻጽር። ለ) አመራርን ይበልጥ ክርስቶስ ባየበት ዓይን ለመመልከት፥ ከተግባራችንና ከአመለካከታችን ሊለወጡ የሚገባቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

8. ኢየሱስ ስለ ጋብቻና ፍች አስተማረ (ማር. 10፡1–12)።

ፈሪሳውያን ክርስቶስን ለመፈተን በመፈለግ ስለ ፍች ጠየቁት። በዚህ ጊዜ እርሱም በፍች ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን አመለካከት ገልጾላቸዋል። ፍች ሁልጊዜም የኀጢአትና በእግዚአብሔር ዓላማ ላይ የማመፅ ምልክት ነው። እግዚአብሔር ጋብቻን የወጠነው ባልና ሚስት በጣም በመቀራረብ በአሳብና በተግባር እንዲጣመሩ ነው። ፍችን ማበረታታት በእግዚአብሔር ፍላጎት ላይ ማመፅ ነው። ፍች የሚፈቀድበት ብቸኛው ጊዜ ግንኙነቱ በዝሙት የተበላሸ እንደሆነ ብቻ ነበር። ከተፋታ ሰው ጋር መጋባቱም በዝሙት ከመኖር እኩል ነው።

በምዕራቡ ዓለም፥ ክርስቲያኖች በእነዚህ ጥብቅ የጋብቻ ትእዛዝ ላይ ዓምፀዋል። ከዚህም የተነሣ፥ ፍች የዓለማውያንን ያህል በዝቷል። ይህ የክርስቶስ ትምህርት ሁሉንም ሁኔታዎች ላያካትት ይችላል። (ለምሳሌ፥ አካላዊ ጥቃት በሚኖርበት ጊዜ ምን ማድረግ ይገባል?) (ለተጨማሪ የፍች ሁኔታ 1ኛ ቆሮ.7፡15ን ይመልከቱ።) ነገር ግን ይህን ትምህርት በከፍተኛ አክብሮት መቀበል አለብን። ችግሮቹ ምንም ያህል ከባድ ቢሆኑም፥ በመንፈስ ቅዱስ እገዛ ክርስቲያኖች ሁሉንም አሸንፈው በአንድነት ሊኖሩ ይችላሉ።

ነገር ግን እግዚአብሔር ለጋብቻ የወጠነውን ፍጹማዊ ዕቅድ የምናፈርስበት ሌላ መንገድ አለ። ወንጌላውያንን ጨምሮ ብዙ ሰዎች ከትዳር ጓደኞቻቸው ተለይተው ለወራት ይቀመጣሉ። ብዙውን ጊዜ ባልና ሚስት በብዙ ኪሎ ሜትሮች ተራርቀው በተለያዩ ከተሞች ውስጥ ይቀመጣሉ። በሥስት ወር ወይም በዓመት አንድ ጊዜ ይገናኛሉ። ይሄ እግዚአብሔር ያጣመረውን የምንለይበት ሌላው መንገድ አይሆንም? የእግዚአብሔር ፍላጎት የባልና ሚስት አብሮ መኖር ከሆነ፥ ከዚያ ውጭ የሆነው ሁሉ ኀጢአት አይደለምን? ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት በምናደርገው ጥረት ቤተሰባችንን መለያየቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ እርግጠኞች ነን? ወይስ የገንዘብ ፍቅር እግዚአብሔርን ወደማናስከብርበት አቅጣጫ እየመራን ይሆን? የቤተሰብና የአካባቢ ሁኔታ ወንጌላውያንን ከሚስቶቻቸው ቢለያቸው፥ ቤተሰባቸውን ክርስቶስን ከመታዘዝ አላስበለጡም ወይ? ቤተሰብ የቤተ ክርስቲያን እጅግ ጠቃሚ ክፍል ከሆነ፥ አነስተኛ ገቢና ተጨማሪ ችግሮች ቢገጥሙንም እንኳ ቤተሰብን ልንንከባከብ ይገባል።

13ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ሰዎች በባልና ሚስት መካከል ስለሚኖረው ግንኙነትና ስለ ጋብቻ ያላቸው የተሳሳቱ አመለካከቶች፥ እግዚአብሔር ለአእምሮ፥ ለልብና ለዓላማ አንድነት ያለውን ፍላጎት ሲያበላሹ የተመለከትህበትን ሁኔታ በምሳሌነት ጥቀስ። ለ) ብዙ ክርስቲያኖች በሥራ ምክንያት ከትዳራቸው ሲርቁ የተመለከትህበትን ሁኔታ አብራራ። ይህ በቤተ ክርስቲያንና በቤተሰብ ላይ ያስከተላቸው አሉታዊ ውጤቶች ምንድን ናቸው?

9. የእግዚአብሔር መንግሥት የተገነባችው እንደ ልጆች ባሉ ሰዎች ነው (ማር. 10፡13–16)።

ክርስቶስ ብዙ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ባይቆጣም፥ አንዳንድ ጊዜ ግን ይህንኑ ሲያደርግ እንመለከታለን። ከእነዚህ ጥቂት ጊዜያት አንዱ፥ ልጆች አስቸጋሪዎች እንጂ በእግዚአብሔር ዓይኖች ብርቅ መሆናቸውን ያላጤኑት ደቀ መዛሙርት፥ ወደ ክርስቶስ እንዳይቀርቡ በተከላከሉበት ጊዜ የሰነዘረው ቁጣ ነበር። ክርስቶስ ግን ለደቀ መዛሙርቱ ልጆች የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት አርአያዎች እንደሆኑ ነገራቸው። ልጆች በወላጆቻቸው ላይ በፍጹም ልባቸው እንደሚተማመኑ ሁሉ፥ የእግዚአብሔርም ልጆች በፍጹም ልባቸው ሊተማመኑበት ይገባል።

10. ደቀ መዝሙርነት ማለት ኢየሱስን ከምንም ነገር በላይ መውደድ ማለት ነው (ማር. 10፡17–31)።

ክርስቶስ ግብረገባዊ ሕይወት ይመራ ለነበረው ሀብታም ወጣት ሹም፥ ደቀ መዝሙሩ ለመሆን ከፈለገ ገንዘቡን ሁሉ ለድሆች መስጠት እንዳለበት ሲናገር፥ ሹሙ ወደ ኋላ ተመለሰ። ለዓለም ነገሮች፥ በተለይም ለገንዘብ የነበረው ፍቅር ሁሉንም ነገር ትቶ ክርስቶስን የበለጠ መውደዱን እንዳያሳይ አገደው።

ደኅንነትና ክርስቶስን መከተል ቀላል አይደለም። እሱድ ቀን እጅን አንሥቶ ክርስቶስን እከተላለሁ ማለቱ ብቻ አይበቃም። ክርስቶስን መከተል ሕይወትን መስጠት ነው። ክርስቶስ በሕይወታችን ቀዳሚውን ስፍራ ሊይዝና ለክርስቶስ ያለንን ፍቅር የሚያደናቅፍ ነገር ሁሉ ሊወገድ ይገባል። ለዚህ ሰው መሰናክል የሆነው ገንዘብ ሲሆን፥ ለሌሎች ደግሞ ትምህርት ወይም የቤተሰብ ፍቅር ሊሆን ይችላል። ክርስቶስ ይህ ሰዎች በተፈጥሯዊ ብርታታቸው የሚያደርጉት ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ጎይል ለክርስቶስ ብለው ሁሉንም ነገር የሚተዉበት እንደሆነ ያውቅ ነበር። ነገር ግን አንድ ሰው ሁሉንም ነገር ለክርስቶስ በሚሰጥበት ጊዜ የበለጠ ዋጋ ያገኛል። በዓለም ፊት ቀዳሚውን ስፍራ ሊይዙ የሚፈልጉ ሀብታሞችና ዝነኞች፥ በዘላለሙ መንግሥት የመጨረሻውን ስፍራ ሲያገኙ ክርስቶስን በመከተላቸው ምክንያት ዓለም የናቀቻቸው በእግዚአብሔር መንግሥት ቀዳሚ ይሆናሉ።

11. ኢየሱስ እንደገና ስለ ሞቱ ተነበየ (ማር. 10፡32–34)።

ክርስቶስ የሚሞትበት ጊዜ እየቀረበ ሲመጣ፥ ስለ ሞቱ በበለጠ መናገሩን ቀጠል። ክርስቶስ ስለዚሁ ጉዳይ ለአራተኛ ጊዜ ሲተነብይ፥ ሞቶ እንደሚነሣ ተናግሯል። ክርስቶስ ከስደት ለመሸሽ ያልፈለገው፥ ይህ በግልጽ

የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለነበር ነው። ተከታዮቹም ተመሳሳይ አመለካከት ይኖራቸው ነበር።

12. መሪነት በኢየሱስ መንግሥት (ማር. 10፡35–45)

ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ለምንድን ነው? በማርቆስ 10፡45 የተሰጠው ግልጽ ምሳሌ እንደሚያስረዳው ክርስቶስ የመጣው «ሰዎች እንዲያገለግሉት ሳይሆን፥ ሰዎችን ለማገልገልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት ነበር»። ክርስቶስ የመጣው ሌሎችን እንጂ ራሱን ለማገልገል አልነበረም። የመሥዋዕቱ ጥልቀት ሰዎችን ከኀጢአታቸው ነፃ ለማውጣት መሞቱን ያረጋግጣል።

ይሁንና፥ ክርስቶስ ጠቃሚ ትምህርት ለማስተማር ወደ ምድር መምጣቱን የሚያሳይ ግልጽ ብያኔ ሰጥቷል። ያዕቆብና ዮሐንስ በክርስቶስ መንግሥት ውስጥ ሹመት ለማግኘት ፈልገው ነበር። ይህ የሌሎችንም ደቀ መዛሙርት ፍላጎት ያንጸባርቅ ስለነበር፥ የእነዮሐንስ አነጋገር ሌሎቹን አስቆጣቸው። ክርስቶስ ተከታዮቹ፥ በተለይም መሪዎች ካሳለማውያን የተለየ የአመራር አመለካከት ሊኖራቸው እንደሚገባ ተናግሯል። አመራር ራስን ለማገልገል፥ ክብርን፥ ሥልጣንንና ጎይልን ለማግኘት ተብሎ የሚገባበት ሳይሆን፥ ሌሎችን ለማገልገል የራስን ሕይወት የሚጠይቅ ነው። ማርቆስ፥ መሪዎች ሲባሉ የሌሎች ሰዎች «አገልጋዮች» እንደሚሆኑ ገልጾአል። ሌሎችን ከማገልገል ውጭ የሆነው ምክንያት ከዓለም የሚመጣ በመሆኑ፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ክርስቶስ በሚፈልገው መንገድ ከመምራት ይልቅ፥ ወደ ጥፋት የሚያደርስ ይሆናል። ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ለመምራት ሕይወቱን ስለ ሰጠ፥ እኛም ለሌሎች ይህንኑ ልናደርግ ይገባል።

13. ኢየሱስ ዓይነ ስውሩን በርጤሜዎስ ፈወሰ (ማር. 10፡46–52)

ክርስቶስ ሌሎችን ካገለገለባቸው ምሳሌዎች መካከል፥ ለመሞት ወደ ኢየሩሳሌም በሚሄድበት ጊዜ የለማኙን ጩኸት ሰምቶ የፈወሰበት አንዱ ነው።

14. ኢየሱስ እንደ ሰላም ንጉሥ ወደ ኢየሩሳሌም በድል ገባ (ማር. 11፡1–11)።

አሁን ማርቆስ የክርስቶስን ታሪክ የሚናገርበት መንገድ ተቀይሯል። በፊት ማርቆስ የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠቅሶ የዕለት ተዕለት ሁኔታዎችን ካስረዳ በኋላ፥ «ወዲያውኑ» በሚሉ ዓይነት ቃላት ታሪኩን በፍጥነት ይተርክ ነበር። አሁን ማርቆስ የዕለት ተዕለት ክስተቶችን ይዘረዝራል። እንደ ግሩም ተራኪ፥ አሁን ትረካውን ቀስ በቀስ የታሪኩን ፍጻሜ (የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ) ይገልጻል። በተለይም በስቅለት ዕለት ማርቆስ ክስተቶችን ከሰዓት ሰዓት እየዘረዘረ የታሪኩን ፍጥነት ዝግ አድርጎታል። በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የተገለጹትን የነገሮች ቅደም ተከተል ከዚህ በታች ይመልከቱ፡–

ሀ. እሑድ፡– ኢየሱስ በድል ወደ ኢየሩሳሌም ገባ (ማር. 11፡1–11)።

ለ. ሰኞ፡– ኢየሱስ በለሏን ረገመ፥ ቤተ መቅደሱን አነጻ (ማር.11፡12–19)።

ሐ. ማክሰኞ፡– ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ተጋፈጠ፥ የተለያዩ ትምህርቶችን ሰጠ (ማር. 11፡20–13–37)።

መ. ረቡዕ፡– ኢየሱስ ሽቶ ተቀባ፥ ይሁዳ አሳልፎ ሊሰጠው ተስማማ (ማር. 14፡1–11)።

ሠ. ሐሙስ፡– ቅዱስ ቁርባንና የኢየሱስ መያዝ (ማር. 14፡12–72)።

ረ. ዓረብ፡– ኢየሱስ በጲላጦስ ተመረመረ፥ ተሰቀለ፥ ሞተ፥ ተቀበረ (ማር. 15)።

ሰ. ቅዳሜ፡– ኢየሱስ ተቀበረ።

ሸ. እሑድ፡– ኢየሱስ ከመቃብር ተነሣ (ማር. 16፡1–8)።

ሮማውያን ትልቅ ጦርነት ካሸነፉ በኋላ፥ ለጦር ጄኔራሎቻቸው ከፍተኛ የአቀባበል ሥነ ሥርዓት የማዘጋጀት ባሕል ነበራቸው። የሮም ጄኔራል በትልቅ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ፊት ፊት ሲሄድ፥ ወታደሮች ከኋላ ይከተሉታል። ምርኮኞችና ባሮች ደግሞ ከወታደሮቹ ኋላ ይከተላሉ። ክርስቶስ በድልኒሺነቱ በሁሉም መንገድ የተለየ ነበር። ክርስቶስ የተቀመጠው በተናቀ የአህያ ውርንጭላ ላይ ሲሆን፥ ሰዎችም እርሱን ሳይሆን እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ይዘምሩ ነበር። ነገር ግን በዚህ ጊዜም ቢሆን አይሁዶች ስለ ንጉሣቸው የተሳሳተ አሳብ ይዘው ነበር፤ እርሱ የመጣው የዳዊትን መንግሥት ለመጀመር ሳይሆን ለመሞት ነበርና።

15. ኢየሱስ ነጋዴዎችን ከቤተ መቅደስ አስወጣ (ማር. 11፡12–19)።

ክርስቶስ ወደ ቤተ መቅደሱ በደረሰ ጊዜ ወዲያውኑ በቁጣ ተሞላ። ሰዎች የአምልኮን ስፍራ ለሌላ ዓላማ ሲጠቀሙ በመመልከቱ፥ በአሕዛብ አደባባይ (አሕዛብ የሚያመልኩበት) እንስሳትን ይሸጡ የነበሩትን ነጋዴዎች አባረረ። ክርስቶስ ለምን ተቆጣ? ማቴዎስ የነጋዴዎችን ሌላ ምክንያት ጠቁሟል። በአሕዛብ አደባባይ ውስጥ መገበያየቱ አሕዛብን ከአምልኮ ማደናቀፍ ነበር። ኢሳይያስ 56፡7 አሕዛብ ከአይሁዶች ጎን እግዚአብሔርን ሊያመልኩ እንደሚችሉ ቢገልጽም፥ አይሁዶች ግን ለአሕዛብ በነበራቸው ጥላቻ ምክንያት ወደ እግዚአብሔር እንዳይቀርቡ እየከለከሏቸው ነበር። ማርቆስ የሃይማኖት መሪዎች ክርስቶስን ለመግደል ከፈለጉባቸው ምክንያቶች አንዱ ይሄ እንደሆነ ገልጾአል።

14ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ክርስቲያኖች ኃጢአትን ሳይፈጽሙ ሊቆጡ የሚችሉባቸው አንዳንድ መንገዶች ምን ምንድን ናቸው? ለ) ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች የሚቆጡባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? ሐ) ብዙውን ጊዜ የእኛ ቁጣ ከክርስቶስ ቁጣ የሚለየው እንዴት ነው?

16. ኢየሱስ የበለስን ዛፍ ረገመ (ማር. 11፡12–14፥ 20–26)።

ቀደም ባለው ቀን ክርስቶስ ፍሬ ያላት የምትመስል (ነገር ግን የሌላትን) የበለስ ዛፍ አይቶ ነበር። ይህችን በለስ በፍርድ ረገማት። በቀጣዩ ዕለት ወደ ኢየሩሳሌም በሚሄዱበት ጊዜ በለሲቱ ጠውልጋ በማየታቸው ደቀ መዛሙርቱ ተደነቁ። ክርስቶስ ይህንን የእምነት ትምህርት አድርጎ ተጠቅሟል። እግዚአብሔር ታላቅ አምላክ ስለሆነ፥ የሚነግረን ነገር ሁሉ ይፈጸማል።

እንደ ተራራ የገዘፉ የሚመስሉ ነገሮች ሳይቀር በጸሎታችን ተግባራዊ ይሆናል። እምነት እንደ መከፈቻ ቁልፍ ነች። ቁልፉ በሚዘጋበት ጊዜ የእግዚአብሔር ኃይል ወደ ሕይወታችን ሊፈስ አይችልም። እምነት በሚኖርበት ጊዜ ግን ቁልፉ ክፍት ስለሆነ፥ የእግዚአብሔር ኃይል በነጻነት እየፈሰሰ ተአምራትን ያደርጋል። ይህም አይሁዶች እግዚአብሔር የሚፈልግባቸውን የጽድቅ ፍሬ ባለማፍራታቸው ምክንያት ፍርድ እንደሚመጣባቸው የሚያሳይ ስውር ታሪክ ነበር።

ሦስተኛ ቀን ማርቆስ 11፡27–16፡20

ፀሐይ የኮሌጅ ትምህርቷን በከፍተኛ ውጤት ስላጠናቀቀች፥ በመንግሥትም ሆነ በግል ድርጅቶች ውስጥ የመቀጠር ዕድል ነበራት። ክርስቲያን ብትሆንም፥ እግዚአብሔር ምን እንድታደርግ እንደሚፈልግ አታውቅም ነበር። ብዙ ገንዘብ ለሚከፍላት ድርጅት ለመሥራት ተቀጠረች። በመደበኛነት ወደ ቤተ ክርስቲያን ብትመላለስም፥ እግዚአብሔር ለምን ልዩ ችሎታዎችንና ዕድሎችን እንደ ሰጣት አታውቅም ነበር።

ምሕረቴ ጎበዝ ተማሪ ባለመሆኗ፥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ለመጨረስ ብዙ ታግላለች። ጥሩ የሥራ ዕድል ባለማግኘቷ በቤት ሠራተኛነት ተቀጠረች። ብዙ ደመወዝ ባታገኝም፥ እግዚአብሔር በዚያ ስፍራ እንዳስቀመጣት ታውቅ ነበር። ስለሆነም፥ ተግታ ትሠራ ነበር፤ ሁኔታው ሲያመቻት ለልጆቹ ስለ ክርስቶስ ከመመስከሯም በላይ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ትወስዳቸው ነበር። ለቤተሰቡ አባላትም ክርስቶስ በሕይወቷ ውስጥ ስላመጣው ለውጥ በመመስከር፥ በእርሱ ቢያምኑ ሰላምንና የዘላለምን ሕይወት እንደሚያገኙ ትነግራቸዋለች። ሀብታሞቹ ባልና ሚስት የጋብቻ ችግሮችን በሚጋፈጡበት ጊዜ፥ የእርሷን ምክር ይጠይቃሉ። በምሕረቴ የሕይወት ምስክርነትና ምሳሌነት ባል፥ ሚስትና ልጆች ክርስቶስን ሊያውቁ ቻሉ።

15ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በፀሐይና በምሕረቴ መካከል የነበረው የአመለካከት ልዩነት ምንድን ነው? ለ) ለእግዚአብሔር የበለጠ በማገልገል ላይ የነበረው የማን ሕይወት ነው? ለምን? ሐ) እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገውን ነገር በግልጽ ማወቁ ለሕይወታችን ዓላማና አቅጣጫ የሚሰጠው እንዴት ነው?

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ማርቆስ በክርስቶስ የሕይወት ዓላማ ላይ ያተኩራል። ክርስቶስ የፈውስና የማስተማር አገልግሎት ቢሰጥም፥ ከሰማይ ወደ ምድር የመጣበት ዓላማ ለሰዎች ኃጢአት ቤዛ ለመሆን ነበር። ይህ ግልጽ ዓላማ የክርስቶስን አቅጣጫ አሳይቷል። አሁን ማርቆስ በመስቀል ላይ በመሞት ዓላማውን እንዴት እንደ ፈጸመ ያሳያል። በዚህ የመጨረሻው የማርቆስ ክፍል አንድም ተአምር አልተጠቀሰም። ይህ ክርስቶስ የሚሞትበት ጊዜ ነበር።

16ኛ ጥያቄ፡– ማር. 11፡27–16፡20 አንብብ። ሀ) እነዚህ ምዕራፎች የክርስቶስን ሕይወት ዓላማ የሚገልጹት እንዴት ነው? ለ) ከእነዚህ ምዕራፎች ስለ ክርስቶስ የምንማራቸው ሌሎች ነገሮች ምንድን ናቸው? ሐ) ስለ ደቀ መዝሙርነት ምን ልንማር እንችላለን?

1. በኢየሱስና የሃይማኖት መሪዎች መካከል የተካሄደ ክርክር (ማር. 11፡27–12፡40)

ማርቆስ፥ «ክርስቶስ በአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች ለምን ተገደለ?» የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የክርስቶስን ሕይወት የመጨረሻ ቀናትና ክርስቶስ ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ያካሄዳቸውን ክርክሮች ገልጾአል። ልማዳቸውንና ሰንበትን ባለመጠበቁ ምክንያት፥ የተጠነሰሰው ጥላቻ እያደገ ሄዶ ወደ መስቀል ሞት አድርሶታል።

ሀ. <u>በካህናት አለቆችና በሽንጎው አባላት የቀረበ ጥያቄ (ማር. 11፡27–12፡12)</u>። የአይሁድ አለቆች ክርስቶስ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱና ከቤተ መቅደስ ውስጥ ነጋዴዎችን ማባረሩ መሢሕነቱን እንደሚያመለክት ተገንዝበው ነበር። ነገር ግን ክርስቶስ ይህንን ለማድረግ ሥልጣን ከየት እንዳገኘ ገርሟቸዋል። እነርሱ ሥልጣናቸውን ከየት እንዳገኙ በሚገባ ያውቁ ነበር። ሥልጣናቸው የመጣው ከአሮን የዘር ሐረግ በመሆናቸው ወይም በእውቅ የሃይማኖት ሰው የተማሩ በመሆናቸው ነበር። ክርስቶስ ግን ሥልጣኑ ከሰማይ እንደ መጣ የሚያስረዱ ተአምራትና ትምህርቶችን አቅርቧል። እግዚአብሔር አብ የነገረውን ብቻ እንደሚያደርግም ገልጾላቸዋል (ዮሐ. 5፡36)። ነገር ግን የማወቅ ፍላጎት ስላልነበራቸው፥ ክርስቶስ ጥያቄያቸውን ለመመለስ አልፈለገም። በዚህ ፈንታ፥ የመጥምቁ ዮሐንስ የነቢይነት ሥልጣን ከየት እንደ መጣ ጠየቃቸው። ይህንን ጥያቄ ከመለሱለት፥ እርሱም ጥያቄያቸውን ለመመለስ ተስማማ። ዮሐንስና ክርስቶስ ሥልጣናቸውን ያገኙት ከእግዚአብሔር ነበር። የሃይማኖት መሪዎቹ የክርስቶስን ጥያቄ ለመመለስ ባለመፈለጋቸው፥ እርሱም ጥያቄያቸውን ሳይመልስ ቀረ።

ክርስቶስ የመሬት ባለቤቱንና የጪሰኞችን ታሪክ በመጠቀም፥ የሃይማኖት መሪዎችን ልብ ከፈተ። ክርስቶስ የሃይማኖት መሪዎች ምን ሊያደርጉበት እንደ ፈለጉና ፍጻሜውም ምን እንደሚሆን ለሕዝቡ ነገራቸው። እግዚአብሔር የአይሁድን ሕዝብ (ኢሳ. 5– እስራኤል የእግዚአብሔር ወይን መሆናቸው ተገልጾአል) ለሃይማኖት መሪዎች አደራ ሰጥቷል። መሪዎቹ ግን ሕዝቡን የእግዚአብሔር ሳይሆኑ የራሳቸው ንብረት በማድረግ፥ እግዚአብሔርን አታለሉ። የእግዚአብሔር መልእክተኞች የነበሩትን ነቢያት የገደሉ ሲሆን፥ አሁን ልጁን ሊገድሉ ነበር። ከዚያስ? <u>በመጀመሪያ</u>፥ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ የመሪነት ሥልጣን የነበራቸውን ሰዎች ይገድላል። ይህም ሮማውያን ኢየሩሳሌምን ወርረው አብዛኞቹን የሸንጎ አባላት በመግደላቸው ተፈጻሚነትን አግኝቷል። <u>ሁለተኛ</u>፥ ክርስቶስ ሌሎች መሪዎችን ያስነሣል። እነርሱም የእግዚአብሔርን ሕዝብ በፍትሕ የሚመሩ ሐዋርያት ነበሩ። <u>ሦስተኛ</u>፥ ሊቀበሉ ያልፈለጉትና የገደሉት ክርስቶስ፥ የአዲሱ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሠረት ይሆናል።

17ኛ ጥያቄ፡– ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ ሰዱቃውያን ሊያስቡና ሊሠሩ የሚችሉት እንዴት ነው? ለ) ይህ ክፍል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለእግዚአብሔር ሕዝብ፥ ለሥልጣናቸውና ለሥራቸው ሊኖራቸው ስለሚገባው አመለካከት ምን ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጣል?

ለ. ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ የፖለቲካ ቡድን አካላት የቀረበ ጥያቄ (ማር. 12፡13–17)። ማርቆስ፥ ክርስቶስ በሮም መንግሥት ላይ የተነሣ አማፂ አለመሆኑን ለአንባቢዎቹ ያሳያል። ከአብዛኞቹ አይሁዶች በተቃራኒ፥ ክርስቶስ ሕዝቡ ታክስ ባለመክፈል የሮምን መንግሥት ከመደገፍ እንዲታቀብ እያስተማረ አልነበረም። በተጨማሪም፥ ማርቆስ ክርስቲያን ለሁለት መንግሥታት ታማኝነቱን መስጠት እንዳለበት ያብራራል። በመጀመሪያ፥ ምድራዊ የፖለቲካ መንግሥት ነበር። ክርስቶስ ሰዎች በጉልበታቸው ተጠቅመው አብዮትን እንዲያካሂዱ አልሰበከም። ነገር ግን ቀረጣቸውን ለሮም እንዲከፍሉ ነግሯቸዋል። ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር የነገሠበት ምድራዊ መንግሥት አለ። ይህንንም መታዘዝ ያሻል። ሁለቱ መንግሥታት በሚጋጩበት ጊዜ፥ ክርስቲያኖች ምድራዊውን ሳይሆን ሰማያዊውን ንጉሥ መታዘዝ ይኖርባቸዋል። የክርስቶስ ተከታዮች የሆንን ሁሉ እርሱ የሕይወታችን ንጉሥ እንደሆነ ማስታወስ አለብን። ከዚህ የተነሣ አምልኳችንን፥ ጊዜያችንንና ቁሳዊ ሀብቶቻችንን ጨምሮ፥ በሕይወታችን ሁሉ ላይ መብት እንዳለው መገንዘብ አለብን። ያለን ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ነው።

ሐ. ከሰዱቃውያን የቀረበ ጥያቄ (ማር. 12፡18–27)። ሰዱቃውያን ጥቅም የሌለው ሥነ መለኮታዊ ክርክር ለመቀስቀስ በመፈለጋቸው፥ ሰባት ባሎችን ስላገባች ሴት ክርስቶስን ጠየቁት። እነዚህ ሰዱቃውያን በትንሣኤ የማያምኑ በመሆናቸው፥ ይህን ያሉት ክርክር ለመቀስቀስ ያህል ብቻ ነበር። ክርስቶስ ሰዱቃውያን ትንሣኤን በመካዳቸው ምን ያህል ከፍተኛ ሥነ መለኮታዊ ስሕተትን እንደ ፈጸሙ አስረድቷቸዋል። እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ ነው። በእርሱ የሚያምኑ ሰዎች እንደ አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ በሥጋ ሊሞቱ ቢችሉም፥ በመንፈስ ግን ሕያዋን ናቸው። ለዚህም ነው እግዚአብሔር የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ተብሎ የተጠራው። ስለዚህ፥ ሞትን መፍራት የለብንም። ሞት የህልውናችን ፍጻሜ አይደለም። ሞት መንፈሳችን ሕያው የሚሆንበትን ሌላ ዓይነት ህላዌ ይጀምራል።

መ. ከሃይማኖት ሊቅ የቀረበ ጥያቄ (ማር. 12፡28–34)። ከሕግ የሃይማኖት ሊቃውንት አንዱ የክርስቶስን ጥበብ በተመለከተ ጊዜ፥ ከትእዛዛት መካከል የትኛው እንደሚልቅ ጠየቀው። አይሁዶች በብሉይ ኪዳን ውስጥ 613 መሠረታዊ ሕግጋት እንዳሉ ያምኑ ነበር። ከእነዚህ ሕግጋት መካከል የትኞቹ «ከባድ» የትኛው ደግሞ «ቀላል» እንደሆነ ለማወቅ ይጥሩ ነበር። ስለዚህ ይህ ሰው ክርስቶስ ከሁሉም በላይ ከባዱ ሕግ የትኛው እንደሆነ እንዲነግረው መጠየቁ ነበር። ክርስቶስ እያንዳንዱ ሃይማኖት አጥባቂ አይሁዳዊ በየጠዋቱና በየግታዊ የሚደግመውን ዘዳግም 6፡4–5 በመጥቀስ መልስ ሰጠው። በዚህ ክፍል፥ ከሕጉ በስተ ጀርባ በእግዚአብሔር ማንነት ላይ ትክክለኛ እምነት አለ። ስለ እግዚአብሔር ያለን አመለካከት የተሳሳተ ከሆነ፥ አንድን ሕግ ለመጠበቅ መሞከሩ ዋጋ የለውም። በመጀመሪያ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን በመጥቀስ ክርስቶስ የሕግጋት ሁሉ መሠረቱ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር እንዳልሆነ ተናግሯል። እግዚአብሔርን በሁለንተናችን ብንወደው (በልባችን፥ በነፍሳችንና በጉልበታችን)፤ እግዚአብሔርን የሚያስቀይም ተግባር ልንፈጽም

አንችልም። ሁለተኛ፥ ከዘሌዋውያን 19፡18 በመጥቀስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን ከመወደድ ጋር ሰውን መውደድም ግንኙነት ያለው መሆኑን ገልጾአል። እግዚአብሔር ከእርሱና ከሌሎች ሰዎች ጋር ስላለን ግንኙነት አጥብቆ ስለሚያስብ፥ የመጀመሪያውና ሁለተኛው ትእዛዝ ሊነጣጠሉ አይችሉም።

18ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እግዚአብሔርን ከመውደድ ሥር የተጠቀሱትን ሕግጋት ዘርዝር። ለ) ሌሎችን እንደ ራሳችን ከመውደድ ሥር የተጠቃለሉትን ሕግጋት ዘርዝር። ሐ) እነዚህ ሕግጋት ከአምልኳችን (ከሚቃጠል መሥዋዕት) በላይ አስፈላጊዎች ከሆኑ፥ ዕለተ እሑድ ወደ አምልኮ ስፍራ ከመሄዳችን በፊት ምን ልናደርግ ይገባል?

የሃይማኖት መሪዎች እነዚህ ሁለት ትእዛዛት ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ግንኙነት መሠረት መሆናቸውን ወዲያውኑ ተገነዘቡ። እነዚህ ትእዛዛት እንደ መሥዋዕት፥ መዝሙር፥ ስብከት ወይም የገንዘብ ስጦታ ከመሳሰሉት ውጫዊ የአምልኮ ተግባራት በላይ አስፈላጊዎች ነበሩ። ብዙ ክርስቲያኖች እሑድ ዕለት ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው ሊዘምሩ፥ የመዘምራንን ዜማ ሊሰሙና ስብከት ሊከታተሉ ይወዳሉ። በእዘቦት ቀናት ግን እግዚአብሔርን ከማስከበርና ለእርሱ ያላቸውን ፍቅር ከማንጸባረቅ ይታቀባሉ። ብዙውን ጊዜ ከቤተሰቦቻቸውና ከሌሎችም ጋር ጤናማ ግንኙነት የላቸውም። ክርስቶስ አምልኮ ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ሰዎች ጋር ካለን ግንኙነት እንደሚጀምር አስተምሯል። እያንዳንዱ የሕይወታችን አካል የእግዚአብሔርን ፈቃድ እስካልተከተለ፥ በፍቅር እስካልተሞላና ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት ሁሉ ከፍቅር ቁጥጥር ሥር እስካልዋለ ድረስ፥ የትኛውም የአምልኳችን ተግባር እግዚአብሔርን ሊያስደስት አይችልም።

ሠ. ኢየሱስ ለሃይማኖት መሪዎች ያቀረበው ጥያቄ (ማር. 12፡35-40)። የሃይማኖት መሪዎች ሊያጠምዱት ሲሞክሩ ከቆዩ በኋላ፥ ክርስቶስ የሚጠይቅበት ጊዜ ደረሰ። ክርስቶስ ምናልባትም ቀደም ሲል ያላስተዋሉትን ሥነ መለኮታዊ እውነት እንዲገነዘቡ ነበር የፈለገው። በጥያቄውም መሢሑ የዳዊት ልጅ ቢሆንም፥ አምላክ መሆኑን ዳዊት በመዝሙሩ ውስጥ ጌታ እንዳለው በመጥቀስ ገለጸላቸው [መዝ. (110)፡1)]።

ክርስቶስ ሕዝቡ የሃይማኖት መሪዎችን ዓይነት አመለካከት እንዳይይዙ አስጠንቅቋል። በራስ እውቀት፥ ሃይማኖትና ክርስቶስን ለማመን ባለመፈለግ መኩራራት አደገኛ ነገር ነው። የሃይማኖት መሪዎች የሰዎችን ሙገሳ ይፈልጉ ነበር። ለእነርሱ ሃይማኖት በሌሎች ዘንድ የመታወቂያ መሣሪያ ነበር። ሰዎች ወዲያውኑ እንዲለዩዋቸውና እንዲያከብሯቸው በማሰብ ለየት ያሉ ልብሶችን ይለብሳሉ። በሚያመልኩበት ጊዜ በቤተ መቅደሱ ውስጥ የፊተኛውን ስፍራ ይይዛሉ። እነዚህ መሪዎች በሰዎች ፊት ለመታየት ረዣዥም ጸሎቶችን ቢጸልዩም፥ ሌሎችን ሰዎች በተለይም ተስፋ የሌላቸውን መበለቶችና እንደ እነርሱ ዓይነቶችን ከመበደል አልተመለሱም።

19ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እኛም በአለባበሳችን፥ በአቀማመጣችን፥ በአዘማመራችን፥ በአሰባበካችን ወይም በማስተማር ስልታችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተለይተን ለመታወቅ የምንጥርባቸው አንዳንድ መንገዶች ምንድን ናቸው? ለ) ክርስቶስ ዛሬ በመካከላችን ቢኖር፥ ስለ አመለካከቶቻችንና ኩራታችን የሚሰጠን ማስጠንቀቂያ ምን ይሆን ነበር?

2. ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ እውነተኛ አሰጣጥ አስተማረ (ማር. 12፡41–44)።

በተፈጥሯዊ መንገድ የአንድን ስጦታ ታላቅነት ከምንለካባቸው መንገዶች አንዱ፥ የስጦታውን መጠን መመልከት ነው። አንድ መቶ ብር ወይም ከዚያ የበለጠ ገንዘብ የሚከፍሉትን ሰዎች እያደነቅን፥ ዐሥር ሣንቲም ብቻ የሚሰጡትን ችል እንላለን። ብዙ የሚሰጡትን እያከበርን፥ ጥቂት ብቻ የሚሰጡንን እንንቃለን። ክርስቶስ ግን እግዚአብሔር አንድን ስጦታ የሚለካው፥ ሰጭውን ምን ያህል እንደሚጎዳው በማገናዘብ መሆኑን ገልጾአል። ዐሥር ብር ብቻ ያላት ድሀ ሴት አምስት ብር በምትሰጥበት ጊዜ፥ አሥር ሺህ ብር ኖሮት አንድ መቶ ብር ከሚሰጠው ነጋዴ የበለጠ ሰጥታለች ማለት ነው። በተማሩትና በሀብታሞች ተማርከን፥ እግዚአብሔር ሰዎችን የሚመለከትበትን ሁኔታ እንዳንረሳ መጠንቀቅ አለብን።

20ኛ ጥያቄ፡– ብዙ ገንዘብ የሚሰጡትን፥ የተማሩና ሀብታሞች የሚመስሉትን እያከበርን፥ ትንሽ ገንዘብ ብቻ የሚሰጡትን ድሆችና ያልተማሩ ሰዎች ችል ልንል የምንችለው እንዴት ነው?

---

3. <u>ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ዳግም ምጽአቱ ምልክቶች ነገራቸው (ማር. 13)</u>። የክርስቶስን ምጽአት የሚያሳዩ ምልክቶችና፥ ክርስቲያኖችም እንዴት ለምጽአቱ መዘጋጀት እንዳለባቸው ብዙ ማብራሪያ ከሰጠው ማቴዎስ በተቃራኒ፥ ማርቆስ በምልክቶች ላይ ብቻ ትኩረት አድርጓል። ከእነዚህ ምልክቶች አብዛኛዎቹ በማቴዎስ 24 ውስጥ ስለ ተጠቀሱ፥ በዚህ ክፍል ዝርዝራቸውን ከማቅረብ የበለጠ ተግባር እናከናውንም።

ሀ. ብዙ ሐሰተኛ መሢሖች ለሕዝቡ ችግሮች መፍትሔ እንደሚያመጡ ምርጥ የእግዚአብሔር መሪዎች አድርገው ራሳቸውን ያቀርባሉ። አንዳንዶች «ክርስቶስ» ተብለው በመጠራት ተአምራት ይሠራሉ።

ለ. ጦርነቶችና የጦርነት ወሬዎች ይሰማል።

ሐ. እንደ መሬት መንቀጥቀጥና ረሃብ ያሉ የተፈጥሮ አደጋዎች ብቻ ይከሰታሉ።

መ. በክርስቲያኖች ላይ ታላላቅ የስደት ጊዜያት ይደርሳሉ። የክርስቶስ ተከታዮች በአይሁድ (ምኩራቦች)፥ እና በአሕዛብ (መንግሥታትና ነገሥታት) ፊት ቀርበው ለእምነታቸው መልስ ለመስጠት ይገደዳሉ። በዚህ ጊዜ ለመሪዎቹ ምላሽ ለመስጠት ከመፍራት ይልቅ፥ መንፈስ ቅዱስ የሚናገሩትን ቃል እንደሚሰጣቸው መተማመን ይኖርባቸዋል። እነዚህን ዕድሎች በመጠቀም ለመሪዎች መመስከር አለብን።

ሠ. ወንጌሉ በዓለም ሁሉ ለሁሉም የጎሳ ቡድኖች ይሰበካል።

ረ. ይህ ወንጌል በቤተሰቦች መካከል ከፍተኛ መለያየትን ስለሚያስከትል፥ የክርስቶስ ተከታዮች ይጠላሉ፤ ይሰደዳሉ። በዚህን ጊዜ ግን እኛ ለክርስቶስ ታማኞች ሆነን መጽናት አለብን።

ሰ. የጥፋት ርኩሰት ይከሰታል። (<u>ማስታወሻ</u>፡– ይህ ኢየሩሳሌም በሮማውያን መደምሰሷን ወይም በመጨረሻው ዘመን የሚከሰተውን ሌላ

ድርጊት ስለ ማመልከቱ እርግጠኞች አይደለንም። ምናልባትም ሁለቱንም ያመለክት ይሆናል።) ዓለም ከዚህ በፊት አይታ የማታውቀው ከፍተኛና ፈጣን ጥፋት ይመጣል።

ሸ. ፀሐይን፥ ጨረቃንና ከዋክብቶችን የሚያጠቃ የህዋ አካላት ወይም ኮስሚክ (cosmic) ውድመት ይመጣል። (ይህ እግዚአብሔር በዓለም ላይ አስከፊ ፍርድ የሚያመጣበትን ሁኔታ የሚያሳይ የተለመደ አገላለጽ ነው። ኢሳ. 13፡10፥ ኢዩ. 2፡10፥ 31፤ አሞጽ 8፡9)።

ቀ. ነገሮች እጅግ በሚከፉበት ሰዓት፥ ክርስቶስ ከመላእክቱ ጋር በመምጣት ልጆቹን (ምርጦቹን) ወደ ዘላለማዊ ፍርድ ከሚሄዱት ይለያቸዋል።

በ. ምንም እንኳ እነዚህ ምልክቶች የክርስቶስን ምጽአት ቢያሳዩም፥ (የበለሰ ዛፍ የዓመቱን ወራት እንደምታሳይ ሁሉ)፥ ትክክለኛውን ቀን ወይም ዓመት ለይቶ ማወቅ አይቻልም።

ጎ. የክርስቶስ ተከታዮች የሆንን ሰዎች ምጽአቱን እየተጠባበቅን፥ በታማኝነት መመላለስ አለብን። ከተሰጡት ምልክቶች ሁሉ ባሻገር፥ ክርስቶስ ባልተጠበቀ ሰዓት ይመጣል። ክርስቶስ ቶሎ አይመጣም ብለን በመንፈሳዊ ሕይወታችን ሳንሰንፍ፥ ክርስቶስ ዛሬ ሊመጣ እንደሚችል በማሰብ ሕይወታችንን ማጥራት አለብን።

21ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ክርስቶስ ነገ እንደሚመጣ ብታውቅ ኖሮ ምን ታደርግ ነበር? ለ) እነዚህን ነገሮች አሁን የማታደርገው ለምንድን ነው?

3. ኢየሱስ ለመስቀሉ ተዘጋጀ (ማር. 14፡1–42)

ሀ. <u>ኢየሱስ ለሞቱ በመዘጋጀት ሽቶ ተቀባ (ማር. 14፡1–11)</u>። የክርስቶስ ሞት ድንገተኛ ነበር? አልነበረም። ክርስቶስ ላለፉት አያሌ ወራት ወደ ተወዳጇ ኢየሩሳሌም ሲደርስ፥ እንደሚገደልና ከሞት ግን እንደሚነሣ ለደቀ መዛሙርቱ ነግራቸው። ከመስቀሉ ሁለት ቀናት ቀደም ብላ አንዲት ሴት ውድ ሽቶ ቀባችው። ክርስቶስ ይህ ለቀብሩ መታሰቢያ እንደሚሆን ገለጸ። በወንጌላት አማካኝነት ከዚያም የዚህች ሴት ታላቅ ድርጊት ለዓለም ሁሉ እንደሚነገር አረጋገጠላቸው። ይህች ሴት ለክርስቶስ ያላየችው ይህ ታላቅ ወሮታ ለዘላለም ሲዘከር ይኖራል።

ይህች ሴት ለክርስቶስ ከገለጸችው መንፈሳዊ ፍቅር በተቃራኒ፥ ከክርስቶስ ጋር ለሦስት ዓመታት አብሮት የኖረው የአስቆሮቱ ይሁዳ፥ ክርስቶስን አሳልፎ ለመስጠት ከካህናት አለቆች ጋር ተስማማ። ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት አንዱ በመሆኑ፥ ከክርስቶስ የቅርብ ወዳጆች አንዱ ነበር። ለክርስቶስም ፍቅር ሊኖረው ይገባ ነበር።

ለ. <u>ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካ ምግብ በላ (ማር. 14፡12–26)</u>። ከሌሎች የሲኖፕቲክ ጸሐፊዎች በላይ ማርቆስ ስለ ክርስቶስ የመጨረሻው እራት ብዙ አሳቦችን ሰንዝሯል። ስለዚህም፥ ብዙ ምሑራን ይህ የመጨረሻው ምግብ በማርቆስ ቤት እንደ ተካሄደ ይገምታሉ። ማርቆስ ውኃ የተሸከመውን ሰውዬ ያውቅ ነበር። በአይሁድ ባሕል ውኃ መቅዳት የሴቶች ሥራ ነበር። ምናልባትም በቤታቸው ሴት ልጆች ባለመኖራቸውና መበለት እናቱ የፋሲካ

ምግብ በማዘጋጀት ላይ ስለነበረች፥ ማርቆስ ውኃ ለመቅዳት ተገዶ ይሆናል። ያም ሆነ ይህ፥ ጴጥሮስና ዮሐንስ ውኃ የተሸከመውን ሰው በቀላሉ ሊለዩትና ሊከተሉት ችለዋል። ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካ በዓል ለመብላት ቀደም ብሎ ዝግጅት አድርጎ ስለነበር፥ እዚያ በደረሱ ጊዜ ሁሉም ነገር ተዘጋጅቶ ነበር። ክርስቶስ ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው ማወቁን ለይሁዳ ጠቁሞታል። ክርስቶስ በሚፈስሰው ደሙ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል አዲስ ቃል ኪዳን እንደሚፈጸም ለደቀ መዛሙርቱ በመግለጽ፥ የጌታን እራት መሠረተ።

ሐ. ኢየሱስ በመጭው የመስቀል ላይ ሞቱ ሳቢያ ታወከ (ማር. 14፡27–42)። ወደ ጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ እየሄዱ ሳለ፥ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደሚሸሹ ነገራቸው። በተጨማሪም፥ ከሞት ተነሥቶ በገሊላ ከእነርሱ ጋር እንደሚገናኝ አሳሰባቸው። ጴጥሮስ በፍጹም እንደማይክደው ሲናገር፥ ክርስቶስ ግን ሦስት ጊዜ እንደሚክደው ገለጸለት። ክርስቶስ በቀጣዩ ሁለት ቀናት ውስጥ የሚፈጸሙትን ዝርዝር ጉዳዮች ያውቅ ስለነበር፥ ምንም ነገር ድንገተኛ አልሆነበትም። የመስቀል ላይ ሞቱ ድንገተኛ ክስተት አልነበረም። ይህ ክርስቶስ ሁልጊዜም የሚያመራበት አቅጣጫ እንጂ የሮም ወይም የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች በጣም ኃይለኞች በመሆናቸው ምክንያት የተከሰተ ጉዳይ አልነበረም።

ጌቴሴማኒ በደረሰ ጊዜ ክርስቶስ በጎዘን ታወከ። እጅግ የቅርብ ወዳጆቹ የነበሩት ጴጥሮስ፥ ዮሐንስና ያዕቆብ እንዲጸልዩለት ጠየቃቸው። ሦስት ጊዜ እግዚአብሔር የመስቀል ላይ ሞትን «ጽዋ» እና የዓለምን ኃጢአት መሸከምን እንዲያስወግድለት ጠየቀ። ክርስቶስ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ሊያደርግ እንደሚችል ያውቅ ነበር። ነገር ግን ክርስቶስ በአባቱ ላይ ካለው እምነቱ ባሻገር፥ ለአብ ፈቃድ ራሱን ያስገዛ ነበር። እንቅልፍ የተጫጫናቸው ደቀ መዛሙርት በጸሎት ሊረዱት አልቻሉም ነበር። ብዙ ምሑራን በእነዚህ ታሪኮች ውስጥ ማርቆስ ከጴጥሮስ ጋር መቀራረቡን ይመለከታሉ። ጴጥሮስ በራሱ ላይ እየደረሰ ላለው ፈተና ባለመጸለዩ ክርስቶስ እንደ ገሠጸው (ማር. 14፡37–38) እና ጴጥሮስ ክርስቶስን ስለ ካደበት ሁኔታ ማርቆስ ተጨማሪ ዝርዝር አሳቦችን ማስፈሩ የምሑራኑን አሳብ የሚያጠናክር ይመስላል። (ማቴ. 26፡69–75ን ከማር. 14፡66–72 ጋር አነጻጽር።)

ጴጥሮስ፥ ዮሐንስና ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ብርታት ሊጠይቁ በሚገባቸው የፈተና ሰዓት ማንቀላፋታቸውን ማርቆስ ሲገልጽ፥ ለሁላችንም ማስጠንቀቂያ እየሰጠን ነበር። ከሕይወታችን ኀጢአትን ለማስወገድ ከፈለግን፥ የሥጋን መንገድ ትተን እግዚአብሔር በሚፈልገው አቅጣጫ መጓዝ አለብን። እንዲሁም በስደትና በፈተና ጊዜ ለክርስቶስ ጸንተን ለመቆም ከፈለግን፥ የጸሎት ሰዎች ልንሆን ይገባል። ጸሎት ቀላል ወይም ተፈጥሯዊና መንፈሳዊ ተግባር አይደለም። ብዙውን ጊዜ ጸሎት እጅግ በሚያስፈልገን ሰዓት ሥራ ይበዛብናል ወይም እንደከማለን። ነገር ግን ሥጋችንን ለፈቃዳችን አስገዝተን በጸሎት ልንተጋ ይገባል። ብርታትን የምናገኘው ከጸሎት ነው።

4. የኢየሱስ መያዝና መመርመር (ማር. 14፡43–15፡20)።

ሀ. <u>የኢየሱስ መያዝ (ማር. 14፡43–52)</u>። ክርስቶስ በሮም ላይ የተነሣ አማፂ ነበር? የሞተው በዚህ ምክንያት ነበር? ሌሎች የአማፅያን መሪዎች ተከላካይ ሠራዊት ነበራቸው። ክርስቶስ ግን የተደራጀ ሠራዊት ስላልነበረው፥ በተያዘበት ወቅት ለመዋጋት አልሞከረም። አብረውት የነበሩት አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ትተውት ሸሽተዋል። ክርስቶስ ለሮም አስጊ ሰው እንዳልነበረ ግልጽ ነው።

ማርቆስ ከሌሎች ደቀ መዛሙርት በላይ ጠንካራ ስለነበረው ወጣት የጻፈው ታሪክ አስገራሚ ነበር። ከርቀት ክርስቶስን ለመከተል ሞከረ፤ ሊይዙት ባለበት ወቅት ልብሱን ትቶ ራቁቱን ሸሸ። ይህ ታሪክ የተጠቀሰው በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ብቻ በመሆኑ፥ ብዙ ምሑራን ራሱ ዮሐንስ ማርቆስ ሳይሆን እንደማይቀር ያስባሉ።

ለ. <u>ኢየሱስ በሸንጎው ፊት ተመረመረ (ማር. 14፡53–65)</u>። ይህ ሸንጎ 71 የካህናት አለቆች፥ ሽማግሌዎችና የሃይማኖት መሪዎች የተካተቱበት ነበር። በአይሁድ ሕግ ከፍተኛው የሥልጣን አካል ይሄ ሸንጎ ነበር። በክርስቶስ ላይ ግልጽ ክስ ለማቅረብ ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም። ክርስቶስ የብሩክ አምላክ ልጅ የሆነ መሢሕ ስለመሆን አለመሆኑ እንዲነግሯቸው በጠየቁት ጊዜ ብቻ፥ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ቀኝ የሚቀመጥ የሰው ልጅ መሆኑን በመናገሩ በእግዚአብሔር ላይ ተሳድቧል የሚል ክስ አግኝተዋል። አሁንም ቢሆን አይሁዶች በክርስቶስ ላይ ያገኙት ክስ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የማድረግ ሃይማኖታዊ ጉዳይ በመሆኑ፥ ክርስቶስ ለሮማውያን አስጊ ሰው አልነበረም። አይሁዶች በክርስቶስ ላይ በመትፋትና በመደብደብ፥ ክርስቶስ የተጠላና ያልተፈለገ ያህል መሆኑን አሳይተዋል (ዘኁል. 12፡14፤ ዘዳግ. 28፡9)። አይሁዶች እውነተኛ ነቢይ ነገሮችን በቅርቡ ለይቶ ያውቃል የሚል እምነት ስለ ነበራቸው፥ ዓይኖቹን ከሸፈኑ በኋላ ትንቢት እንዲናገር ጠየቁት።

ሐ. <u>ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ (ማር. 14፡66–72)</u>። ብዙውን ጊዜ ኃጢአታችንን ለመደበቅ እንፈልጋለን። የጴጥሮስ ወዳጅ የነበረው ማርቆስ፥ ጴጥሮስ ክርስቶስን የካደበትን ኃጢአት ቢደብቅ አያስገርምም ነበር። ነገር ግን ማርቆስ፥ የክርስቶስን መሢሕነት በድፍረት የመሰከረው እጅግ ጠንካራውና ለክርስቶስ ለመሞት ቃል የገባው ብርቱው ደቀ መዝሙር፥ በሁለት ሴቶችና በጥቂት ቡድኖች ፊት ስለካደበት ሁኔታ ጽፎአል። ምናልባትም ማርቆስ ይህንን ያደረገው በራሱ በጴጥሮስ ግፊት ሳይሆን አይቀርም። እንደ ጴጥሮስ ማናችንም ክርስቶስን ልንክድ እንችላለን። ነገር ግን ክርስቶስ በቸርነቱ ጴጥሮስን ይቅር እንዳለው፥ እኛንም በምንክደው ጊዜ ይቅር ሊለን ይችላል።

ክርስቶስን በብዙ መንገዶች ልንክደው እንችላለን። ይህም በክፍል ውስጥ ስለ ክርስቶስና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የምናውቀውን ለማካፈል በምንፈራበት ጊዜ፥ በሥራ ቦታ ለመመስከር ስንፈራ፥ እንዲሁም ጓደኞቻችን እንዳይሳለቁብን በመፍራት የስሕተታቸው ተካፋይ ስንሆን ክርስቶስን እንክዳለን። ማንም ሰው ክርስቶስን እንደማይክድና እጅግ ብርቱ ወይም በሳል እንደሆነ አድርጎ ሊያስብ አይገባም። መፍትሔው ደግሞ ኃጢአታችንን

መደበቅ ሳይሆን፥ መቀበል ነው። ማመኻኛ ሳናቀርብ ኃጢአታችንን ልንናዘዝ ይገባል። ይህም የምንወደውን አምላካችንን በመካዳችን የተሰማንን ሕመም በመፈወስና ይቅርታን በማስገኘት ደስ ያሰኘናል።

22ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ክርስቶስን በሆነ መንገድ የካድህበትን ጊዜ ግለጽ። ለ) ለምን? ሐ) በምንወድቅበት ጊዜ ስለምናገኘው ይቅርታ ከዚህ ታሪክ ምን እንማራለን?

መ. <u>ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት ተመረመረ</u> (ማር. 15፡1–20)። በሮማውያን ሳይሾሙ ንጉሥ ነኝ ማለቱ በአብዛኛው በሮም ላይ እንደ ማመፅ ይቆጠር ነበር። ነገር ግን የሮም ገዥ የሆነው ጲላጦስ እንኳ ክርስቶስ ሮምን የሚያሰጋ የነገሥታት ንጉሥ እንዳልሆነ ያውቅ ነበር። ክርስቶስን ብዙ ጊዜ «የአይሁድ ንጉሥ» ሲል ጠርቶታል። ነገር ግን ክርስቶስ እንዲፈታ ለማድረግ የሚችለውን ያህል ጥሯል። ምናልባትም ሮማውያን በደካማና ጥበብ በጎደለው አመራሩ ስለሚታወቀው ጲላጦስ ቀደም ሲል የሰሙት አደገኛ ነገር ሳይኖር አይቀርም። ማርቆስ ወንጌሉን በሚጽፍበት ጊዜ ጲላጦስ ከመሪነቱ ሥልጣን ተነሥቶ ነበር። ስለዚህም ማርቆስ ለሮማውያን እንደራሴ የነበረው ጲላጦስ፥ ክርስቶስ ዓማፂ አለመሆኑን እንደሚያውቅ ገልጾአል። ነገር ግን ሕዝቡን በመፍራቱ ምክንያት ንጹሑ የነበረው ክርስቶስ እንዲሰቀል ተስማምቷል።

5. የኢየሱስ መሰቀል፥ መሞትና መቀበር (ማር. 15፡21–47)

ክርስቶስ በደረሰበት ከፍተኛ ድብደባ ምክንያት በመድከሙ፥ ሮማውያን ስምዖን መስቀሉን ተሸክሞ ክርስቶስ ከሁለት ወንበዴዎች ጋር ወደሚሰቀልበት ከከተማ ወጣ ያለ ስፍራ እንዲያደርስ አስገደዱት። ብዙውን ጊዜ ወንጀለኞች ወንጀላቸው የተዘረዘረበት ጨርቅ ከአንገታቸው ላይ ይደረግና መስቀሉን ተሸክመው ወደሚሰቀሉበት ስፍራ እንዲወሰዱ ይገደዱ ነበር። ማርቆስ መስቀሉን የተሸከመው ስምዖን፥ የአሌክሳንድሮስና የሩፎስ አባት እንደነበር ገልጾአል። ጳውሎስም በሮም 18፡13 ሩፎስን ስለሚጠቅስ፥ እነዚህ ሰዎች ምናልባትም በሮም የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሳይሆኑ አይቀሩም።

ስቅላት እጅግ አስከፊ ግድያ ዘዴ በመሆኑ፥ ባሮችና ከፍተኛ ወንጀል የሚፈጽሙ ሰዎች ወይም አማፅያን ብቻ በዚህ ዓይነት ይገደሉ ነበር። የአይሁድ መሪዎች ለክርስቶስ በነበራቸው ከፍተኛ ጥላቻ ምክንያት ለዚህ ቅጣት ዳረጉት። በእጆቹና በእግሮቹ ላይ ምስማሮችን ቸነከሩባቸው። በዚህ ዓይነት ስቅላት የሚቀጡ ሰዎች ነፍሳቸው እስኪወጣ ድረስ በአብዛኛው ከሁለት እስከ ሦስት ቀናት ይሠቃዩ ነበር። የተሰቀለው ሰው ቶሎ እንዲሞት ለማድረግ፥ አንዳንድ ጊዜ ወታደሮች ቅልጥሙን ይሰብሩ ነበር።

ክርስቶስን የሰቀሉት ወታደሮች የክርስቶስን ልብስ ተከፋፈሉ። ከሦስት ሰዓት ጀምሮ እስከሞተበት ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ዋለ። ክርስቶስ ከሚቀበለው ሥጋዊ ሥቃይ በላይ ሰዎች በቃላት ይዘልፉት ነበር። ከሁሉም በላይ፥ ክርስቶስ የዓለምን ኃጢአት በመሸከሙ ምክንያት እግዚአብሔር አብ ከእርሱ ጋር የነበረውን ኅብረት አቋረጠ። ክርስቶስ በታላቅ ድምፅ ጮኾ መሞቱ፥ ክርስቶስ ነፍሱን እንደ ሰጠ ያመለክታል። ብዙውን ጊዜ የስቅላት ቅጣት የሚፈጽምባቸው ሰዎች እየተዳከሙ ሄደው ራሳቸውን ይስቱና በዚያው ያርፋሉ።

በዚህ ጊዜ ማርቆስ ስለ ክርስቶስ አንድ መልካም ቃል ብቻ ተናግሯል። ክርስቶስ በሚሞትበት ጊዜ አይሁዶች ምን እየሆነ እንዳለ ወይም ክርስቶስ የተለየ ሰው መሆኑን አልተገነዘቡም ነበር። ነገር ግን ቀደም ሲል ብዙ ሰዎች ሲሰቀሉ የተመለከተው የሮም ወታደር፥ ክርስቶስ የተለየና የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ተገነዘበ።

የአርማቲያሱ ዮሴፍ ጲላጦስ የክርስቶስን አስከሬን እንዲሰጠው በጠየቀ ጊዜ፥ ጲላጦስ ክርስቶስ ቶሎ በመሞቱ ተደነቀ። የመቶ አለቃው ክርስቶስ መሞቱን ካረጋገጠ በኋላ፥ ዮሴፍ የክርስቶስን አስከሬን ለመውሰድ ፈቃድ አገኘና በራሱ መቃብር ውስጥ ወስዶ ቀበረው። በመጨረሻም፥ ከዮሴፍና ኒቆዲሞስ በተጨማሪ ለክርስቶስ ትኩረት ሰጥተው የቆዩ ሦስት ብቸኛ ሰዎች ነበሩ። እነርሱም ከክርስቶስ ጋር የኖሩ ሴቶች ሲሆኑ ክርስቶስ ሰባት አጋንንት ያወጣላት መግደላዊት ማርያም፥ የታናሹ ያዕቆብና የዮሳ እናት የሆነችው ማርያም፥ የዮሐንስና ያዕቆብ እናት የሆነችው ሰሎሜ ከእርሱ ጋር ቆዩ። አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ከሸሹ በኋላ፥ እነዚህ ሴቶች ጌታቸው ሲሞትና ሲቀበር ለማየት እዚያው ቆዩ።

> 23ኛ ጥያቄ፡– ብዙውን ጊዜ ወንዶች ከሴቶች በላይ ደፋሮች እንደሆኑ ይነገራል። በዚህ ጊዜ ግን ሴቶች ከወንዶች በላይ ደፍረው የተገኙት ለምን ይመስልሃል? ይህ እነዚህ ሦስት ሴቶች ለክርስቶስ ስለነበራቸው የእምነት ጥልቀት ምን ያስተምራል?

መጀመሪያ የማርቆስን ወንጌል ያነበቡ ብዙ ሰዎች ከፍተኛ ስደት ደርሶባቸዋል። አንዳንዶች በእንስሳት ቆዳ ተሸፍነው ለዱር አራዊት ተጥለዋል። ሌሎች ዘይት ተርከፍክፎባቸው በስታዲዮም እንደ ሻማ እየነደዱ ብርሃን እንዲሰጡ ተደርገዋል። ከወታደሮች ወይም ከአናብስት ጋር ለመታገል የተገደዱም ነበሩ። አንዳንዶች እንደ ክርስቶስ ተሰቅለዋል። ነገር ግን ስደቱ ምንም ያህል ከባድ ቢሆንም፥ ጌታቸው ክርስቶስ በስቅላት እንደ ሞተ በመገንዘብ ይጽናኑ ነበር። የእርሱ ሞት ለአሚኗታቸው አርአያ ነበር። ጳውሎስ በኋላ እንደገለጸው፥ ክርስቲያኖች መከራ በመቀበልና በመሠዋት ለቤተ ክርስቲያን የጎደለውን ይፈጽማሉ (ቆላ. 1፡24)።

6. ኢየሱስ ከሞት ተነሣ (ማር. 16)።

ማርቆስ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ያቀረበው ዘገባ ከሁሉም ወንጌላት አጠር ያለ ነው። ይህም በተለይ ብዙ ምሑራን እንደሚሉት፥ ምዕራፍ 16 ቁጥር 8 ላይ የሚያበቃ ከሆነ እውነት ነው ማለት ይቻላል። የክርስቶስን መቀበር የተመለከቱት ሦስት ሴቶች ወደ መቃብሩ ተመለሱ። በዚህ ጊዜ የተመለከቷቸው መላእክት ክርስቶስ ከሞት እንደ ተነሣና ወደ ገሊላ እንደ ሄደ ነገሯቸው። ደቀ መዛሙርቱ በዚያ ከእርሱ ጋር ተገኝተዋል።

ማርቆስ ወንጌሉን የፈጸመው በሴቶቹ ፍርሃትና ግራ መጋባት ነው። ለምን እንዲህ መጽሐፉን ድንገት ጨረሰው? አንዳንድ ምሑራን ማርቆስ መጽሐፉን ቁጥር 8 ላይ የጨረሰው አንባቢያኑ ስለ ትንሣኤ እንዲያስቡ ለማድረግ እንደሆነ ያስባሉ። ክርስቲያኖች ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን ማምለካቸው፥ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ገሊላ ሄደው ከክርስቶስ ጋር እንደ ተገናኙ ያረጋግጣል። በዚህ ጊዜ ሕይወታቸው ሙሉ በሙሉ ተለወጠ። ቤተ

ክርስቲያን የተመሠረተችው በዚያ ነበር። ሰዎች በክርስቶስ የሕይወት ታሪክ ግራ ተጋብተው ለመናር ወይም በክርስቶስ አምነው ግራ መጋባታቸውን ለማስወገድ ምርጫ ነበራቸው።

ሉቃ ምሑራን የማርቆስ የመጀመሪያው መደምደሚያ እንደ ጠፋ ያስባሉ። ለዚህም ነው የቀድሞዎቹ ጸሐፊዎች አብዛኞቹ የማርቆስ ወንጌል የመጀመሪያ ቅጂ አካል አይደለም የሚሉትን ማርቆስ 16፡9–20 ላለመጨመር የተገደዱት።

ማርቆስ 16፡9–20 በሉቃ ወንጌላትና የሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚገኙትን አንዳንድ ታሪኮች ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል። ከማቴዎስ ወንጌል ጋር በመስማማት፥ መግደላዊት ማርያም መጀመሪያ ክርስቶስን ያገኘችው እንደ ነበረች ያስረዳል። እንደ ሉቃስ፥ ሁለት ሰዎች በኤማሁስ መንገድ ከክርስቶስ ጋር እንደ ተገናኙ ያስረዳል። እንደ ዮሐንስ፥ ክርስቶስ ከአሥራ አንዱ ጋር እንደ ተገናኘና አንዳንዶች እንደ ቶማስ እንደተጠራጠሩት ይገልጻል።

ስለ ታላቁ ተልእኮ የሚናገረውም የማርቆስ ምንባብ በሉቃ ወንጌላት ውስጥ የተጠቀሱት እውነቶች ውህደት ይመስላል። ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ በዓለም ሁሉ ወንጌልን እንዲሰብኩ አዝዟቸዋል። በክርስቶስ ያመኑ ደኅንነትን ሲያገኙ፥ ለማመን ያልፈለጉት ግን ተፈርዶባቸዋል።

ጸሐፊው በተጨማሪም ወንጌሉ በሚስፋፋበት ጊዜ ተአምራት (ምልክቶች) እንደሚታዩ ገልጾአል። (<u>ማስታወሻ</u>፡– ይህ እያንዳንዱ ክርስቲያን ይህንን ሁሉ እንደሚያደርግ ሳይሆን፥ ምልክቶቹ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደሚፈጸሙ የሚያሳይ መሆኑን አስተውል።)

ሀ. በክርስቶስ ስም አጋንንትን ማስወጣት

ለ. በአዲስ ልሳናት መናገር

ሐ. እባቦችን መያዝ። (ምናልባትም ይህ ጳውሎስ እባብን ከያዘበት ታሪክ የተወሰደ ይሆናል። የሐዋ. 28፡3)

መ. መርዝ ጠጥቶ አለመሞት። ይህንን በተመለከተ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ምንም መረጃ የለም።

ሠ. በበሽተኞች ላይ እጅ በመጫን መፈወስ።

በእነዚህ ጥቅሶች ላይ ብቻ ተመርኩዘን እምነታችንን እንዳንመሠርት መጠንቀቅ አለብን። ከእነዚህ ነገሮች ውስጥ አብዛኞቹ በቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጸሙ ሲሆን፥ ዛሬም እንኳ እየተፈጸሙ ነው። ነገር ግን ይህ ጥቅስ በራሱ ሁሉም ክርስቲያኖች በልሳን ይናገራሉ ብሎ ለማስተማር ጥቅም ላይ መዋል የለበትም። እባብን ስለመያዝና መርዝ ስለመጠጣት የቀረበው ትምህርት በሌላ ቦታ ስላልተደገመ፥ ክርስቲያኖች መንፈሳዊነታቸውን ለማሳየት መርዛማ እባቦችን እንዲይዙ ወይም መርዛማ መጠጥ እንዲጠጡ ማበረታታት ጥበብ የጎደለው ድርጊት ነው። በአገልግሎታቸው እነዚህን ድርጊቶች የሚፈጽሙ ጥቂት ክርስቲያኖች አሉ፥ ከዚህም የተነሣ ብዙ ሰዎች ይሞታሉ።

ጸሐፊው ሌሎች የአዲስ ኪዳን ትምህርቶችንም እንደ ማጠቃለያ አድርጎ ያቀርባል። ኢየሱስ ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ፥ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ወዳለ ከፍ ያለ የክብርና የሥልጣን ስፍራ (በቀደመው ዓለም በነበረው የሥልጣን ተዋረድ ሁለተኛው ስፍራ) ሄደ። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንደሚያሳየው፥ ሐዋርያት የኢየሱስን ታሪክ ለሌሎች ነገሩ፥ የኢየሱስንም አገልግሎት በሽተኞችን በመፈወስ፥ አጋንንትን በማውጣት፥ ወዘተ... ቀጠሉ።

አራተኛ ቀን፥ የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ከሳምንታዊ ስብሰባ ላይ የመወያያ ጥያቄዎቹን ተመልከት።

ሳምንታዊ ስብሰባ

ማስታወሻ፥- በመጀመሪያው ሳምንት የተጠቀሰውን የስብሰባ ሥርዓት ተከተል።

የመወያያ ጥያቄዎች፥-

1. ሀ) ከማርቆስ ወንጌል ውስጥ ስለ ክርስቲያኖች እና ክፋትና ሰይጣን ግንኙነት ልንማረው የምንችለው ምንድን ነው? ለ) የሰይጣንን ኃይል በግልጽ ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ። ሐ) ብዙ ክርስቲያኖች ሰይጣንን፥ ቡዳን፥ እርግማንን፥ ወዘተ... የሚፈሩት ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? መ) እነዚህ ሰዎች እንዳይፈሩ ለማበረታታት የምትጠቀምባቸው በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙ እውነቶች ምን ምን ናቸው? ሠ) ሰዎች በኢየሱስስስ ስም የሚሉት፥ ወይም ሲጸልዩ የሚጮሁት፥ ወይም የኢየሱስን ስም የሚደጋግሙት ለምንድን ነው? ረ) እነዚህ ሰዎች ይህን የሚያደርጉበት ምክንያቱ የኢየሱስን ስም በተሳሳተ መንገድ ስለተረዱት ነው ብለህ ታምናለህ? መልስህን አብራራ።

1. ሀ) ኢየሱስ ሰዎችን ለቤተ ክርስቲያን መሪነት ያሠለጥን የነበረው እንዴት ነበር? ለ) መሪዎች ብዙ ጊዜ ሥራው ብዙ ሆኖ ሳለ ረዳቶች ግን በቂ እንዳልሆኑ ያጉረመርማሉ። ይህንን ችግር እንዴት መፍታት እንደምንችል ከኢየሱስ አገልግሎት የምንማረው ምንድን ነው? ሐ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላለው ሥራ ሠራተኞቹ ጥቂት የሆኑት ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? መ) ትልቁ ችግር የትኛው ነው ብለህ ታስባለህ፥ በቂ ሠራተኞች አለመኖራቸው፥ ወይስ ትክክለኛው ባህሪ ያላቸው በቂ ሠራተኞች አለመኖራቸው፥ ወይስ የሠለጠኑና ስጦታ ያላቸው ሰዎች ከፍርሐትና ከቅንዓት የተነሣ እንዳይሠሩ መደረጋቸው? መልስህን አብራራ።

2. ሀ) ኢየሱስ ሀብታሙን ወጣት ሰው ለመቀበል ያልፈለገው ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? ለ) ሰዎች ኢየሱስን መከተል ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲረዱ በኢየሱስ ማመንን የበለጠ ከበድ አድርጎ መናገር የሚያስፈልግባቸው ጊዜያት አሉ ብለህ ታስባለህ? ሐ) ሰዎች ክርስቲያን በሚሆኑበት ጊዜ አስፈላጊ ናቸው ብለው የሚያስቧቸውንና ሊተዉአቸውም ሆነ ስለ እነርሱ ያላቸውን ግንዛቤ ለመቀየር የሚቸገሩባቸውን ነገሮች በዝርዝር ጻፍ። መ) እኛ ክርስቲያኖች

በኢየሱስና በቃሉ ማፈራችንን የምናሳይባቸው መንገዶች ምን ምንድን ናቸው? ሠ) የመስቀሉን መንገድ መከተል አንተን እንዴት አድርጎ እንደለወጠህ ግለጽ።

4. ሀ) ሐዋርያት ስለ መሪነት ያላቸውን የተሳሳተ አስተሳሰብ በተደጋጋሚ ያሳዩት እንዴት ነበር? ለ) ኢየሱስ መሪነት በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ምን ይመስላል አለ? ሐ) ሽማግሌዎችን ለተገቢው የቤተ ክርስቲያን አመራር እንዴት አድርገን ልናዘጋጃቸው እንችላለን?

5. ሀ) የኢየሱስ ወደ ምድር የመምጣቱ ቀዳሚ ዓላማ ምን እንደሆነ ነው የማርቆስ ወንጌል የሚያሳየን? ለ) ሌሎች ተከታይ ዓላማዎቹ ምንድን ናቸው? ሐ) ለሕይወት የሚኖረን ግልጽ ዓላማ በማናቸውም ባለንባቸው አገልግሎቶች ውስጥ የሚመራን እንዴት ነው? ሐ) እግዚአብሔር ለሕይወትህ ምን ዓይነት ትላልቅ ዓላማዎች አሉት ብለህ ታስባለህ?

ትምህርት አሥራ አንድ

የመጀመሪያ ቀን የሉቃስ መግቢያ

አስፋው የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነበር። አንድ ቀን መምህሩ፥ «እናንተ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስ በሮማውያን የተገደለ ጥሩ ሰው እንደ ነበረ እንጂ አምላክ እንዳልነበረ ማወቅ አለባችሁ። ሌላው ነገር ሁሉ ሰዎች የጻፉት ነው። ስለ ኢየሱስ ተአምራት፣ ስለ አምላክነቱና ስለ ትንሣኤው የሚነገረው ሁሉ፥ የጥንት ተከታዮቹ በዚህ አስቸጋሪ ዓለም ውስጥ መጽናኛ እንዲሆንላቸው የተናገሩትና የጻፉት ታሪክ ነው» ሲል ተናገረ።

1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ያመንነው ነገር ሁሉ በአፈ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ቢሆን ኖሮ እምነታችን ምን በሆነ ነበር? ኢየሱስ ክርስቶስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጻፈው መሠረት እንደነበረና ስለ እርሱ የሚናገሩ ታሪኮች እውነት መሆናቸውን ማወቁ ለምን ይጠቅማል? ለ) 1ኛ ቆሮ. 15፡12-19 አንብብ። ጳውሎስ ኢየሱስ ከሞት ካልተነሣ የክርስትና እምነት ምንድን ነው ይላል? ሐ) ሉቃስ 1፡1-4 አንብብ። ሉቃስ በወንጌሉ ውስጥ የጠቀሳቸው ታሪኮች፥ እውነት እንጂ አፈ ታሪክ አለመሆናቸውን የሚያሳይ ምን ነገር ተናገረ?

ኢየሱስ ክርስቶስ ከ2,000 ዓመታት በፊት የኖረ እውነተኛ አምላክና እውነተኛ ሰው እንደሆነ በትክክል ማወቁ አስፈላጊ አይደለም ብለው የሚያስቡ፥ አንዳንድ ክርስቲያኖች አሉ። በእርሱ ካመንንና ስለ እርሱ የሚናገሩ ታሪኮች የሚያበረታቱን እስከ ሆኑ ድረስ፣ እነዚያ ታሪኮች በሰዎች የተጻፉ ቢሆኑም እንኳ አሳሳቢ አይሆንም ብለው ያስባሉ። ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ ከላይ እንደ ምሳሌ የተጠቀሰው የዩኒቨርስቲ መምህር ያቀረበውን ዓይነት አሳብ ቢሰማሙበትም፥ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ይሆን ወይ? የሚለው ጥያቄ አያስጨንቃቸውም። «ይህ ምሑራን የሚያቀርቡት ክርክር ነው።--- እኛ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየዘመርን ለመደሰት እንፈልጋለን። ጥሩ ስሜትም ይፈጥርልናል» ብለው ይናገራሉ።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ከመሆኑም በላይ ፈቃዱንም የሚገልጽ እውነተኛ መጽሐፍ እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል። መጽሐፍ ቅዱስን የምንጠራጠር፥ ዐበይት ስሕተቶችና በሰዎች የተጻፉ ታሪኮች ያሉበት መጽሐፍ እንደሆነ አድርገን የምናስብ ከሆን፣ እምነታችን የተመሠረተው ባለማስተዋል ላይ ነው ማለት ነው። ይህን የምናደርግ ከሆነ ከሌሎች የዓለም ሃይማኖቶች ከሚባሉት በምንም አኳኋን እንደማንለይ መረዳት ይኖርብናል።

ከልብ ማወቅ ያለብን ክርስትና ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ ብቸኛ ሃይማኖት መሆኑን ነው። ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸው አሳብ ሁሉ እውነት እንደሆነና ሰዎች ከአእምሮአቸው አፍልቀው ያልጻፉት መሆኑን ያምናሉ። እምነታችን የተመሠረተው ተአምራትን በሠራውና ወደ እግዚአብሔር የሚወስደውን መንገድ ባስተማረው፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው። ይህ ኢየሱስም በመስቀል ላይ ሞቶአል፥ ተቀብሯል፥ ከሙታንም ተነሥቷል። ከእነዚህ ነገሮች አንዱም እንኳ ልብ ወለድ ቢሆን፥ እምነታችን ስሜታዊ ብቻ በሆነ ነበር። ባዶ ከበሮ ከፍተኛ ድምፅ እንደሚሰጥ፥ እኛም ጮክ ብለን ልናመልክ ብንችልም፣ ነገሩ ባዶ አየር ከመሆን አያልፍም።

በየዘመኑ የተነሡ በክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች ስለ እርሱ የሚናገሩ ታሪኮች በተለይም ከሞት መነሣቱ እውነት እንዳልሆነ ላይንሳዊ ማረጋገጫ ለማቅረብ ሲሞክሩ ቆይተዋል። ከጥቂት ዓመታት በፊት ማልከም ማግሪጅ የተባለ የብሪታኒያ ሪፖርተር ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት እንዳልተነሣ ለማረጋገጥ ሞክሮ ነበር። ለብዙ ወራት በጥንቃቄ ሲያጠና ቆይቶ፥ የክርስቶስ ትንሣኤ እውነት መሆኑን ለማመን በመገደዱ ጠንካራ ክርስቲያን ለመሆን በቅቷል። ክርስትና ትርጉም የሚሰጠው ተአምራትን ያደረገ፣ ስለ እግዚአብሔር ያስተማረ፣ የሞተና ከሞት የተነሣ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚባል ሰው እንዳለ ስናውቅ ብቻ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ የጥንት ደቀ መዛሙርት ለምን ብለው ለዚህ እምነት ይሠዉ ነበር? ደግሞም ታሪኩ ውሸት ቢሆን ኖሮ ለዚህ እምነት ከመሞት መካዱ አይቀላቸውም ነበር? ጆሽ ማክዶውል የተባለ አንድ አሜሪካዊ የሕግ ባለሙያ እንዳመለከተው፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ የሚናገረው እውነት እንደሆነ አምኖ ከመቀበል ውጭ ለክርስትና ሌላ አመክንዮአዊ ትንታኔ ማቅረብ አይቻልም። ክርስትና ለሰዎች ጥሩ ስሜት በሚሰጡ አፈ ታሪኮች ላይ የተመሠረተ ሃይማኖት አይደለም። ክርስትና በጽኑ ታሪካዊ እውነቶች ላይ የተመሠረተ ሃይማኖት ነው፣ ተምረናል የሚሉትና ነገሩንም ተረት ተረት ነው የሚሉ ሰዎች የክርስቶስን ታሪክ በሳይንሳዊ መንገድ ለማብራራት አልሞከሩም። ስለሆነም፣ ስለ እምነታችን የምናፍርበት ወይም ሳይንሳዊና ታሪካዊ አይደለም ብለን የምንሸማቀቅበት ምክንያት የለም!

የሉቃስ ወንጌል የተጻፈው ሉቃስ በተባለ ጥንታዊ የታሪክ ምሑር ነው። ሉቃስ የእርሱም ሆነ የሌሎች ክርስቲያኖች እምነት በፈጠራ ታሪክ ላይ እንዲመሠረት አልፈለገም። እርሱም ከክርስቶስ ሕይወት መጀመሪያ አንሥቶ ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ መርምሮ እንደጻፈ ገልጾአል። ዓላማውም

ቀደም ሲል የተነገሩት አሳቦች እውነት መሆናቸውን ማረጋገጥ ነበር። አንድ የታሪክ ጸሐፊ ኢየሱስ በሞተበት የመጀመሪያዎቹ ሠላሳ አምስት ዓመታት ክልል ውስጥ ታሪኩን የሚያረጋግጡ በርካታ የዓይን ምስክሮች ባሉበት ዘመን ከጻፈ፥ እርሱም ሆነ ሌሎች የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ስለ ክርስቶስ የሚነግሩንን አምኖ ለመቀበል ፍጹም ድፍረት ይኖረናል። ታሪኩ እውነት ባይሆን ኖሮ፥ በዚያን ዘመን የነበሩት ሰዎች ይቃወሙት እንደነበር አይጠረጠርም።

2ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ስለ ሉቃስ የተጻፈውን አንብብ። ስለ መጽሐፉ ደራሲና ስለ ሌሎች ጠቃሚ ጉዳዮች የቀረበውን አሳብ ጠቅለል አድርገህ ጻፍ። ለ) ቆላ. 4፡14፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡11፤ ፊል. 24 አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች ስለ ሉቃስ ምን ያስተምሩናል? ሐ) የሐዋ. 16፡11-13፤ 20፡6-7፤ 21፡1-6፤ 28፡16 አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች ስለ ደራሲውና ከጳውሎስ ጋር ስላሉት ተግባራት ምን ያሳዩናል?

የሉቃስ መጽሐፍ ደራሲ

ምንም እንኳ «የሉቃስ ወንጌል» የሚለው ርእስ የመጀመሪያው ቅጂ አካል ባይሆንም፥ መጽሐፉ ከተጻፈ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ርእስ በመሆን ሊያገለግል ችሏል። ይህም የሆነው የሉቃስን ወንጌል ከሌሎች ወንጌላት ለመለየት ሲባል ነው። ይህ ደግሞ ገና ከጥንት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጀምሮ ሉቃስ ይህንን ወንጌል እንደ ጻፈው የሚታመን መሆኑን ያስረዳል። የጳውሎስ የወንጌል አገልግሎት ባልደረባ የነበረው ሉቃስ፥ የዚህ ወንጌል ደራሲ መሆኑን ሁሉም የጥንት የቤተ ክርስቲያን አባቶች በአንድ ድምፅ ይስማሙበታል። ምሑራን ሉቃስ የዚህ ወንጌል ጸሐፊ መሆኑን መጠራጠር የጀመሩት ባለፉት 100 ዓመታት ውስጥ ብቻ ነው። እነዚህ ምሑራን ጥርጣሬያቸውን ያቀረቡት ከሉቃስ ዘመን በኋላ ስለ ተነሡት የቤተ ክርስቲያን ችግሮች የሚዘግቡ አሳቦች በመጽሐፉ ውስጥ እንደሚገኙ በመግለጽ ነበር። ይህም ሆኖ ሉቃስ የዚህ ወንጌል ደራሲ አለመሆኑን የሚያሳይ ጠንካራ መረጃ አልተገኘም።

እንደ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ባለታሪኮች ሁሉ ስለ ሉቃስም ያለን መረጃ የተወሰነ ነው። ከሥነ ቱ የጳውሎስ መልእክቶች እንደምንረዳው፤ ሉቃስ በሙያው ሐኪም የነበረ ሲሆን፤ የጳውሎስ የቅርብ ጓደኛና የሥራ ባልደረባ ነበር። ሉቃስ ሌሎች ስደትን ፈርተው ገሸሽ ባሉ ጊዜ ከጳውሎስ ያልተለየ ሰው ነበር። ከዚህ ውጭ ስለ ሉቃስ የምናውቃቸውን ነገሮች የምናገኘው ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ነው።

ምንም እንኳ ሉቃስና የሐዋርያት ሥራ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ሁለት የተለያዩ መጻሕፍት የነበሩ ቢሆኑም፤ ሉቃስና የሐዋርያት ሥራ ቀድሞ ሁለት ዐበይት ክፍሎች ባሉት አንድ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቃለለው እንደ ነበር ብዙ ምሑራን ይስማማሉ። ክፍል አንድ ስለ ኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት የሚናገር ሲሆን፤ ክፍል ሁለት ደግሞ የክርስቶስ አገልግሎት እንዴት በሮም ግዛት ውስጥ እንደ ተስፋፋ ያስረዳል። የሐዋርያት ሥራን በጥንቃቄ ስናነብ በሁለተኛው የጳውሎስ የወንጌል ጉዞ ወቅት የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ደራሲ ከመቅጽበት የታሪኩ አካል ሆኖ እናገኛዋለን። ታሪኩ

«እነርሱ» እያለ ሲናገር ቆይቶ «እኛ» እያለ መተረክ ይጀምራል። ከጢሮአዳ ጀምሮ ሉቃስ ከጳውሎስና ከሲላስ ጋር አብሮ ይሠራ ነበር። ጳውሎስና ሲላስ ጉዞአቸውን ሲቀጥሉ እርሱ አብሮአቸው አልቀጠለም፣ ፊልጵስዩስ ላይ የቀረ ይመስላል። እግዚአብሔር በጳውሎስ አማካይነት ሉቃስን በጢሮአዳ ወደ ክርስቶስ መርቶት ይሁን ወይም ቀደም ሲል ክርስቲያን ይሁን የምናውቀው ነገር የለም። ከፊልጵስዩስ በኋላ አሁንም ታሪኩ ወደ «እነርሱ» ይቀየራል። ነገር ግን በሦስተኛው የጳውሎስ የወንጌል ጉዞ ፍጻሜ ወቅት፥ ሉቃስ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዝ አብሮት ነበር። ጳውሎስ በኢየሩሳሌምና በቂሣሪያ በታሰረባቸው አራት ዓመታት ውስጥ፥ ሉቃስ አብሮት ሳይለያነብት አልቀረም። ወደ ሮምም አብሮት የሄደ ይመስላል። በእነዚያ አራት ዓመታት ሉቃስ የኢየሱስን እናት ማርያምን፣ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያትና ሌሎች ኢየሱስ ሕይወታቸውን የለወጠላቸውንና የጳለስቲና ነዋሪዎችን ለማነጋገር መረጃ ለመሰብሰብ ጥሩ ዕድል አግኝቷል። ጳውሎስ ሮም በእስር ቤት ሆኖ የቆላስይስንና የፊልሞናን መልእክቶች በሚጽፍበት ጊዜ፥ ሉቃስ አብሮት ነበር። ከብዙ ዓመታት በኋላ ጳውሎስ ሊገደል በተቃረበበት ጊዜም ሉቃስ አብሮት ነበር።

ሉቃስ አይሁዳዊ አልነበረም። ይህም አንድን ሙሉ መጽሐፍ የጻፈ ብቸኛ አሕዛብ ያደርገዋል። የት ተወልዶ እንዳደገ አናውቅም። የምዕራብ ቱርክ ሰው ቢሆንም፥ በአንጾኪያ አካባቢ እንዳደገ የሚያስረዳ መረጃ አለ። ሐኪም እንደ መሆኑ፣ ሉቃስ የግሪክን ባህል እንደ ተማረ ምንም አያጠራጥርም። በተጨማሪም ሉቃስ ጥሩ የታሪክ ጸሐፊ ነበር። ምንም እንኳ ኢየሱስን በዓይኑ ባያየውም፣ ሉቃስ እንደ አንድ የታሪክ ጸሐፊ ስላመነበት ስለ ክርስቶስ ጥንቃቄ የተሞላበትን ጥናት አድርጓል። እርሱ ስደትና ሞትን መቀበል ካለበት ጽናቱ በተራ ወሬ ላይ ሳይሆን በእውነተኛ መረጃ ላይ እንዲደገፍ ፈልጎ ነበር። ሉቃስ ይህንኑ መረጃ ለማግኘት የተጠቀመባቸውን መንገዶች ይዘረዝርልናል። <u>አንደኛው</u>፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገሩና በጽሑፍ የሰፈሩ መዛግብትን አገላብጧል። ምናልባትም ከእነዚህ መዛግብት መካከል የማቴዎስና የማርቆስ ወንጌላት ይገኙበት ይሆናል። <u>ሁለተኛው</u>፣ የዓይን ምስክሮችንና የተከበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ቃለ መጠይቅ አድርጓል። ለምሳሌ፣ ሉቃስ የኢየሱስ እናት ከሆነችው ከማርያም ጋር በመነጋገሩ ምክንያት፥ ታሪኳን ብቻ ሳይሆን በልቧም ውስጥ ስለነበረው ነገር ገልጾአል (ሉቃስ 2፡19)። ሁሉንም መረጃ ከሰበሰበና ታሪኮቹን ፈር ካስያዘ በኋላ፣ ሉቃስ ስለ ክርስቶስ በሚጽፈው መጽሐፍ ውስጥ የትኞቹ መካተት እንዳለባቸው ወሰነ። እንደ ሌሎቹ የወንጌላት ጸሐፊዎች ሁሉ ታሪክን ብቻ አልጻፈም። ይልቁንም ስለ ክርስቶስ ለማስተማር ፈልጎ ነበር። ይህንንም ያደረገው ሰዎች ለእምነታቸው ጽኑ መሠረት እንዲኖራቸውና ክርስቶስን መከተል ማለት ምን ማለት እንደሆነ እርሱን እንዲያውቁ ለማድረግ ነበር። ሉቃስ መረጃውን በሚሰበስብበትና በሚጽፍበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ይመራው ነበር፣ ዛሬ በእኛችን ያለው ወንጌል በለው የተጻፈ ታሪክ ብቻ ሳይሆን፣ መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዳችን እንድናውቅ፣ እንድናምንና ከሕይወታችን ጋር እንድናዛምድ የሚፈልገውን እውነት ሁሉ እንዲጽፍ አድርጎታል።

ሉቃስ ወንጌሉን የጻፈው ለማን ነው?

3ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ሉቃስ 1፡1–4 እና የሐዋ. 1፡1–2 አንብብ። ሉቃስ ወንጌሉን ለማን እንደ ጻፈ ነው የገለጸው? ለ) የሐዋ. 28፡30–31 አንብብ። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰው የመጨረሻው ክስተት ምንድን ነው?

በሉቃስም ሆነ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ደራሲው መጽሐፉን የጻፈው፥ «ቴዎፍሎስ» ለሚባል ሰው ነው። «ቴዎፍሎስ» ማለት «የእግዚአብሔር ወዳጅ» ማለት ስለሆነ አንዳንድ ሰዎች ይህ «የእግዚአብሔር ወዳጅ ለሆኑ ክርስቲያኖች» የተጻፈ ነው ብለው ያስባሉ። ይህ ግን ትክክል አይመስልም። ቴዎፍሎስ ሉቃስ በደንብ የሚያውቀው ከአሕዛብ ወገን የሆነ ሰው ሳይሆን አይቀርም። አንዳንድ ምሑራን ቴዎፍሎስ ሉቃስ ወደ ክርስቶስ ያመጣው አማኝ ክርስቲያን ሳይሆን እንደማይቀር ያስባሉ። ሉቃስ «ክቡር ቴዎፍሎስ ሆይ» ብሎ ስለሚጠራውና ይህም የሮማውያን የማዕረግ ስም ስለሆነ፣ ቴዎፍሎስ አሕዛብ ምናልባትም ሮማዊ ሳይሆን አይቀርም ይላሉ። ምናልባትም ሀብታም የሮም ባለሥልጣን ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ምሑራን ቴዎፍሎስ ለሉቃስ ገንዘብ በመስጠት የሉቃስ ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ ታትሞ በዓለም እንዲሰራጭ እርዳታ አድርጓል በማለት ይናገራሉ። ይህ በጥንት ዘመን የተለመደ አሠራር ነበር። አንዳንድ ምሑራን ሉቃስ ቴዎፍሎስን ለማሳመን ወይም አዲስ ክርስቲያን ስለ ማድረጉና ክርስቶስን ስለ መከተል ለማስተማር ሲል መጽሐፉን እንደ ጻፈ ይገምታሉ።

ቴዎፍሎስ የሉቃስ ወንጌል የመጀመሪያው ተቀባይ ቢሆንም፣ ሉቃስ መጽሐፉ በብዙ ሰዎች እንደሚነበብ ያውቅ ነበር። ሉቃስ መጽሐፉን የጻፈው የአይሁድን ባሕል ለማያውቁ አሕዛብ ነው። እርሱም በመጽሐፉ ውስጥ ወንጌል አሕዛብን ጨምሮ ለሰዎች ሁሉ መሰበክ አለበት በሚለው እውነት ላይ ያተኩራል። አንዳንድ ምሑራን ሉቃስ የቀድሞ አምልኮአቸውን ትተው እግዚአብሔርን በመፍራት ለሚኖሩ አሕዛብ እንደ ጻፈ ያስባሉ። እነዚህ አሕዛብ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተገለጠውን አንድ አምላክ ለመቀበል ፈቃደኞች ቢሆኑም፥ ተገርዘው አይሁድ ለመሆን ግን አልፈለጉም ነበር (የሐዋ. 13፡16)። ምንም እንኳ የሉቃስ ወንጌል ክርስቲያኖችን ለማስተማር የተጻፈ ቢሆንም፣ ክርስትና በአፈ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ነው ለሚለው ክስም መልስ ይሰጣል። አንዳንድ ምሑራን ሉቃስ ክርስትና ሕጋዊ ሃይማኖት ሊሆን የሚገባው እንጂ፥ ስጋትን እንደሚያስከትል ተቆጥሮ መሰደድ እንደ ሌለበት ለአሕዛብ ለማሳየት የተጻፈ ነው ይላሉ።

ምንም እንኳ ጳውሎስ ከማንም በላይ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙ መጻሕፍትን ቢጽፍም፣ በገጽ ብዛት ግን ሉቃስን የሚወዳደር የለም። የሉቃስ ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ በአንድነት ቢደመሩ የጠቅላላው አዲስ ኪዳን ሲሶ ይሆናሉ። የሉቃስ ወንጌል በአዲስ ኪዳን ውስጥ በርዝመቱ ተወዳዳሪ የሌለው ሲሆን፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ከሌሎች ሁሉ ጠለቅ ያለ መልእክትን ያስተላልፋል።

ወንጌሉ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ

የሉቃስ ወንጌል መቼ እንደ ተጻፈ ለመገመት የሌሎቹን ወንጌላትና የሐዋርያት ሥራን ቅደም ተከተል መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፤ ሉቃስ የማርቆስን ወንጌል ከምንጮቹ እንደ አንዱ አድርጎ ተጠቅሞ ይሆን? የሐዋርያት ሥራ የተጻፈው መቼ ነው? በሐዋርያት ሥራ 1፡1 ላይ ሉቃስ ስለ መጀመሪያው መጽሐፉ ማለትም ስለ ሉቃስ ወንጌል ስለሚጠቅስ፤ የሐዋርያት ሥራ ከሉቃስ ወንጌል በኋላ እንደ ተጻፈ አያጠራጥርም። የሐዋርያት ሥራ የሚያበቃው ጳውሎስ ከሮም ወጎኒ ቤት ይወጣል ተብሎ በሚጠበቅበት ወቅት ነው። ሉቃስ ስለ ጳውሎስና ስለ አሟቱ ምንም ዓይነት ተጨማሪ አሳብ ስላልጻፈ፥ የሐዋርያት ሥራን ጽፎ የጨረሰው ጳውሎስ ከእስር ቤት ከመውጣቱና እንደገና ከመታሰሩ በፊት ሳይሆን አይቀርም። ስለሆነም የሐዋርያት ሥራ በ63 እና 64 ዓ.ም. መካከል እንደ ተጻፈ ይገመታል። ይህም የሉቃስ ወንጌል ከዚያ በፊት እንደ ተጻፈ ያመለክታል። ስለሆነም ሉቃስ ወንጌሉን ከ59–63 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ እንዳጠናቀቀ ይገመታል።

ሉቃስ የማርቆስን ወንጌል እንደ ምንጭ ተጠቅሟል የሚሉ ምሑራን፥ መጽሐፉ የተጻፈበትን ዘመን ወደ 70 ዓ.ም. ያመጡታል። እነዚህ ወገኖች እንደሚሉት፤ ይህን ወንጌል እንደ አንዱ ምንጭ አድርጎ ሉቃስ ከመጠቀሙ በፊት፥ የማርቆስ ወንጌል ተጽፎ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እስኪሰራጭ ድረስ ጊዜ ሳይወሰድ እንዳልቀረ ይናገራሉ። ነገር ግን የማርቆስ ወንጌል ቀደም ብሎ ተጽፎ ተቀባይነትን ካገኙት ወንጌላት እንደ አንዱ ሆኖ ካገለገለባት በኋላ፥ በሮም የራሱን መጽሐፍ ጽፎ ይሆናል ብለው ይገምታሉ። ሉቃስ ከ63 ዓ.ም. በኋላ ጽፎታል የሚለው ግምት ግን ይህን ያህል ተቀባይነት አላገኘም።

ሉቃስ ወንጌሉን የጻፈው በየት ስፍራ እንደሆነ በውል አይታወቅም። በአማራጭነት የሚጠቀሱት አገሮች ፤ 1) ሉቃስ ብዙ ጊዜ ያሳለፈባት ፊልጵስዩስ፤ 2) ጳውሎስ ለሁለት ዓመት የታሰረባት ቂሣርያ፥ ወይም 3) ጳውሎስ ታስሮ የቆየባት ሮም ናቸው። ከእነዚህ በአንዱ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል። ሆኖም ሉቃስ ወንጌሉን የጻፈው ቂሣርያ ወይም ሮም በቆየባቸው ጊዜያት ይመስላል።

4ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ ሊያውቋቸውና ከሕይወታቸው ጋር ሊያዛምዱቸው የሚገቧቸው እውነቶች ምንድን ናቸው? ለ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከእነዚህ እውነቶች አብዛኞቹ የሚገኙት የት ነው?

የሉቃስ መጽሐፍ ዓላማ

አዲስ ኪዳን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶች ላይ በማተኮር፤ ስለ ማንነቱ፤ ስላስከተላቸው ለውጦች፤ በሕይወታችን ውስጥ እንዴት ልናስከብረው እንደሚገባን ያብራራል። መልእክቶች ሁሉ እውነትን ተግባራዊ የሚያደርጉት ከኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት አንጻር ነው። ለመሆኑ የጥንት ክርስቲያኖች እምነታቸውንና ተግባራቸውን የመሠረቱት በምን ላይ ነበር? በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ላይ ነበር። እያንዳንዱ መልእክት ከግምት ውስጥ የሚያስገቡት ነገር አለ። ይኸውም እያንዳንዱ ክርስቲያን ስለ ኢየሱስ የሚናገሩትን ታሪኮችና ተከታዮቹም ሕይወታቸውን እንዴት መምራት

እንደሚገባቸው ያውቃል። መልእክቶች ኢየሱስ ማን እንደሆነ ይበለጥ ያብራራሉ። ክርስቲያኖች የክርስቶስን ትምህርት ራሳቸው ከሚገኙባቸው ሁኔታዎች ጋር ያዛምዱታል። መልእክቶች ስለ ኢየሱስ ፍጹም አዲስ ትምህርት አያስተምሩም። ነገር ግን ከወንጌላት ውስጥ ስለ ክርስቶስ ጥልቅ ጥናት የሚያደርጉ ክርስቲያኖች ብዙዎች አይደሉም። መልእክቶችን ማንበብ እንወዳለን። ይህም አንድ አባል የሚስቱን ባሕርይ ለማወቅ ከጓደኞቿ ጋር እንደሚናገር ማለት ነው። ነገር ግን ከራሷ ጋር በመነጋገር ስለ ባሕሪዋና ምን እንደሚያስፈልጋት እስካልተገነዘበ ድረስ፥ ሚስቱን በትክክል ሊያውቃት አይችልም። በዚሁ መሠረት ኢየሱስን እንደ ጳውሎስ ባሉት ሌሎች ሰዎች አማካይነት ልናውቅ አንችልም። ግን በወንጌላት ውስጥ እንደተገለጸው በቀጥታ ኢየሱስን መመልከት አለብን። ኢየሱስ የእምነታችን መሠረት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌላት ውስጥ የተገለጸበትን ሁኔታ እስካልተገነዘብን ድረስ በእምነታችን ልንጠነክር አንችልም።

ስለ ክርስቶስ የተለያዩ ታሪኮች ይነገሩ እንደነበር አይጠረጠርም። ከእነዚህም መካከል አንዳንዶቹ እውነት ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ግን ውሸትና የተጋነኑ ነበሩ። ስለሆነም፣ ሉቃስ እያንዳንዱ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖረው ፈልጓል። ሉቃስ ይህንን መጽሐፍ ሲጽፍ አያሌ ዓላማዎች ነበሩት፡—

1. ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ግልጽ ታሪካዊ ዘገባ ማቅረብ። ሉቃስ ሌሎችም ሰዎች የኢየሱስን ታሪክ እንደ ጻፉ ገልጾአል። ምናልባትም የማርቆስ ወንጌል መኖሩን ያውቅ ይሆናል። ሰዎች ከጻፉዋቸው ነገሮች አንዳንዶቹ ብቃት የጎደላቸው ወይም የተሳሳቱ ላይሆኑ ይችላሉ። ሌሎች የኢየሱስን ሕይወት ቅደም ተከተሉን በጠበቀ ሁኔታ አላቀረቡም ወይም በቂ መረጃ አልሰጡም ይሆናል። ወይም ሉቃስ እንደ ታሪክ ጸሐፊ ከታሪኮቹ በአንዳንዶቹ ላይ ብቁ የምርምር ሂደት እንደ ተካሄደ አላመነም ይሆናል። ታሪክ ጸሐፊው ሉቃስ፥ ለዘመናት ሁሉ የሚሆን ትክክለኛ የኢየሱስ ታሪክ መጻፍ እንዳለበት ተገንዝቦ ነበር። መንፈስ ቅዱስም ሉቃስ ተጨማሪ ወንጌል እንዲጽፍ ቀሰቀሰው።

2. ክርስቲያኖች ግንን እንዳመኑ እንዲያውቁ። ለዚህም ነው ለቴዎፍሎስና ለሌሎችም፣ «ይህንንም የማደርገው የተማርኸው ነገር እውነተኛ መሆኑን እንድታውቅ ነው» ሲል የገለጸው (ሉቃስ 1፡4)። የእምነታችን ጥንካሬ የሚለካው ያመንነውን ነገር ባወቅነው መጠን ነው። በስደት ጊዜ ታማኞች ሆነን እንድንጸና ከተፈለገ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እንደሆነና እርሱን መከተል ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ግልጽ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል።

5ኛ ጥያቄ፡— ሰዎች ክርስቶስን የሚክዱት በእርሱ ላይ ያላቸው እምነት ስላልጠነከረ ይሆን? መልስህን አብራራ።

የሉቃስ መጽሐፍ ልዩ ገጽታዎች

1. የሉቃስ ወንጌል ከወንጌላት ሁሉ የላቀ ሥነ ጽሑፋዊ ውበት አለው። መጽሐፉ የተጻፈው ጥልቅ የግሪክ ቋንቋ ከህሎት ባለው ሰው ነው።

2. ከሦስቱ ተመሳሳይ ወንጌላት መካከል ሉቃስ የተለየ ነው። የማቴዎስንና የማርቆስን አጠቃላይ ገጽታ ቢከተልም፣ ካቀረባቸው መረጃዎች መካከል 50 በመቶው ከማቴዎስና ማርቆስ የተለየ ነው።

3. ሉቃስ የታሪክ ባለሙያ እንደ መሆኑ መጠን፣ ሁኔታዎቹ የተፈጸሙበትን ትክክለኛ ጊዜ ይገልጻል። መጥምቁ ዮሐንስ መቼ አገልግሎቱን እንደ ጀመረ (ሉቃስ 3፡1-2)፣ የሮም ገዥዎች እነማን እንደሆኑና ሌሎችንም ነጥቦች ይገልጻል። ሉቃስ የክርስቶስን ሕይወት በግልጽ ታሪካዊ የጊዜ ቀመር ውስጥ አኑሮታል።

4. ሉቃስ ሌሎች ሰዎችንና መጻሕፍትን መረጃ አድርጎ እንደ ተጠቀመ ገልጾአል። ከእነዚህ መረጃዎች መካከል ማቴዎስና ማርቆስ ሊካተቱ ቢችሉም፣ ሌሎች እጅግ ብዙ የጽሑፍ መረጃዎችም ሳይኖሩ አይቀርም። መንፈስ ቅዱስ የትኞቹ የጽሑፍ መረጃዎች የመጽሐፍ ቅዱስ አካል መሆን እንዳለባቸው በጥንቃቄ መርጧል። ምክንያቱም ስለ ክርስቶስ የተነገሩ ታሪኮች ከሰው ወደ ሰው እየተላለፉ ሲሄዱ እውነተኝነት ሊጎድላቸው ይችላልና።

6ኛ ጥያቄ፡- ሉቃስ 2፡14፥32፥38 አንብብ። እነዚህ ምንባቦች የእግዚአብሔር የደኅንነት ዕቅድ ለሰዎች ሁሉ እንደሆነ የሚያስረዱት እንዴት ነው?

5. ሉቃስ፥ ወንጌሉ ሁሉን አቀፍ ባሕርይ እንዳለው በአጽንኦት ገልጾአል። ሉቃስ የኢየሱስን የዘር ሐረግ የጀመረው እንደ ማቴዎስ የአይሁዶች አባት ከነበረው ከአብርሃም ወይም ከዳዊት ሳይሆን፣ የመጀመሪያው ሰውና የሰው ልጆች ሁሉ አባት ከነበረው ከአዳም ነው (ሉቃስ 3፡38)። መላእክት የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት ሲያውጁ፥ መልካሙ የምሥራች ለሰዎች ሁሉ እንደሆነ ተናግረዋል (ሉቃስ 2፡14)። አይሁዳዊው ስምዖን ኢየሱስ የአሕዛብ ብርሃን እንደሆነ መስክሯል (ሉቃስ 2፡32)። ሉቃስ ወደ ብሉይ ኪዳን በማመልከት፥ አሕዛብን የእውነተኛው እምነት መገለጫዎች ማብራሪያ አድርጎ ጠቅሷቸዋል (ሉቃስ 4፡25-27፣ 11፡31-32)። ኢየሱስ በደጉ ሳምራዊ አማካይነት ፍቅር ምን እንደሆነ ገልጾአል (ሉቃስ 10፡30-37)።

6. ሉቃስ ከየትኞቹም የወንጌል ጸሐፊዎች በላይ ስለ ኢየሱስ የልጅነት ጊዜ ዝርዝር ጉዳዮችን አቅርቧል። ቅድስት ማርያምን በተመለከተ ስለ ድንግል መውለድ ይተርክልናል። በተጨማሪም መጥምቁ ዮሐንስ ተምሳራዊ በሆነ መንገድ እንደ ተወለደ፣ ኤልሳቤጥ ማርያምን እንደ ጎበኘች፣ እረኞች ሕጻኑን ኢየሱስን ለመጎብኘት እንደ መጡ፣ ኢየሱስ እንደ ተገረዘና ወደ ቤተ መቅደስ እንደ ተወሰደ፣ እንዲሁም በ12 ዓመት ዕድሜው በቤተ መቅደስ ውስጥ የሃይማኖት መሪዎችን እንዳስደነቃቸው ያስረዳል።

7ኛ ጥያቄ፡- ሉቃስ 8፡1-3፣ 15፡8-10፣ 7፡11-15 አንብብ። ኢየሱስ ለሴቶች ያለውን አክብሮት ያሳያው እንዴት ነበር?

7. ሉቃስ ከሌሎቹ ወንጌላት በላይ ሴቶች በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ የነበራቸውን ልዩ ድርሻ ገልጾአል። ማቴዎስና ማርቆስ በአንድነት ስለ ሴቶች 49 ጊዜ የጠቀሱ ሲሆን፣ ሉቃስ ብቻውን 43 ጊዜ ጠቅሷል። ኢየሱስ ለሴቶች የነበረው ግምት በዘመኑ ከነበሩት ሁሉ የተለየ ነበር። ሉቃስ ሴቶች

እንዴት ኢየሱስን ከሁሉም በተሻለ ሁኔታ ይረዱ እንደነበሩ ያስረዳል። ሕጻኑ ኢየሱስ ለሚያከናውነው ተግባር እግዚአብሔርን ያመሰገንችው ሴት ነበረች (ሉቃስ 2፡36–38)። ኢየሱስ ሴቶች የደቀ መዛሙርቱ ቡድን አባላት እንዲሆኑ ፈቅዱል። ዮሐና የተባለች ሴት የአንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ሚስት ነበረች (ሉቃስ 8፡1–3)። ኢየሱስ ከፈወሳት በኋላ የምኞት ኑሮዋን ትታ ከስፍራ ስፍራ የሚዞረውን የኢየሱስን ቡድን ተቀላቀለች። ኢየሱስን ከመውደዱና ከማክበርዋ የተነሣ ለአገልግሎቱ የገንዘብ ድጋፍ ታደርግ ነበር። ከሞተም በኋላ ተስፋ ቆርጣ ወደ ቤቷ ሳትመለስ፥ ከኢየሱስ መስቀል አጠገብ ቆይታለች። ከዚህም የተነሣ ባዶውን መቃብር ከተመለከቱት አንዱ ለመሆን በቅታለች። ኢየሱስ በሚናገራቸው ምሳሌዎች ውስጥ ሴቶችን ያካትት ነበር (ሉቃስ 13፡20–21፤ 15፡8–10)። ኢየሱስ ልጆቻቸውን ከሞት በማስነሣት (ሉቃስ 7፡11–15)፤ ንስሐቸውንና ፍቅራቸውን በማክበር (ሉቃስ 7፡36–50)፤ በመፈወስ (ሉቃስ 13፡10–13) እና በመሳሰሉት ለሴቶች ርኅራኄን አሳይቷል።

8. በሁለቱም መጽሐፎቹ ውስጥ ሉቃስ በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ላይ አጽንኦት ሰጥቷል። መንፈስ ቅዱስ ማርያም እንድትፀንስ አድርጓል። መጥምቁ ዮሐንስም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቷል (ሉቃስ 1፡15)። ሌሎች እንደ ኤልሳቤጥ (ሉቃስ 1፡41)፤ ዘካርያስ (ሉቃስ 1፡67) እና ስምዖን (ሉቃስ 2፡25–27) የመሳሰሉ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሊናገሩ ችለዋል። የኢየሱስ ሕይወት ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ አመራር ሥር ነበር። በተጠመቀ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላ በኋላ ወደ ምድረ በዳ ተወስዷል (ሉቃስ 4፡1)። ኢየሱስ በገሊላ ያከናወነው አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተደረገ ነበር (ሉቃስ 4፡14)። ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ደስታ ተሞልቶ ነበር (ሉቃስ 10፡21)። ኢየሱስ ለተከታዮቹ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንደሚሰጥ ቃል ገብቶላቸው ነበር (ሉቃስ 11፡13፤ 12፡12)።

9. ማቴዎስ ኢየሱስ የእስራኤል ንጉሥ መሆኑን ሲያመለክት፥ ማርቆስ ደግሞ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ባሪያ መሆኑን ያስረዳል። ሉቃስ ደግሞ በኢየሱስ ሰብአዊነት ላይ በማተኮር ፍጹም ሰው መሆኑን አመልክቷል።

10. ሉቃስ ሰዎች እግዚአብሔርን ያመሰገኑባቸውን መዝሙራት (ቅኔዎች) በመጽሐፉ ውስጥ አካትቷል። ኤልሳቤጥ (ሉቃስ 1፡39–45)፤ ማርያም (ሉቃስ 1፡46–55)፤ ዘካርያስ (ሉቃስ 1፡67–79)፤ መላእክት (ሉቃስ 2፡13–14) እና ስምዖን (ሉቃስ 2፡28–32) የዘመሯቸውን መዝሙሮች በሉቃስ ወንጌል ውስጥ እናገኛለን።

8ኛ ጥያቄ፡– ሉቃስ 3፡21፤ 5፡16፤ 6፡12፤ 28፤ 9፡28–29፤ 11፡1፤ 22፡40–46፤ 23፡34፤ 46 አንብብ። ኢየሱስ እንደ ጸለየ የተነገረባቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ዘርዝር።

---

11. ሉቃስ በኢየሱስ የጸሎት ሕይወት ላይ ትኩረት ሰጥቷል። እርሱም ሌሎች ያልጠቀሷቸውንና ኢየሱስ የጸለየባቸውን ሰባት ጊዜያት አመልክቷል። መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ የመጣው፥ ኢየሱስ እየጸለየ ባለበት ወቅት ነበር (ሉቃስ 3፡21)። ብዙውን ጊዜ ብቻውን ሆኖ ይጸልይ ነበር (ሉቃስ 5፡16)። ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ከመምረጡ በፊት ጸልዮአል (ሉቃስ

6፡12–13)። በጸለየበት ጊዜ መልኩ ተለውጦ ክብሩ ተገልጾአል (ሉቃስ 9፡29)። በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንኳ ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር ጸልዮአል (ሉቃስ 23፡34፤ 46)።

12. ሉቃስ፥ ከኢየሱስ ምሳሌዎች ብዙዎቹን በመጽሐፉ ውስጥ አካትቷል። ከ22 ምሳሌዎች መካከል 17ቱ የሚገኙት በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው።

9ኛ ጥያቄ፡– ሉቃስ 1፡53፤ 4፡18፤ 6፡20፤ 24፤ 12፡16–21፤ 6፡19–31 አንብብ። ኢየሱስ ለድሆችና ለራስ ወዳድ ባለጠጎች ስለነበረው አመለካከት እነዚህ ጥቅሶች ምንን ያስተምራሉ?

13. ሉቃስ፥ ኢየሱስ ለድሆች የነበረውን ፍቅር ገልጾአል። የኢየሱስ ቤተሰቦች ድሆች በመሆናቸው፥ ለድሆች የተፈቀደውን መሥዋዕት ለማቅረብ ተገድደው ነበር (ሉቃስ 2፡24)። ኢየሱስ አገልግሎቱን በጀመረ ጊዜ ሉቃስ ይህ ለድሆች ወንጌልን መስበክ እንደሆነ አመልክቷል (ሉቃስ 4፡18)። ሉቃስ ለድሆች የሚሰጠውን ይህንኑ ልዩ ትኩረት ድሆችን ብፁዓን ብሎ በመጥራት (ሉቃስ 6፡20)፤ እግዚአብሔር ለድሆች የሚያስፈልጋቸውን እንደሚሰጣቸው (ሉቃስ 1፡53–54) ገልጾአል፤ እንዲሁም የለማኙን ታሪክ በማቅረብ (ሉቃስ 16፡19–31) በግልጽ አሳይቷል። በአንጻሩም፤ ሉቃስ ለሀብታሞች ብዙ ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጣል። ማርያም ባለጠጎች ባዶ እጃቸውን እንደሚመለሱ ስትገልጽ (ሉቃስ 1፡53)፤ ኢየሱስ ለባለጠጎች ወዮላቸው ብሏል (ሉቃስ 6፡24)። ባለጠጎችን የሚቃወሙ አያሌ ምሳሌዎችም ቀርበዋል (ሉቃስ 12፡16–21፤ 16፡19–31)።

የሉቃስ መጽሐፍ አወቃቀር

የሉቃስ ወንጌል በአራት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል።

ሀ. የኢየሱስ ልደትና የልጅነት ጊዜ (ሉቃስ 1–2)

ለ. የኢየሱስ አገልግሎት በገሊላ (ሉቃስ 3፡1–9፡50)

ሐ. የኢየሱስ አገልግሎት ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ (ሉቃስ 9፡51–19፡27)

መ. የኢየሱስ አገልግሎት በኢየሩሳሌም (ሉቃስ 19፡28–24፡53)

የሉቃስ መጽሐፍ አስተዋጽኦ

1. የሉቃስ ወንጌል መግቢያ (ሉቃስ 1፡1–4)
2. ኢየሱስ በምድር ላይ ላለው አገልግሎት ያደረገው ዝግጅት (ሉቃስ 1፡5–4፡13)

ሀ. የመጥምቁ ዮሐንስና የኢየሱስ መወለድና የልጅነት ጊዜ (ሉቃስ 1፡5–2፡52)

ለ. የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት (ሉቃስ 3፡1–20)

ሐ. የኢየሱስ መጠመቅና በመንፈስ ቅዱስ መሞላት (ሉቃስ 3፡21–4፡13)

1. የኢየሱስ አገልግሎት በገሊላ (ሉቃስ 4፡14–9፡9)

ሀ. ኢየሱስ መልካሙን የምሥራች ዐወጀ (ሉቃስ 4፡14–5፡16)

ለ. ኢየሱስ ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ተጋጨ (ሉቃስ 5፡17–6፡11)

ሐ. ኢየሱስ ለድሆች መልካሙን የምሥራች ዐወጀ (ሉቃስ 6፡12–8፡3)

መ. ኢየሱስ መሢሕ መሆኑን ገለጠ (ሉቃስ 8፡4–9፡50)

2. ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ (ሉቃስ 9፡51–19፡28)

ሀ. ኢየሱስ በይሁዳ አገለገለ (ሉቃስ 9፡51–13፡21)

ለ. ኢየሱስ በጴሪያና አካባቢዋ አገለገለ (ሉቃስ 13፡22–19፡27)

3. የኢየሱስ የመጨረሻው አገልግሎት በኢየሩሳሌም (ሉቃስ 19፡28–24፡53)

ሀ. የኢየሱስ አገልግሎት ከስቅለቱ በፊት (ሉቃስ 19፡28–22፡46)

ለ. የኢየሱስ መያዝ፣ መመርመርና መሰቀል (ሉቃስ 22፡47–23፡56)

ሐ. የኢየሱስ ትንሣኤና ዕርገት (ሉቃስ 24)

ሁለተኛ ቀን — ሉቃስ 1–2

ደመራዝ የአንድ ዕውቅ ወንጌላዊ ልጅ ነበረች። እግዚአብሔር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ የጸሐፊነት ሥልጠና እንድታገኝ ረዳት። ከዚያም ለአንድ ነጋዴ ተቀጥራ ለመሥራት አሰበች። አንድ ቀን አንድ ከገጠሪቱ ኢትዮጵያ የመጣ ወንጌላዊ ለጋብቻ ጠየቃት። የወንጌላዊው ጥያቄ ደመራዝን አስከፋት። ሰውዬው የገጠር ወንጌላዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቀው በቅርቡ ነበር። ደመወዙ ትንሽ ስለሆነ ይጠቅሙኛል ብላ የምታስባቸውና የወርቅና የብር ስጦታዎች ሊያቀርብላት እንደማይችል ተገንዝባለች። ብሔሩም ቢሆን እርሷ ከምታከብራቸው ብሔሮች መካከል አልነበረም። ከሰውዬው ሁኔታ የሚስባት ምንም ነገር ስላልነበረ በፍጥነት አሉታዊ ምላሿን ሰጠችው። ውሎ ሲያድር ግን እግዚአብሔር በልቧ ውስጥ መሥራት ጀመረ። «ከእኔ በላይ ምቹ ሕይወት ትፈልጊያለሽ? ከትምህርትሽ በላይ እኔን ትወጅኛለሽ? ከክብርሽ በላይ እኔን ትወጅኛለሽ? ይህን ወንጌላዊ እንድታገቢው እፈልጋለሁ። ፈቃደኛ ነሽ?» ሲል እግዚአብሔር አፋጠጣት። ጓደኞቿን ስታማክር፣ «ድሃ ወንጌላዊ ለማግባት ማሰብሽ ራሱ ዕብደት ነው» ሲሉ መለሱላት። መጫወቻም አደረጓት። ወላጆቿም የማይመጥናትን ሰው ልታገባ ነው ብለው ስለተበሳጩ፥ ሁኔታው በጣም አናጋት።

10ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ደመራዝ ምን ማድረግ ያለባት ይመስልሃል? ለ) ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር እንድናደርግ የሚፈልጋቸው ነገሮች የተሻለ ደረጃ፣ ክብርና የተሻለ የሕይወት መንገድ ያመጡልናል ብለን የምናስበው እንዴት ነው?

አብዛኛውን ጊዜ ለራሳችንና ለልጆቻችንን ውሳኔ የምንሰጠው ራስ ወዳድና ዓለማዊ መመዘኛዎችን መሠረት አድርገን ነው። ስለዚህ የልባችንን መሻት ለመግለጽ ለልጆቻችን መልካሙን ሁሉ እንመኛለን። ስለዚህ ልጆቻችን ጥሩ ትምህርትና ጥሩ ሥራ እንዲያገኙ፣ ከሀብታም ወይም ከዝነኛ ቤተሰብ ጋር እንዲጋቡ እንፈልጋለን? ወይስ ትልቁ ፍላጎታችን ልጆቻችን በጌታ መንገድ ሲመላለሱ፣ ሲታዘዙትና የዓለምን ምኞት መጣል በሚያስፈልግበት ሁኔታ እንኳን እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ማየት ነው? የቤተ ክርስቲያን መሪ ልጆች አነስተኛ ደመወዝ በሚያስገኝ የወንጌላዊነት ሥራ ላይ ተሰማርተው እግዚአብሔርን የማያገለግሉት ለምንድን ነው?

ዛሬ እግዚአብሔር አንዲት ወጣት እጅግ ከባድ ውሳኔ እንድታደርግ እንዴት እንዳደረገ እንመለከታለን። ይሽውም በሰብአዊ ባሕል ባል ስታገባ የእርሱን ልጅ በማሕፀኗ ውስጥ እንድትሸከም አድርጓል። ይህች ወጣት የጓደኞቿን ሽሙጥ ታግሣ ፅንሱን በማሕፀንዋ ውስጥ ትሸከማለች? የወላጆቿን ቁጣም ለመታገሥ ፈቃደኛ ነበረች? እጮኛዋ መተጫጨታቸውን እንዲያፈርስ ፈቅዳለች? ከአምልኮ ቦታዋ ለመባረር ፈቃደኛ ሆናለች? ማርያም እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ስለ መረጠችና የዓለምን ውርደት ለመቀበል ስለ ፈቀደች እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። ይህች ወጣት በዓለም ሁሉ የታወቀች ለመሆን በቅታለች። እግዚአብሔርን ለመታዘዝና እርሱ በሚፈልገው መንገድ ለመኖር ስንወስን፣ ዓለም ልትስቅብን፣ ወላጆችን አሳባችንን ላይረዱት፣ እኛም መልካሙን ስማችንንና ሕይወታችንን ልናጣ ብንችልም፣ በሰማይ ስማችን የከበረ ይሆናል። እግዚአብሔርም የሚገባንን ዋጋ ይሰጠናል።

11ኛ ጥያቄ፡- ሉቃስ 1–2 አንብብ። ሀ) በዚህ ክፍል ስለ ኢየሱስና ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ምን እንማራለን? ለ) በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች ውስጥ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ስለ መሆን የተገለጹት እውነቶች ምንድን ናቸው? ሐ) ሦስት ዓምዶች ያሉት ሠንጠረዥ ሥራ። የሉቃስን ወንጌል ስታነብ፣ በመጀመሪያው ዓምድ መንፈስ ቅዱስ የተገለጸበትን ጥቅስ፣ በሁለተኛው ዓምድ መንፈስ ቅዱስ ያከናወነውን ተግባር፣ በሦስተኛው ዓምድ ደግሞ ዛሬ መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደዚያ ዐይነቱን ተግባር እንደሚያካሂድ ጻፍ። ይህንን ሠንጠረዥ ከትምህርት አሥራ ሦስት መጨረሻ በኋላ በቡድን ውይይት ላይ ታቀርባለህ።

ስለ መጪሑና ስለ መንገድ ጠራጊው መግቢያ (ሉቃስ 1–2)

1. ሉቃስ መጽሐፉን የጻፈበት ዐላማ (ሉቃስ 1፡1–4)

ሉቃስ የኢየሱስን ሕይወትና ሞት በዐይኑ አልተመለከተም። ነገር ግን ከኢየሱስ ጋር የነበሩ ሰዎች የነገሩትን ታሪክ ከመስማቱም በላይ፣ ስለ ኢየሱስ ሕይወት የሚገልጹ መጻሕፍትም አንብቧል። ሉቃስ የተማረ ሰው በመሆኑ እምነቱን በሌሎች እምነት ወይም ታሪክ ላይ ብቻ ሳይሆን፥ በእውነት ላይ እንዲመሠረት ይፈልግ ነበር። ለእምነቱ መሞት ካለበት ያመነው ነገር እውነት እስከ ሆነ ድረስ ሕይወቱን ቢያጣ ግድ አልነበረውም። ሉቃስ የኢየሱስን እውነት አምኖ ከተቀበለ በኋላ፥ ኢየሱስን አይተው ለማያውቁ ሌሎች ሰዎች ማሰብ ጀመረ። ስለሆነም በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ መጽሐፉን ጻፈ።

በጥንት ሥነ ጽሑፍ እንደተለመደው፣ ሉቃስ መጽሐፉን የጻፈው ለሚያሳትምለት ሰው ነው። ስለሆነም በጊዜው ሀብታም ክርስቲያን ለነበረው ቴዎፍሎስ ጻፈ። ሉቃስ መጽሐፉን የጻፈበትን ዓላማ ሲገልጽ ክርስቲያኖች እምነታቸው በእውነተኛ ታሪክ፣ ተአምራትን ባደረገው፣ ባስተማረውና ለዓለሙ ሁሉ በሞተው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተመሠረተ መሆኑን እንዲያውቁ ነበር። እንደ አስተዋይ ሳይንቲስት ሉቃስ ስለ ኢየሱስ የተጻፉትን መጻሕፍትና ታሪኮች በጥንቃቄ መርምሯል። የታሪኮቹን እውነተኝነት ካረጋገጠ በኋላም ሉቃስ ለዘመናት ሁሉ በታላቅነታቸው ከሚዘከሩ ታሪኮች አንዱን ሊጽፍ በቅቷል።

2. የመጥምቁ ዮሐንስ በተአምር መፀነስ (ሉቃስ 1፡5–25)

ሉቃስ የታሪክ ምሑር እንደ መሆኑ መጠን፣ ሁኔታዎቹ የተፈጸሙበትን ጊዜ ጠቅሷል። እነዚህ ሁኔታዎች የተፈጸሙት የይሁዳ ንጉሥ በሆነው በሄሮድስ ዘመን ነበር። ይህም ከፊል አይሁዳዊና ከፊል አሕዛብ የነበረ ሲሆን ጳለስቲናን ከ37 እስከ 4 ዓ.ዓ. ድረስ ያስተዳድር የነበረው ታላቁ ሄሮድስ ነው። ከሌሎቹ ወንጌላት ጸሐፊዎች ይልቅ ሉቃስ፥ የመጥምቁ ዮሐንስንና የኢየሱስን ልደት ጨምሮ በነገሮች አጀማመር እጅግ የሚደነቅ ጸሐፊ ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር አዲስ የዘመን ምዕራፍ የሚከፍተውና መሪ የሚመርጠው፥ አንድ የተለየ ሰው ሲወለድ ነው (ለምሳሌ፣ ሳምሶን፣ ሳሙኤል)። እግዚአብሔር ለመጥምቁ ዮሐንስና ለኢየሱስም ተመሳሳይ ነገርን አድርጓል። ሉቃስ ታሪኩን የጀመረው ከኢየሱስ የስድስት ወራት ቅድሚያ በነበረው በመጥምቁ ዮሐንስ ታሪክ ነው።

ሉቃስ የእነዚህን ታሪኮች ዝርዝር ከየት አገኘ? ስለዚህ በእርግጥ የምናውቀው ነገር የለም። በዚህ ጊዜ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ በሕይወት ያሉ አይመስልም። ሆኖም ስለ ዮሐንስ ልደትና የኢየሱስ የልጅነት ጊዜ ካቀረበው ዝርዝር መረጃ በመነሣት ሉቃስ የኢየሱስ እናት ከሆነችው ከቅድስት ማርያም ጋር ሳይነጋገር እንዳልቀረ እንገምታለን። ቅድስት ማርያም የኢየሱስን የልጅነት ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ ከዘመዱ ኤልሳቤጥ የሰማችውን የዮሐንስንም ልደት ታሪክ በሚገባ ታስታውሳለች።

የመጥምቁ ዮሐንስ ወላጆች የነበሩት ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ሁለቱም ከአሮን የክህነት ሐረግ ወገን ሲሆኑ፣ ኑሯቸውን የመሠረቱት በይሁዳ ነበር። በዘመኑ ከነበሩት ብዙ ካህናት በተለየ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ትእዛዛቱን በመጠበቅ ይገልጹ ነበር። ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር ሕይወታቸውን ባርኮ ነበር ማለት አይደለም። ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ልጅ ለመውለድ የማይችሉ መካኖች ነበሩ። ስለ እነዚህ ሰዎች በምናስብበት ጊዜ ለእግዚአብሔር በመኖራችን ብቻ የምንፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ እናገኛለን ማለት አይደለም።

በጊዜው ካህናት ሁሉ በ24 መደብ የተከፈሉ ነበር። እያንዳንዱ የካህናት ቡድን በየተራ በቤተ መቅደሱ ውስጥ መሥዋዕቶችን በማቅረብና ሌሎች ተግባራትን በማከናወን ያገለግል ነበር። እነዚህ የአንድ ቡድን አባላት ዕጣዎችን በመጣል አንዱን ካህን ይመርጡና፥ የተመረጠው ካህን ወደ ቅድስቱ ይገባል። ይህ ካህን ዘይት በመቅረዙ ውስጥ በመጨመር፣ ልዩውን ቅዱስ ጎብስት በሳምንት አንድ ጊዜ በአዲስ ጎብስት በመተካትና ዕጣኑን በተገቢው ጊዜ በማጥንቱ ውስጥ በመጨመር ያገለግላል።

ይህ የአገልግሎት ዕጣም አንድ ቀን ለዘካርያስ ደረሰ። እርሱም በቅድስቱ ሙሉ ዕጣኑን እያጠነ ሳለ፥ የጌታ መልአክ ተገለጦለት እርሱና ባለቤቱ ኤልሳቤጥ ልጅ እንደሚወልዱ አበሰረው። መልአኩ ስለዚህ ልጅ በጣም ግልጽ የሆኑ መመሪያዎችን ጨምሮ ሰጠው። ልጁ «ዮሐንስ» ተብሎ እንደሚጠራም ነገረው። ትርጉሙም «እግዚአብሔር ቸር ነው» የሚል ነው። በዚህ አኳኋን እግዚአብሔር ለዘካርያስና ለኤልሳቤጥ ልጅ በመስጠት ቸርነቱን ገለጠላቸው።

ከሁሉም በላይ ግን እግዚአብሔር የዓለም አዳኝ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲወለድ በማድረግ ለዓለም ሁሉ ቸርነቱን አሳየ።

ዮሐንስም እንደ ሳምሶን ሁሉ በናዝራውያን የአስተዳደግ ሥርዓትና ሕግ መሠረት ሳያድግ አልቀረም (ዘኍልቁ 6፡1–4 አንብብ)። ለምሳሌ፥ አልኮል እንዲጠጣ አልተፈቀደለትም ነበር። መልአኩ ዮሐንስ ለወላጆቹም ሆነ ለአይሁዶች በረከትን እንደሚያመጣ ገልጾአል። በእግዚአብሔርም ፊት ታላቅ ሰው ይሆናል ተብሏል። እግዚአብሔር የአይሁዶችን ልብ ወደ ራሱ ለመመለስ ይጠቀምበታል ብሏል። እርሱም በሚል. 4፡5–6 ላይ በተነገረው ትንቢት መሠረት ለመሢሑ መንገድ ጠራጊ መሆኑ የተነገረ ሲሆን፥ በተለየ መንገድ ከመወለዱ ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ እንደሚሆንም ተመስክሮለታል።

ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ለብዙ ዓመታት ልጅ ለማግኘት ያቀርቡት የነበረ ጸሎት ባለመሳካቱ ያዝኑ ነበር። ምናልባትም አንዳንድ መልካም ወዳጆቻቸው፣ «አይዟችሁ፣ እግዚአብሔር ጸሎታችሁን በመመለስ ልጅ ይሰጣችኋል» ሳይሏቸው አልቀሩም። ሆኖም ወዳጆቻቸው በየቀኑ በልጆቻቸው ተከብበው ሲሄዱ በሚያዩበት ጊዜ ልባቸው የበለጠ በሐዘን ሳይሞላ አልቀረም። ስለሆነም፣ መልአኩ ዘካርያስ ልጅ እንደሚያገኝ በነገረው ጊዜ በቃሉ ወዲያውኑ አላመነም። ምናልባትም የመልአኩን ቃል የተጠራጠረው፣ «እኔም ባለቤቴም አርጅተናልና ልጅ የመውለድ ተስፋ የለንም» በሚል ጥርጣሬ ይሆናል። ምንም እንኳ ዘካርያስ እግዚአብሔርን የሚወድና በታዛዥነት የሚመላለስ ሰው ቢሆንም፣ እግዚአብሔር በአብርሃም ሕይወት ውስጥ ያደረገውን ተአምር አላስታወሰም።

የመልአኩ ምላሽ ግን በጣም ፈጣን ነበር። የዘካርያስን አፍ በመዝጋት፥ ኤልሳቤጥ ልጁን እስከምትወልድበት ጊዜ ድረስ ድዳ እንደሚሆን ነገረው። ሁኔታው በዚህ አብቅቶ ዘካርያስ ወደ ቤቱ እንደ ተመለሰ እግዚአብሔር ቃሉን አከበረ። ኤልሳቤጥም አረገዘች። ሆኖም ልብዋ በተለያዩ አሳቦች እንደ ተሞላ ምንም አያጠራጥርም። ምናልባት ፅንስዋ ቀኑን ጠብቆ በደህና ስለ መወለዱ ሳትሰጋ አትቀርም። ያም ሆኖ የኋላ ኋላ ለማርገዝ በመቻሏም ደስ ብሏታል። ሉቃስ ለአምስት ወራት ያህል የትም ሳትሄድ ራሷን ደብቃ እንደቆየች ይነግረናል።

12ኛ ጥያቄ፡– እግዚአብሔር እኛ በምንፈልገው መንገድ ጸሎታችንን ባለመመለሱ፥ ተስፋችንና እምነትን ስለ ማጣት ከዚህ ታሪክ ምን እንማራለን?

3. ስለ ኢየሱስ መወለድ አስቀድሞ ተነገረ (ሉቃስ 1፡26–38)

ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ከሚኖሩበት አካባቢ በሰሜን በኩል ራቅ ብሎ በሚገኝ ስፍራ ምናልባትም 15 ወይም 16 ዓመት የሚሆናት አንዲት ልጃገረድ ትኖር ነበር። ይህች ልጃገረድ ለዮሴፍ የታጨች ነበረች። መልአኩ ገብርኤል አንድ ቀን መጥቶ መልካም ዜና ባበሠራት ጊዜ አባባሉ አሳብ ላይ ጣላት። ገብርኤል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስማቸው ከተጠሩ ሁለት መላእክት መካከል አንዱ ነው። ሌላው በስሙ የተጠራው ሚካኤል ነው (ዳን. 10፡21)። ገብርኤል ወሳኝ የሆኑ መልእክቶችን ከእግዚአብሔር ወደ

ሕዝብ የሚያደርስ ልዩ መልአክ ነው (ዳን. 8፡16፤ 9፡21–22 አንብብ።) ማቴዎስ፥ ማርያም መልአኩን በሕልምዋ እንዳየች ሲናገር፤ ሉቃስ ግን ፊት ለፊት እንደ ተነጋገሩ ይገልጻል። ማቴዎስ ስለ ኢየሱስ ልደት የተረከው ከዮሴፍ እይታ አንጻር ሲሆን፤ ሉቃስ ታሪኩን ያቀረበው ግን ከማርያም አንጻር ነው።

ገብርኤል ለማርያም ያስተላለፈው መልእክት በጣም ግልጽ ነበር። እግዚአብሔር በዓለም ታሪክ ውስጥ ልዩ ለሆነ ዓላማ መርጧታል። ልጅ ትወልዳለች። የልጁም ስም ኢየሱስ ይባላል። ይህም ኢያሱ ከሚለው የዕብራይስጡ ስም ጋር ተመሳሳይ ስያሜ ነው። የሁለቱም ስሞች ፍች፥ «እግዚአብሔር ያድናል» ወይም «እግዚአብሔር ደኅንነት ነው» የሚል ነው። ይህም የኢየሱስ ትልቁ አገልግሎት ለሰው ልጆች ደኅንነትን ማስገኘት እንደሆነ ያመለክታል። ኢየሱስ «የልዑል ልጅ» እንደሚባል ገብርኤል ለማርያም ገልጾላታል። አብዛኞቹ አይሁዶች «እግዚአብሔር» የሚለውን ቃል ለመጥራት ስለማይደፍሩ፤ ይህ «የእግዚአብሔር ልጅ» ለሚለው አገላለጽ ሌላው አማራጭ ነበር። ኢየሱስ ተስፋ የተሰጠው መሢሕና በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጥ ንጉሥ ነበር። ከዳዊት በተለየ አኳኋን የኢየሱስ አገዛዝና መንግሥት ዘላለማዊ ነው።

ሉቃስ ማርያም ከሌሎች ሴቶች ሁሉ በላይ ቅድስት መሆኗን አይነግረንም። ይልቁንም እግዚአብሔር ትምህርትን፤ ዘርን፥ ሀብትን መሠረት ሳያደርግ ሰዎችን ለዓላማው እንደሚመርጥ የሚያመለክት ምሳሌ ነው። ከሰው አስተሳሰብ አንጻር እግዚአብሔር የተማረችውንና ከልዩ ዘር የተወለደችውን ሀብታም ሴት ይመርጣል ብለን እናስብ ይሆናል። የገጠር ገበሬ ልጅ እንደ መሆኗ፥ ማርያም ከእነዚህ መስፈርቶች አንዱንም አታሟላም ነበር። ስለ ማርያም የምናውቀው ነገር ቢኖር እግዚአብሔርን የምትወድ ሴት መሆኗ ነበር። ይህ ታሪክ ባለን ስጦታ ተመክተን እንዳንታበይ ያስጠነቅቀናል። የመዝሙር ስጦታ ቢኖረን ይህ የሆነው በራሳችን ችሎታ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ነው። ቁሳዊ በረከት፤ ጥሩ ቤተሰብ፤ ልዩ ችሎታ፤ ውበትና መልካም ገላ ቢኖረን፤ ይህንን ሁሉ ለማግኘት ያደረግነው ጥረት እንደሌለ መገንዘብ ይኖርብናል። ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ትምክህት እንዳይገዛንና ከእኛ የተሻሉ ናቸው ብለን በምናስባቸው ሰዎች እንዳንቀና ይህንን ማስታወስ አለብን። ይህ የእግዚአብሔር ምርጫና ስጦታ እንጂ የእኛ እንዳልሆነ መገንዘብ አለብን።

13ኛ ጥያቄ– ሀ) እኛ ልንቆጣጠራቸው በማንችላቸው እንደ ዘር፥ ትምህርት፤ ሀብት፤ ውበት በመሳሰሉት ነገሮች የምንታበየው እንዴት ነው? ለ) ከእኛ በተሻሉ ሰዎች ላይ የምንቀናው ለምንድን ነው? ሐ) ስንታበይ ወይም ስንቀና እግዚአብሔር በሕይወታችን ላይ ስላለው ሉዓላዊ ፈቃድ የምንዘነጋው ነገር ምንድን ነው? መ) የአንተን ሕይወት ከምታውቀው አንድ ለማኝ ጋር አነጻጽር። የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫና ስጦታ ባይኖር ኖሮ፥ እንደዚያ ሰው ልትሆን ትችል የነበረው እንዴት ነው?

ባለን አንድ ልዩ ስጦታ መታበይ ወይም በሌላው ሰው መቅናት ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ናቸው። ሁለቱም መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የስጦታዎች ሁሉ ምንጭ እንደሆነ ከሚያስተምረው አሳብ ውጭ ናቸው።

እነዚህ ኃጢአቶች ካሉብህ አሁኑኑ ንስሐ ግባ። እግዚአብሔር ስለ ሰጠህ ስጦታ የሚያመሰግን ልብ እንዲሰጥህ ጸልይ። ስጦታዎችህን ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዳታነጻጽር ትሑት እንዲያደርግህ እግዚአብሔርን ለምን።

«ይህ እንዴት ይሆናል?» የሚለው የማርያም ምላሽ፥ ከዘካርያስ ጥርጣሬ ጋር ተመሳሳይ ነው። ነገር ግን መልአኩ ዘካርያስን የቀጣው ሲሆን፤ ማርያምን ግን አልቀጣትም። ለምን? ምናልባትም ከጥርጣሬያቸው በስተ ጀርባ የተለያዩ አመለካከቶች ሊኖሯቸው ይችላሉ። የዘካርያስ አቀራረብ ልጅ ለመውለድ እንደማይችል በማሰብ እግዚአብሔርን እንደ ተጠራጠረ የሚያመለክት ይሆናል። የማርያም አቀራረብ ግን እግዚአብሔር የሚሠራበትን መንገድ ለማወቅ የጠየቀች ይመስላል። ያላገባች ልጃገረድ እንደ መሆኗ ከወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አድርጋ አታውቅም። እስከታገባ ድረስ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ እንደማትችል ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል። በታሪክ ደግሞ ከወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳታደርግ ያረገዘች ሴት ኖራ አታውቅም። እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጅ በማርያም ማሕፀን ውስጥ ሊፀነስ የሚችለው እንዴት ነው? የመልአኩ መልስ ለማርያም ትርጉም የሚሰጥ አይመስልም። መንፈስ ቅዱስ በሰውነቷ ውስጥ ተአምር በመሥራት ከወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳታደርግ የምትፀንስበትን ተግባር እንደሚፈጽም ነበር የገለጸላት።

14ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ልጅህ በመንፈስ ቅዱስ ተአምር አርግዣለሁ ብትልህ ምላሽህ ምን ይሆናል? ታምናታለህ? ለምን? ለ) ያላገባች የቤተ ክርስቲያናችሁ አባል አርግዛ ብትገኝ ከቤተሰቧ፣ ከጓደኞቿና ከቤተ ክርስቲያን የሚገጥማት ችግር ምን ሊሆን ይችላል? ሐ) የማርያም ምላሽ በእግዚአብሔር ላይ ያላትን አስደናቂ እምነት የሚያሳየው እንዴት ነው?

ማርያም ገና ወጣት ብትሆንም፣ «እኔ የጌታ ባሪያ ነኝ። እነሆም፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ» በማለት የሚያስገርም መንፈሳዊ ብስለት አሳይታለች። በእዚህም ማርያም ከቤተሰቧ ለመፈናቀል ፈቃደኛ መሆኗን ገልጻለች። ምክንያቱም በዚያን ዘመን ከጋብቻ ውጭ ያረገዘች ሴት ልጅ ለቤተሰቡ ትልቅ ሐፍረት እንደምትሆን ይታመን ነበር። ከጋብቻ በፊት የወለደች ሴት የሚያገባ ሰው ስለማይኖር፣ ያለ ጋብቻ ለመኖር ወሰነም ነበር። በመላው ሰዎች ሊሰድብዋት ከፈለጉ ሳይከፋት በገሊላ የዲቃላ እናት ተብላ ለመጠራት ዝግጁ ነበረች። ለዚህም ምክንያቱ ለእግዚአብሔር ያላት ፍቅርና ታዛዥነት ነበር። እግዚአብሔር ነገሮችን እንዴት እንደሚሠራ ባታውቅም፣ ስለ እግዚአብሔር መነቀፍን መርጣለች።

4. ማርያም ኤልሳቤጥን ጎበኘች (ሉቃስ 1፡39–56)

መልአኩ በቅርቡ ስለሚፈጸመው ሁለተኛው ተአምራዊ ልደት ለማርያም ነግሯት ሲሄድ፥ ማርያም በልቧ ውስጥ የሚጋጭ ስሜት እንደ ፈጠረባት ልንገምት እንችላለን። ማርያም ስለዚሁ ጉዳይ ለመነጋገር በመፈለጓ ምክንያት ብዙ ኪሎ ሜትር ተጉዛ ወደ ዘመዱ ወደ ኤልሳቤጥ ዘንድ ሄደች። በአይሁድ ባሕል ወጣት ሴቶች ከቤታቸው ወጥተው ሩቅ መንገድ ለመሄድ ስለማይችሉ፤ ይህንን ማድረጉ ለማርያም ቀላል አልነበረም።

እግዚአብሔር አንድ ከባድ ነገር እንድናደርግ ሲጠይቀን፥ አብዛኛውን ጊዜ የሚያበረታታንን ነገር ያደርጋል። ማርያም ኤልሳቤጥን በነበኘች ጊዜ መጥምቁ ዮሐንስ በኤልሳቤጥ ማሕፀን ውስጥ ዘለለ። በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በኤልሳቤጥ ላይ በመውረዱ፥ ማንም ሳይነግራት ማርያም ታላቅ ልጅ እንዳረገዘች አወቀች። አሁንም ኤልሳቤጥ የሆነውን በትክክል መገንዘቧ አጠራጣሪ ነው። እግዚአብሔር እንዴት ሰው ሊሆን ይችላል? ምንም እንኳ ግሪኮች እንዲህ ዓይነት አፈ ታሪክ ቢኖሯቸውም፣ ይህ ለአይሁዳውያን ስድብ ነበር። ይሁንና የማርያም ልጅ አምላክ እንደሆነ ኤልሳቤጥ ተገንዝባ ነበር።

ሉቃስ በመጽሐፉ ውስጥ ካካተታቸው ልዩ ነገሮች መካከል፥ በዚህ ወቅት ሰዎች የሰጡትን ምላሽ ያንጸባረቁዋቸውን ምላሾች በመዝሙር መልክ መጻፉ ነበር። በዚህ ክፍል አራት መዝሙራት ተመዝግበው የሚገኙ ሲሆን፣ ከእነዚህም የመጀመሪያው የማርያም ነው። ማርያም ይህንን የማጽናኛ ቃል ከተቀበለች በኋላ በርካታ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች የሚገኙበትን መዝሙር ለመዘመር ችላለች። የተዋረደችውን ልጃገረድ እግዚአብሔር ስለ መረጠ አመሰገነች። ይህ ከታላቅነቷ ወይም ከኃጢአት-የለሽነቷ የተነሣ (ካቶሊኮችና ኦርቶዶክሶች እንደሚያስተምሩት ሳይሆን)፣ ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ እንደሆነ ተገንዝባ ነበር። ምሕረት ታላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሲሆን፣ ፍችውም እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ የማይገባንን ነገር እንዳደረገልን የሚያመለክት ነው። የማርያም መዝሙር እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ከሰዎች በተለየ አቅጣጫ የሚሠራበትን ሁኔታ ያመለክታል። ሰዎች ለባለጠጎችና ለጎያላን ሲያሸረግዱ፣ እግዚአብሔር እንዴት ገሥጾችን እንደሚያዋርድ፣ ባለጠጎችን ባዶአቸውን እንደሚሰድድና ሰዎች የሚኩራሩበትን ነገር እንደሚያፈርስ ማርያም በመዝሙሯ ገልጻለች። በአንጻሩም፣ እግዚአብሔር እንደ ማርያም ያሉ የተዋረዱ ሰዎችን ከፍ ከፍ ያደርጋል፥ ያከብራል። እንደ ማርያም ያሉ ድሆችን ይመግባል፥ ይባርክማል። ማርያም ስለ መሢሑ የተረዳችው ከብሉይ ኪዳን የነቢያት መጻሕፍት ነው። ይሁንና እንደ ብዙዎቹ አይሁዶች ማርያም መሢሑ በመጀመሪያ መከራ መቀበል እንዳለበትና በምድር ላይ የሚነግሠው ከዚያ በኋላ እንደሆነ አልተገነዘበችም ነበር። ለዚህም ነው ማርያም ግራ በመጋባት ኢየሱስ የአእምሮ ችግር እንዳለበት ሰው ያሰበችው (ማርቆስ 3፡21 አንብብ)።

ሉቃስ ማርያም ከኤልሳቤጥ ጋር ሦስት ወር እንዳሳለፈች ገልጾአል። ኤልሳቤጥ በዚህ ጊዜ የስድስት ወር እርጉዝ ስለ ነበረች፣ ማርያም መጥምቁ ዮሐንስ እስኪወለድ ድረስ እዚያው ቆይታለች ማለት ነው። ማርያም ወደ ዮሴፍ ዘንድ የመጣችው የሦስት ወር እርጉዝ ሆና ምናልባትም ከኤልሳቤጥ ዘንድ ከተመለሰች በኋላ ሳይሆን አይቀርም።

5. የመጥምቁ ዮሐንስ መወለድ (ሉቃስ 1፡57–80)

በዚህ ታሪክ ሉቃስ የኢየሱስ መንገድ ጠራጊ ወደሆነው ወደ መጥምቁ ዮሐንስ መወለድ ይመለሳል። በአይሁድ ባህል መሠረት፣ ዮሐንስ ስምንት ቀን ስለ ሞላው ከተገረዘ በኋላ ስም የማውጣት ሥነ ሥርዓት ተካሄደ። አይሁዶች ብዙ ጊዜ ልጅን በአባት ወይም በዘመድ ስም ይጠሩ ስለ ነበር፣ ጎረቤቶቻቸው ዘካርያስ ብለው ሊሰይሙት ፈለጉ። ነገር ግን ኤልሳቤጥ ልጁ

ዮሐንስ መባል እንዳለበት ታውቅ ነበር። ስለዚህ ዘካርያስም ልጁ ዮሐንስ መባል እንዳለበት በጽሑፍ ገለጸ። ሰዎቹ እግዚአብሔር ተአምር እንደ ሠራ ያውቁ ስለ ነበር፣ ዮሐንስ ታላቅ ሰው እንደሚሆን ባይጠራጠሩም፥ ነገር ግን ልባቸውን ለመሚሔ የሚያዘጋጅ ታላቁ ኤልያስ መሆኑን አላወቁም ነበር።

ዘካርያስ የልጁ ስም ዮሐንስ እንደሆነ ለሕዝቡ በተናገረ ጊዜ፥ እግዚአብሔር አፉን ከፈተለት። በዚህም ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በመዝሙር ትንቢት ይናገር ጀመር። (ይህ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ሁለተኛው መዝሙር ነው።) ዘካርያስ እግዚአብሔርን ያመሰገነው ስለ ልጁ ሳይሆን፥ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ስለሚፈጸመው ነገር ነበር። ዘካርያስ እግዚአብሔር በጥንት ዘመን የተነገሩ ትንቢቶችን እንደሚፈጽም ይገነዘብ ነበር። በተጨማሪም የዮሐንስና የመሚሔ መምጣት የእግዚአብሔርን አገዛዝ የሚያመለክት መሚሓዊ ዘመን መሆኑን ያውቅ ነበር። እስራኤላውያን አሁን ከኃጢአታቸው ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብ ተላልፈው ከተሰጡበት ባርነትም ነፃ ይወጣሉ፥ ጠላቶቻቸውም ይሸነፋሉ። የሰዎች ልብ ተለውጦ ያለ ፍርሃት፣ በቅድስናና በጽድቅ ያገለግላሉ። ምንም እንኳ ዘካርያስ ልጁ መሚሔ እንዳልሆነ ቢያውቅም፣ እግዚአብሔር በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጠቀምበት ይገባው ነበር። ዮሐንስ የልዑል እግዚአብሔር ነቢይ እንደሚሆን ተረድቶ ነበር። ሥራውም ሰዎች ከኃጢአታቸው ተመልሰው የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንዲጠይቁ በማድረግ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለመሚሔ እንዲዘጋጁ ማድረግ ነው። ዘካርያስ የተገነዘበው ልጁ ከሁሉም የሚልቅ ታላቅ ሰው እንደሚሆን ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሚሆን ነበር።

መሪዎች ቅንዓትና ኩራትን ከሚያሳዩባቸው መንገዶች አንዱ፥ የልጆች አያያዝ ነው። ለልጆቻችን ከሁሉም የተሻለውን እንመኝላቸዋለን። ብዙውን ጊዜ ይህ ማለት ደግሞ እኛን የሚተኩ መሪዎች እንዲሆኑ እንሻለን ማለት ነው። ልጆቻችን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የሚገቡበትን ወይም የወጣት ማኅበራት መሪዎች የሚሆኑበትን መንገድ ለማመቻቸት እንጥራለን። ይህ ለቤተ ክርስቲያን በጣም አደገኛ ነገር ነው። ትልቁ ምኞታችን የእግዚአብሔር ክብር እንጂ የልጆቻችን መሆን የለበትም። ስለሆነም በአመራር ስፍራ ላይ ካለን መሪ መሆን የሚገባቸው የመሪነት ስጦታ ያላቸው (በእግዚአብሔር የተመረጡ) ሰዎች ብቻ ሊሆኑ እንደሚገባ መገንዘብ አለብን። እግዚአብሔር የሌላውን ሰው ልጅ ለመሪነት ከመረጠው፣ የእግዚአብሔርን ምርጫ በማክበር ደስ ልንሰኝ ይገባል። እግዚአብሔር በመንግሥቱ ውስጥ ለሁሉም ሰው የተለያዩ ስጦታዎችን ስለሚሰጥ፣ ለልጆቻችንና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች መመኘት የሚገባን ሁላችንም የየራሳችንን ልዩ ስፍራ ለይተን ለእግዚአብሔር ክብር እንድናውለው ነው።

15ኛ ጥያቄ፡– ሀ) እንደዚህ ማሰቡ አስቸጋሪ እንደሆነ የምታስበው ለምንድን ነው? ለ) የእግዚአብሔር ስጦታ ከሁሉ የሚሻለውን እንዲወስኑ በማድረግ ፈንታ፥ አንድ መሪ ልጁን ወደ መዘምራን ወይም ወደ ሌላ የተለየ አገልግሎት ለማስገባት በሚሞክርበት ጊዜ ምን ዐይነት ችግሮች ሊከሰቱ አስተውለሃል?